# ርዕሰ አንቀፅ

## የተገነባን አንናድ፤ ስንገነባ በዐለት ላይ እንገንባ

ቤቱን ለመስራት አጥልቆ የቆፈረና በዐለት ላይ መሰረቱን የጣለ ሰው ጎርፍ በመጣ ጊዜ የውሃው ሙላት ገፍቶ አይጥለውም:: በአግባቡ ስለታነፀ ሊያነቃንቀው አይቻለውምና:: ይህን ጉዳይ በቤት ግንባታ አየነው እንጂ በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እንቅስቃሴም እውነታው ይታያል:: በአስረሽ ምቺው የተዋቀረ ማንኛውም አይነት አስተዳዳር ጠንከር ያለ ጐርፍ ከመጣ ገፍትሮ ይጥለዋል:: እንደ ድክመቱ መጠን ጐርፍ ይዞት ይሄዳል፤ አለበለዚያ እንደምንም ተንደፋድፎ ይቆማል:: የምንተክለው ዛፍ መልካም ከሆነ መጥፎ ፍሬ አያፈራም፤ መጥፎ ዛፍ ሆኖ መልካም ፍሬ የሚያፈራ የለም:: ዛፍ ሁሌም በፍሬው ይታወቃል፤ ከእሾህ የበለስ ፍሬ አይለቀምም፤ ከቀጋ ቁጥቋጦ የወይን ፍሬ አይቆረጥም:: መልካም ስርዓት ከሌለ ምስቅልቅሎሽና የሰው ልጅን የእለት ተእለት መሰረታዊ ፍላጐቶችን የሚያቃውስ ሁኔታ ይፈጠራል::

ከመደንርደሪያችን ለመግለፅ እንደሞከርነው የአንድ ነገር መሰረት ጠንካራና ቀናነትን ማዕከል አድርጐ መቆም አለበት:: በሶስተኛ ሀገራት በተለይ በአፍሪካ፤ በይበልጥ ደግሞ በኢትዮጵያ መሰረቱ የፈረጠመ የአወቃቀር ሂደትን ተከትሎ የተመሰረተ ስርዓት እስካሁን አላየንም:: በተለያየ ጊዜ የተፈራረቁት አገዛዞች የነበረውን እየናዱ በሌላ አዲስ አወቃቀር የመተካቱ ነገር የመንግስታቱ አይነተኛ መለያ ነው:: አንድ ስርዓት መጥፎ ገፅታዎች ቢኖሩትም ጥሩ ነገሮቹን በመጥፎ ማጨማለቅ በኢትዮጵያ የተፈራረቁ አገዛዞች በተደጋጋሚና በተግባር አሳይተውናል:: ለዚህም ይመስላል «ከክስተት አካሚነት» የዘለለ ሚና ሳይኖራቸው በእርዳታ ጥላ ስር የመኖር ውል ፈራሚዎች ለመሆን የተገደድነው:: በዚህ የተነሳ ለረጂዎች አጐብዳጅ ሆነን፤ የሀገርን ጥቅም ሳይሆን የሌሎች ሀገራት ጉዳይ በማስፈፀም ተግባር ራሳችንን የምንጠምድ ሁነናል:: ዛሬ እናራምደዋለን ብለን ቃል የገባነውን አስተሳሰብ በወራት ልዩነት በሌላ ተቃርኗዊ አስተሳሰብ መተካት የእኛ መለያ ከሆነ ውሎ አድሯል:: ከሁለት አመት በፊት ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአንዱ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለሀገራችን እና ለመንግስታቸው የዋስትናቸው ምንጭ እንደሆነ በተደጋጋሚ ገልፀዋል:: ዴሞክራሲ ማለት ለእሳቸው ለችግሮች ሁሉ የመፍትሔ ቀንዲል እንደነበር አበክረው ሲናግሩ ተደምጠዋል:: ከ97ቱ ምርጫ ማግስት በነበሩ ጊዜያት ሁሉ ለፓርላማ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት ሳያሳልሱ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ለሀገራችን ለሁለንተናዊ ዋስትና መረጋገጥ አይነተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው አስምረው ተናግረዋል:: ከወራት በኋላ ግን የገልፍ ሀገራትን ርዕዮት ማቀንቀን ጀምረዋል:: በተለይ The African developmental Stage በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት በፊት የኢኮኖሚ ግንባታ መቅደም እንዳለበት የሚያበስር አስተሳሰብ አንፀባርቀዋል:: በእርግጥም እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ በሀገሪቱ ወደ ተግባር የተቀየረ እስኪመስል ድረስ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው:: የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ቀደም ሲል ከነበራቸው በባሰ መልኩ ወደ ኋላ በመመለስ ከመገንባት ይልቅ በተቃራኒው መልኩ ስርዓቱን ወደ መናድ ተቀይረዋል:: አንድ ስርዓት ስንጠነስስ ፍሬውንም ለማየት እና ለመቅመስ ዝግጁዎች ልንሆን ይገባል:: ስለዚህ የምንጠነስሳቸው አስተሳሰቦችም ሆኑ ወደ ተግባር የምንለውጣቸው ማናቸውም ሂደቶች መሰረታዊ የሆነ እድገታቸውን ጠብቀው እንዲሆኑ የማድረግ ሀላፊነት አለብን:: ስለ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ስናወራ መሰረታዊ ስለሆኑ የስርዓቱ መርሆች አደረጃጀትና አቀነጃጀት ማሰብ እና ማሰላሰል ያስፈልጋል::

ወደ ተግባር ስንቀይረው አንድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሊበስል በሚገባው መልኩ እየተጓዘ ስለመሆኑ እርግጠኞች ልንሆን ይገባል:: ለስርዓቱ መስፈን የሚደራጁ ተቋማት

ሁኔታ፤ የሚያስፈፅሙትን ደንቦች እና ህጐች፤ የማህበረሰባዊ ፖሊሲ አወቃቀር፤ የስልጣን እርከን አወቃቀር፤ በተለይም የህጐች ሁሉ የበላይ የሆነው ህገ መንግስት ለምንፈጥረው ስርዓት ተስማሚ መሆኑን እርግጠኞች ልንሆን ይገባል:: በዚህ መልኩ መሰረቱን የጣለ ስርዓት በነጋና በጨለመ ቁጥር የምናበራው እና የምናጠፋው አይሆንም:: ምክንያቱም ተቋማዊ ይዘት ያለው አደረጃጀትን ስለምንፈጥር እንደ ቤታችን መብራት ስንተኛ የምናጠፋው ስንነሳ የምናበራው አይሆንም:: ስለዚህ አንድ ስርዓትን ስንጠነስስ የጠነሰስንበት ጋን በትክክል መቀመጡን ማረጋገጥ ይገባናል::

የምንገነባው የሀገር «ራዕይ» እና የወደፊት እጣ ፈንታ በአለት ላይ ስለመገንባቱ እርግጠኞች እንሁን:: አንድ ሀገርን ስንገነባ የባለስልጣኖች ፍላጐትን ያማከለ ብቻ መሆን የለበትም:: መነሻውም መድነሻውም መሆን ያለበት ከላይ እስከ ታች ያለውን የሀገራችንን ህዝብ ነው:: አንድ ሀገር እንደ ሀገር ራዕይ ይኖራታል:: በየደረጃው ያሉ ዜጎች ለራዕይዋ ስኬት የሚረዷትን ግቦች ታስቀምጣለች:: እነዚህ ግቦች በአቋራጭ በሚመጡ ሌሎች ግቦች መተካት የለባቸውም::

የፖለቲካ ልሂቃኖቻችንም ቢሆኑ አንዴ ዴሞክራት በሌላ ግዜ «ልማታዊ መንግስት» የመሆን እና የአቋም መሸራተት እንዳያሳዩ መሰረቱን ጠብቆ የተገነባ ስርዓት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል:: አገሪቷን ያዋቀርንበት ስርዓት የተረጋጋ እና ተቋማዊነት የሌለው በሚሆን ጊዜ ነፀብራቁ በሀገሪቷ የእለት ተዕለት ክስተት ውስጥ እናየዋለን:: የምንቀርፃቸው አሰራሮችና የፖሊሲ «Durability» ወጥነት እንዳይኖር ይረዳል::

እንዲህ አይነቱን ነገር በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚታይ አይደለም:: በአብዛኛው የመንግስት አወቃቀር የዘመቻ እንጂ ወጥ የሆነ ፖሊሲዎችን በተግባር በማዋል ላይ የተመሰረተ አይደለም:: የኢኮኖሚያችን አወቃቀር ሆነ የመንግስት የእለት ተእለት ስራ ባለስልጣኖቻችን ለኦፐን ዩኒቨርሲቲ የ«መመረቂያ ፅሁፋቸውን» ባቀረቡ ሰሞን በሀገሪቱ ላይ ወደ ተግባር ለመለወጥ ሲባል የሚከወኑ ይመስላሉ:: ሌላ መፀሀፍ ሲያነቡ ደግሞ በሌላ ገፅ ላይ የሀገሪትዋን እጣ ፈንታ ለማስኬድ ይሞክራሉ:: አልያም የራሳቸውን ህልውና በማሰብ የአስተዳደር መዋቅሩን መሪ ወደ አንድ አቅጣጫ ይጠመዝዙታል:: ለዚህ ትልቁ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተረቀቁና ለመፅደቅ በመንደርደር ላይ ያሉት እና የፀደቁ ህጐች ናቸው:: ፓርቲዎችን ለማስተዳደር የፀደቀው ህግ፣ የፕሬስ ህግ፣ እና የግብረሰናይ ድርጅቶችን የሚያስተዳድሩ ህጐች ተጠቃሾች ናቸው:: እነዚህን ህጐች ለተመለከተ በአንድ ወቅት «ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የህልውናችን ዋስትና ነው:: ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውጭ ምንም አማራጭ የለንም» ተብሎ በተነገረበት ፓርላማ ፊት ቀርበው የፀደቁ ስለመሆናቸው እንዲጠራጠር ያደርገዋል:: ምክንያቱም መሰረቱ የበሰለ፤ በአለት ላይ የተገነባ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባትም ሆነ አንድ ኢንች የኢትዮጵያን ችግር ለመግፋት የሚያስችሉ አይደሉም::

የመንግስት አሰራርም ቢሆን ወጥነት ያለው አይደለም:: ዛሬ የጠነሰስነውን አወቀቃር ነገ በሌላ «ሪፎርም» አፈር ከድሜ ሲሆን አስተውለናል:: ከዚያ እንደገና ከዜሮ እንጀምራለን:: አንድ አሰራር ሲዘረጋ መጀመሪያ ጥቅምና ጉዳቱ ይጠናል:: ባገኘነው ተሞክሮ መነሻነት ድክመቶችን አርሞ ሌላ የተሻለ ስኬት ለማስመዝገብ እንጂ ዛሬ የነበረውን ነገ እንዳልነበረ ማድረግ የአሰራር ጥራትንም ሆነ መልካም አስተዳደርን አያሰፍንም:: በመልካም ሁኔታ ያልተያዘ የመንግስት ሰራተኛ መልካም አስተዳደርን ያሰፍናል ብሎ ማለት ከህልምነት የዘለለ አይደለም:: አንዴ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ Civil Service reform በሌላ ጊዜ ደግሞ በቢ.ፒ.አር የምናሽማቅቀው የመንግስት ሰራተኛ (የሰራ ዋስትውን ላም አለኝ በሰማይ ሆኖበት) በምን መመዘኛ የመንግስትን የመልካም አስተዳደር እና የአደረጃጀት ብቃትን የማረጋገጥ ተግባርን እውን ማድረግ ይቻለዋል? ሁሌም ቢሆን ጉርፍ በመጣ ቁጥር የሚሸረሸር እና የሚንገዳገድ መዋቅር ከመፍጠር ይልቅ ማኛውም አይነት ጫናዎች ሲመጡ ሊሸከም የሚችል ተቋማዊ ስርዓት ልንገነባ ይገባል እንጂ በራሳችን ድክመት የተከሰተውን ቀውስ ዜጐችን ከስራ በማፈናቀል ለውጥ ለማስመዝገብ አይቻልም:: ምናልባት ፖለቲካዊ መፍትሔ ሊኖረው ቢችልም!

መንግስታት ሁሉ በኢትዮጵያ ሲነግሱ የራሳቸው የሆነ ደካማም ጠንካራም ጐኖች ይኖሯቸዋል፡፡ ለጠንካራዎቹ እውቅና ስጥተን ደካማ ጎናቸውን ወደ ማሻሻሉ መንዝ ይኖብናል፡፡

ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ህልም አለኝ ሲል መሰረት ስለመጣሉ እርግጠኛ ነበር፡፡ በእርሱ የተፀነሰው እውነት እና አሜሪካውያን በጠነሰሱት መሰረት አንድ ቀን የሰው ልጆች እኩልነት በሀገራቸው እንደሚረጋገጥ ያልሙ ነበር፡፡ እናም የቀለም ልዩነት ሳይበግራቸው በውስጣዊ ማንነቱ ብቻ ባራክ ኦባማን ለትልቁ  የአለማችን ስልጣን አብቅተውታል፡፡ ይህ የአሜሪካውያን የስርዓት መዋቅር በአለት ላይ ስለመገንባቱ ትልቁ ማስረጃ ነው፡፡ የአጭር ጊዜ የከተፋ ፓለቲካና የአስረሽ ምቺው አደረጃጀት መሪዎቿ የሚከበሩባት ሳይሆን መሪዎቿ ከስልጣን በኋላ የሚሰደዱባት አገር ነው የምንገነባው፡፡ ስለዚህ ለሁላችንም የምትሆን አገር ለመገንባት ስናስብ ሁሌም ቢሆን መሰረታችንን በጠነከረ መልኩ ስለመገንባታችን እርግጠኞች እንሁን፡፡ ህልምን እንጂ ገበታችንን አንየው፡፡ ራዕያችንን  እንጂ ኪሳችንን አንዳስሰው፡፡ ያኔ አገራችንን የምንገነባበትን የአለት መሰረት እናገኛለን፡፡ ኢትዮጵያን በመላ ሳይሆን በመርህ እንመራታለን፡፡ በዜግንታችን የምንሰራበትና በምላሹ የምትጠረን አገር እንገነባለን፡፡
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር፡፡

# <u>ዜናዎች</u>

## ሁለት ባለሀብቶች በአንድ ሳምንት እራሳቸውን አጠፉ

የተለያዩ የተዘጋጁ ልብሶችን ብትን ጨርቆችን ድርና ማግ አስመጥቶ በማከፋፈል የንግድ ዘርፍ የሚታወቁት የጌታነህ ትሬዲንግ እና የጌታነህ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለቤት አቶ ዮሐንስ ጌታነህ ሀሙስ ታህሳስ 9 ቀን 2001 ዓ.ም ጉለሌ አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ራሳቸውን ገድለው መገኘታቸው የሚታወስ ነው፡፡

ከሁለት ቀናት በኋላ ባለፈው ቅዳሜ ደግሞ የአሴ ማርብል እና የአሴ ሴራሚክ ባለቤት የሆኑት አቶ ምክንያቱ ባልታወቀ ጉዳይ በተመሳሳይ ሁኔታ ራሳቸውን እንዳጠፉ ለማወቅ ተችሏል  የካንጋሮ ፎም ባለቤት ልጅ እንደሆኑ የሚነገርላቸው እኒሁ ባለሀብት አሴ ማርብል እና አሴ ሴራሚክ በተባሉ ድርጅቶቻቸው የተለያዩ የሴራሚክ ውጤቶችን ለገበያ እንደሚያቀርቡ እና ለበርካታ ወገኖች የስራ እድል በመክፈት በርካታ ሰራተኞችን እንደሚያስተዳድሩ የድርጅቱ ሰራተኞች በሀዘን ይገልጻሉ፡፡

ባለፈው ሐሙስ የጌታነህ ትሬዲንግ እና የጌታነህ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለቤት የሆኑት አቶ ዩሐንስ ጌታነህ ከቀኑ በ7:00 ሰዓት ገደማ በመኖሪያ ቤታቸው ራሳቸውን በጥይት ገድለው መገኘታቸው የሚታወስ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የአሴ ማርብል እና የአሴ ሴራሚክ ባለቤትም በተመሳሳይ ሁኔታ ለህልፈት መዳረግ ለብዙዎች እንቆቅልሽ እንደሆነባቸው አስተያየት ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡

# መጣጥፎች

# «ጫማው ቀርቶብኝ ጥያቄ በወረወርኩ»


**የኢትዮጵያ ጋዜጠኛ**

**አቤ ቶኪቻው**

abeto2007@yahoo.com


ወዳጄ እንዴት ሰንብተዋል? ይቺ ቀጭን ኑሮ እንዴት አድርጋዎታለች? እኔ እየታገልኩኝ ነው:: ጫካ ሳልገባ መሳሪያ ሳልታጠቅ ከኑሮ ጋር ሰላማዊ ትግል እያደረኩኝ እገኛለሁኝ:: በነገራችን ላይ ባለፈው ሳምንት ውስጥ አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ (አንድነት) ፓርቲ አንድ ጋዜጣዊ መግለጫ አውጥቶ ነበር:: መግለጫው «የመንግስት አካላት የሚያደርጉት ህገወጥ ጫና እንቅስቃሴያችንን አይገታውም» የሚል ሲሆን ውስጡ ያሉት እና በተደጋጋሚ በፓርቲው ላይ ደረሱ የተባሉትን ጫናዎችን የተመለከተ አንድ ወዳጄ ይሔ ፓርቲ ይሔንን ሁሉ ነገር ታግሶ እስከ ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለት ከደረሰ ስሙን «ችሎ ማደር» ቢለው ይሻላል ብሎኛል ትግስታቸውን በማድነቅ:: እውነትም ግን የደረሰባቸው ሁሉ ሃቅ ከሆነ «ይቺ ሰላማዊ ትግል አታዋጣም» ለሚሉት ሰዎች የማስረጃ ግብዓት ሳትሆን አትቀርም የሚል ስጋት አለኝ:: ለነገሩ ሰላማዊ የትግል ስልት አጅግ ውጤታማ የሚሆነው ከኑሮ ጋር ሲሆን ነው:: (ከመንግስት ጋር ሰላማዊ ትግል አያዋጣም አላልኩም:: ሰላም ማጣት መች አማረኝ:: ለኑሮ ግን በጣም ያዋጣል ባይ ነኝ::)

እስከ አሁን ከኑሮ ጋር ባደረኩት ሰላማዊ ትግል ውጤታማ ሆኜበታለሁኝ:: ለምሳሌ እቤት ውስጥ የመዋል አድማ፣ ይህ ከሰላማዊ ትግል ዘዴዎች አንዱ ነው:: እናም ለዘንድሮ ኑሮ ከቤት ውስጥ ሳይወጡ መዋል ከተለያዩ አጓጉል ወጪዎች ስለሚጠብቅ ውጤታማነቱ የተመሰከረለት ነው:: ሌላው የርሃብ አድማ ነው፣ በተለይ ኑሮው የከፋው በሚበሉ ነገሮች ላይ ስለሆነ ይህ አይነቱ ሰላማዊ ትግል /ርሃብ አድማ/ ማድረግ የተጨበጨበለት የትግል ስልት ነው:: ሌላው ከኑሮ ጋር ለሚደረገው ሰላማዊ ትግል አይነተኛ ዘዴ የማንኛውንም ሃገር ምርት እና አገልግሎት አለመጠቀም ነው:: በዚህም ወጪዎን መቶ በመቶ መቀነስ ይቻላል:: ወዳጄ ከኑሮ ጋር እያደረኩት ስላለው ሰላማዊ ትግል ወደፊት ሰፋ አድርጌ አስተማሪ በሆነ መልኩ ልምዴን ላካፍልዎ ቃል እገባለሁኝ:: እልቅስ እኛ በእንዲህ አይነት ሰላማዊ ትግል እየታገልነው ያለ ኑሮ ልማታዊ ባለሃብቶቻችንን በምን እንዳሸነፋቸው እንጃ... እጅ እየሰጡ ይገኛሉ:: ሰሞኑን በሰማነው ዜና ሁለት ቱባ ቱባ ባለሃብቶቻችን አንዱ በገመድ ሌላው በጥይት ራሳቸውን በማጥፋት ለኑሮ ምርኮኛ ሆነውለታል:: እንኳንስ ለራሳቸውና ለስንቱ ይተርፉሉ ያልናቸው «ልማታዊ» ባለሃብቶቻችንን ምን አንደነካብን እንጃ!? አንዳንዶች «እኛ ከሃብቱም ከልማቱም የሌለንበት ሰዎች ኑሮው ራሱ አዙሮ ካልጣለን እጅ አንሰጥም ብለን ስንታገል የተመካንባቸው፣ ለክፉ ቀን መሸሸጊያ ያልናቸው፣ ቀጣሪዎቻችንን ምን ክፉ ነገር አጋጠመብን!?» እያሉ ከመጠየቅም አልፈው ነገርየው በዚህ ከቀጠለ ሃገሪቱ የምስኪኖች ሃገር እንዳትሆን ስጋታቸውን ሲገልፁ ተሰምተዋል::

ወዳጄ እንደው ስለ ኑሮ ካነሳሁኝ አይቀር ብዬ የሳምንቱን አስደንጋጭ ዜና አወጋሁኝ እንጂ የዛሬ ወሬዬን እንኳን ለመጀመር ያሰብኩት በእንኳን ደስ አላችሁ ነበር? ምን ተገኘ ? እንደማይሉኝ ተስፋ አደርጋለሁኝ:: የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትራችን አቶ ታምራት ላይኔ ከእስር መፈታታቸውን አስመልክቶ እንኳን ደስ ያላችሁ ሳልል ባልፍ እርስዎስ አይታዘቡኝም?

እኒህ ሰው ከመፈታቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሙሉ በሙሉ መንግስትን የሚያገለግለው ኢቲቪ (ይቅርታ መንግስት ማለት ህዝብ ህዝብ ማለት መንግስት በሚለው ግንዘቤ ነው ከላይ ያለውን አረፍተ ነገር የተናገርኩት) አርፍተ ነገሩ ተስተከሎ ሲነበብ ሙሉ በሙሉ ህዝብን እና መንግስትን በታታሪነት የሚያገለግለው እና

የኢትዮጵያን ህዳሴ በማብሰር ላይ የሚገኘው (ልብ ብላችሁ እንደሆነ ቴሌቪዥናችን ቀድሞ «ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል» የሚል መፈክር በየ ሳሙና እና ቢራ ማስታወቂያው ጣልቃ ያስነብበን ነበር:: አሁን ደግሞ ትጋቱን ትቶ «የኢትዮጵያን ህዳሴ እናበስራለን» ማለት ጀምሯል:: ይህንን ልብ ያሉ አንዳንድ አስያየት ሰጪዎች «መትጋቱ ስለሚያደክም ማብሰሩ ይሻላል ብሎ ነው» ሲሉት ሌሎች ደግሞ አቲቪ ቢያንስ ለሶስት ወራት ያህል «ለኢትዮጵያ ህዳሴ ሲተጋ ቆይቷል አሁን በትጋቱ የኢትዮጵያን ህዳሴ እውን አድርጎታል እና ቀጣዩ ስራ የትጋቱን ውጤት ማብሰር ነው:: ሲሉ ተደምጠዋል:: ጎበዝ ለካስ እስከ አሁን በቅንፍ ውስጥ ነበርን እና እንደሚከተለው ከቅንፋችን ሹልክ ብለን ወጥተን ከእስር ሹልክ ብለው ስለወጡት የቀድሞ ጠቅላይ ሚንስትር ወሬ እንቀጥላለን)

አቶ ታምራት ላይኔ ሊለቀቁ አንድ ቀን ሲቀራቸው ኢቲቪ የዛሬ አስራ ሁለት አመት ሰውየው ሊታሰሩ ሲሉ ለድርጅታቸው ያላቸውን ታማኝነት ምንም እንደማይቀይረው እና ከማንኛውም ተቃዋሚ ጋር ለማበር ፍላጎት እንደሌላቸው ከድርጅቱ ከተሰናበቱ ግን ከፖለቲካ ተገልለው ነፃ ሆነው መኖርን እነደሚመርጡ የሰጡትን መግለጫ አሳይቶን ነበር:: ይህንን ቃለ ምልልስ በጥርጣሬ የተመለከተው አንድ ወዳጃችን «ዛሬ ይሄንን ቃለ ምልልስ ያስታወሱን ነገ ሲለቀቁ ቃላቸውን እንዳይረሱት ለማሳሰብ ነው:: እንደ አቶ ስዬ በየ ተቃዋሚው ስብሰባ ላይ እየተገኙ «አይዟችሁ አምባገነንነትን አብረን እንታገላለን!» አይነት መልዕክት ለማስተላለፍ እንዳይዳዱ ታስቦ ነው» አለን::

ለነገሩ እርሳቸውም በእስር ከከረሙባት አራት ሜትር በስምንት ሜትር ከሆነችው ኮሪደር አጥራቸው ሲወጡ በሃይማኖት ታጥረው ስለወጡ ከእንግዲህ የሃገራቸውን ነገር ለሚያመልኩት «የሰራዊት ጌታ» አደራ ይሰጡ እንደሆነ ነው እንጂ እርሳቸው ከትግል ጎራ ለመቀላቀል ወኔ ያላቸው አይመስሉም:: አንዳንድ ወዳጆቻችን የሰውየውን ሃይማኖተኛነት ቀድሞ ከነበራቸው «ኮሚኒስት» አቋም ጋር በማነፃፀር «ህዳሴስ ማለት እንደ እርሳቸው ነው!» በማለት ትችት አዘል አድናቆታቸውን ሰንዝረዋል:: ሰዉ ትችት ይችላልና አረ ጎበዝ! ትችት መተዳደሪያ አይሆንም የታደሉ ለህዳሴው ሲተጉ አንዳንዶች ጥሎባቸው በትችት እየተጉ ይገኛሉ እንዲህ አይነቶቹን ለመምከር እኛም መትጋት ግድ ይለናል::

ወዳጄ ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ላይ ከተሰሙት አስገራሚ ዜናዎች ውስጥ «ሲያልቅ አያምር ጆርጅ ቡሽ በጫማ ተሳቱ» የሚለው የአርባ አራት ቁጥሩ ጫማ ጉዳይ ነው:: የስልሳ ሰባት አመቱ ሽማግሌ ፕሬዚዳንት ከዕድሜያቸው ጋር ቅልጥፍናቸው አብሮ አልሸሻቸውም እንጂ እንደ ጋዜጠኛው ሃሳብ ቢሆን ኖሮ ፊታቸው ላይ የጫማውን ቁጥር ሊያትምባቸው ነበር::

ይህ በጆርጅ ቡሽ ላይ ጫማውን የወረወረው ጋዜጠኛ ከበርካታ ሰዎች የአድናቆት ቃላት እየጎረፉለት ነው:: ከዛም አልፎ ተርፎ በሺህ የሚቆጠሩ ጠበቆች እንቁምልህ እያሉት ይገኛሉ ከሁሉ ከሁሉ የሚገርመው ግን አንድ ግብፃዊ ባለ ሃብት የሆኑ ትልቅ ሰው በጋዜጠኝነት ትምህርቷን እየተከታተለች ያለችን የሃያ አመት ኮረዳ ልጃቸውን ልቡ ከፈቀዳት ከነ ሙሉ ጎጆ መውጫቸው ሊያበረክቱለት በወንድሙ በኩል ጥያቄ ማቅረባቸው ነው::

የትልቁ ሰው ኮረዳ ልጅ በበኩሏ «ደስታውን አልችለውም የዚህ ጀግና ሚስት ብሆን እና ኢራቅ ውስጥ ኑሮዬን ባደርገው ምንኛ ዕድለኛ ነኝ!?» ብላለች::

ታዲያ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በኛ ሃገር ያሉ ወንደ ላጤ ጋዜጠኞች እንዲህ አይነቱን ሲሳይ ለመቋደስ የኢራቁ ጋዜጠኛ በጆርጅ ቡሽ ላይ ያደረገውን በሃገራችን ባለስልጣናት ላይ ሊሞክሩት ይችላሉ:: ሲል አንድ ወዳጃችን ስጋቱን በገለፀልን ወቅት ሌላው ወዳጃችን መንግስት «ብልህ ሰው ከሌላው ይማራል» እንዲሉ ከዚህ በኋላ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ባለትዳር ያልሆኑ ጋዜጠኞች እንዳይገቡ የሚከለክል የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ማውጣት አለበት ብሎናል:: በርግጥ እንደ አንዳንድ ግለሰቦች ሃሜታ ከሆነ «የኛ ሃገር ጋዜጠኞች

የባለስልጣኖቻቸውን ጋዜጣዊ መግለጫ የሚሰሙት በወሬ በወሬ ነው ስለዚህ አይደለም ጫማ ጥያቄ ለመወርወር እንኳን አልታደሉም:: እንደውም አንዳንዶች ከኢራቁ ጋዜጠኛ ገጠመኝ በኋላ «ጫማው ቀርቶብኝ ጥያቄ በወረወርኩ - አለ የአትዮጵያ ጋዜጠኛ!» ሲሉ ተደምጠዋል::

ይህ ዕድል የገጠማቸው የኢትዮጵያ ሬድዮ እና ቴሌቪዝን ጋዜጠኞችም ጥያቄ ሲጠይቁ የፍቅር ጥያቄ እንደሚያቀርብ ወጣት ስለሚሽኮረመሙ እና ስለሚፈሩ የሃገራችን ባለስልጣናት ይሔ ችግር አያሰጋቸውም:: የሚሉም አልታጡም::

በመጨረሻም ለባለ ስልጣኖቻችን ስጋትን ያርቅልን ለጋዜጠኞቻችንም ድፍረትን ይስጥልን! ብዬ ልመርቅ እናንተም አሜን በሉኝና ለዛሬ ላብቃ::

አማን ያሰንብተን!

# ፍራቻ በነገሰበት የአፍሪካ ቀንድ

## /አህዬች፣ውሸታሞችና የጦር ወንጀለኞች/

**በአለማየሁ ገብረማርያም (ፕሮፌሰር)**

ሁለት አመታት የሚፈጥሩት ልዩነት! በታህሳስ 2006 ሶማሊያን ከ«ተጣመሩ ሽብርተኛ ሰይጣኖች» - አል-ቃኢዳ፣አል-ሻባብ እና «እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት» - ለመታደግ መለስ ዜናዊ ወረራ ፈጸሙባት:: በጥር 2007 «በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሶማሊያን ለቀን እንወጣለን» በማለት ለአለም አረጋገጡ:: ከአመት በኋላ በፖርላማው የሚገኙ የተወሰኑ ተቃዋሚዎች ወረራውን በመቃወማቸው ከዚያ ከታማኝ የሽክም እንስሳ (አህያ) ጋር አመሳስላቸው፤«ሁለት ትላልቅ አይኖች አሉት ግና ሩቅ መመልከት ይሳነዋል፤ትላልቅ ጆሮዎችም አሉት ሆኖም አይሰማበትም::» በማለት አቶ መለስ የተለመደው ዘለፋ ሰነዘሩ:: በዚህ ባሳለፍነው መስከረም፤ በሶማሊያ የነበሩ «ጂሃዲስቶችን» ማስወገድ እና በኢትዮጵያ ላይ የጋረጡትን አደጋ ማኮላሸት ተቀዳሚ አላማው በማድረግ ሶማሊያ የገባው ሰራዊታቸው አላማውን ሙሉ በሙሉ እንዳሳካ በድል አድራጊነት ስሜት አወጁ - አቶ መለስ:: ከጥቂት ቀናት በፊት ሶማሊያን ለቀው ለመውጣት እየተዘገጃጁ በነበረበት ወቅት በአፍሪካ ህብረት በኩል ወታደራዊ ድጋፍ እንደተጠየቁ ለፖርላማቸው ገለጹ፤ «የአፍሪካ ህብረት፣ዩጋንዳ እና ብሩንዲ የወታደሮቻቸው ደህንነት ተጠብቆ /ከሶማሊያ/ ለመውጣት እንዲቻላቸው እኛ ወደኋላ ቀርተን ከለላ እንድንሰጣቸው ጠይቀውናል::» በማለትም አስረግጠው ተናገሩ:: ነገር ግን የዩጋንዳ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የሆኑት ኦኬሎ ኦሪም የአቶ መለስ አነጋገር ሙልጭ ያለ ፈጠራ እንደሆነ በሚከተለው አኳሁን ገለጹ፤ «ፈፅሞ ሀሰት ነው ከተናገርናቸው ነገሮች ጋር በጠቅላላ የሚፃረር ነው:: የእኛ አቋም ሆኖ የቆየው ኢትዮጵያ

ከሶማሊያ ለቃ የምትወጣ ከሆነ በእዚያ የሚገኙ ወታደሮቻችንን ቁጥር እንደምንጨምር ነው:: አስፈላጊ ሆኖ ከተገኝ ዩጋንዳ ተጨማሪ ብርጌድ ለመላክ ዝግጁ ነች::»
በማለት ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተናገሩ::

«So Much to Fear: War Crimes and the Devastation of Somalia» **በሚል ርእስ ሁዩማን ራይትስ ዎች የተሰኘው የሰብአዊ መብቶች ዘብ ባወጣው 104 ገፅ ሪፖርት ፤ የመለስ ዜናዊ ስርአት እና በሶማሊያ የሚገኙ ወታደራዊ ሃይሎቹን፣ የሶማሊያ ጊዜያዊ ፌዴራል መንግስትን እና የሶማሊያ ሰርጐ ገብ ተዋጊዎችን «መጠነ ሰፊ እና ከፍተኛ የጦርነት ህጎችን በመጣስ፣ተደጋጋሚ ጅምላ ጥቃቶች፣ግድያዎች፣ሰብአዊ ፍጡርን እንደ ጋሻ መጠቀም እና ዘረፋን ያካተተ ድርጊት ፈጽመዋል» ሲል በጦር ወንጀሎች ክስ አቅርቦባቸዋል::**

## *የተጠቀሱት የጦር ወንጀሎችና ማስረጃዎቻቸው*

**ዘቡ በሶማሊየ ስለተፈፀሙ የጦር ወንጀሎች ያጠናቀረው ማስረጃ አስደማሚ ነው፤ ከጥር 2007 (መለስ ዜናዊ ወረራ ከተጀመረበት) አንስቶ ከሞቃዲሾ ብቻ 870ሺ የሚሆኑ ወይም 2/3ኛውን የከተማዋን የህዝብ ቁጥር ይይዛሉ የተባሉ ሲቪሎች በፍርሀት ከተማዋን ሸሽተዋል:: በመላ ደቡብ-ማዕከላዊ ሶማሊያ፤1.1 ሚሊዩን ሶማሊያዊያን ከመኖሪያዎቻቸው ተፈናቅለዋል::**

**(ወረራውን ተከትሎ) ሰርጐ ገብ ተዋጊዎች ወዲያው የደፈጣ ጥቃት ስንዘራ ታክቲኮችን መጠቀም ጀመሩ:: . . . የኢትዮጵያ እና የሶማሊያ ጊዜያዊ ፌደራል መንግስት ሰራዊቶች ለሚሰነዘርባቸው ጥቃቶች በሚወስዱት አፀፋዊ ምላሽ ዕለታዊ ዑደቱ ተመሳሳይ የሆነና በሞቃዲሾ በየቀኑ የሚከሰት የህይወት አንድ አካል ሆነ:: ከመጋቢት 3/2007 አንስቶ በሞቃዲሾ የሚገኘው የኢትዮጵየ መከላከያ ሰራዊት በየእለቱ እና በጅምላ የሞቃዲሾ ህዝብ በብዛት የሚኖርባቸውን የመኖሪያ አካባቢዎች በቦምብ አጋይቷቸዋል:: በሞቃዲሾ በአንድ ጊዜ ብዙ ሮኬቶችን ከሚያስወነጭፈው «ቢ.ኤም.21» የሚተኮሱ «ካትዩሻ» ሮኬቶችን በቋሚነት በጥቅም ላይ አውሏል::**

**ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላት ቤሌትዌይን ከተማ ውስጥ በተካሄዱ ውጊያዎች የኢትዮጵያ ሃይሎች ተመሳሳይ ጅምላ የቦምብ ጥቃት ፈፅመዋል:: ከሃምሌ 2008 ጀምሮ የኢትዮጵያ ሰራዊቶች በወሰዱት የሶስት ቀናት አፀፋዊ ምላሽ ሰፋፊ የከተማዋ ምዕራባዊ አውራጃዎችን በጅምላ የቦምብ ጥቃት ተፈፅሞባቸዋል:: ሰብአዊ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች በቦምብ ጥቃቱ እና ተያያዥነት በነበራቸው ውጊያዎች፤75 በመቶ የሚሆነው ወይም 75ሺ የከተማዋ ህዝብ ከቤት ንብረቱ ተፈናቅሏል::**

**የኢትዮጵያ ሃይሎች ለሰርጐ ገቦቹ የደፈጣ ጥቃት እና ለሌሎች ጥቃቶች ህዝብ በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ላይ በተለይ በሞቃዲሾ፣በባይዶዋ እና ከሞቃዲሾ-**

አፍጉዬ መተላለፊያ መንገድ ላይ በሚገኙ ንጹሀን ላይ በመተኮስ አፀፋዊ ምላሽ እንደሰጡ የ2008 የሰብአዊ መብት ተቋሙ ሪፖርት ጨምሮ ያትታል፡፡

በ2008 በሶማሊያ ውስጥ ያለው የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊ እርዳታ ልገሳ ሁኔታዎች፤ማስታረቅ አዳጋች በሆነ መልኩ እጅግ ተባብሷል . . . የረዣዥም ሁለት አመታት የተባባሰ ደም-መፋሰስ እና ውድመት የአገሪቱን ህዝብ ያንኮታኮተ እና ዋና ከተማዋን ሞቃዲሾን ያፈራረሰ ነው፡፡

የኢትዮጵያ፣ የጊዜያዊ መንግስቱ እና የሰርጎ ገቦቹ ሃይሎች በሚያካሂዱት የከተማ ቶክስ ልውውጦች፣እና በሙቶ ሺህዎች ለሚቆጠሩ በከተማዋ መግቢያ መውጫያ ለጠፋቸው ሲቪሎች ህይወት ግድ ሳይላቸው እርስ በእርስ በሚያደርጉት መደቋቆስ፤ያለፉት ሁለት አመታት በሞቃዲሾ ውስጥ ያለው ዕለታዊ ህይወት አስፈሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በአብዛኛው የሚሰነዘሩት የፈንጂ ጥቃቶቹ በጅምላ ነው፡፡ ሰርጎ ገቦቹ የሚተኩሷቸው የሞርታር እና ሌሎች ጥይቶች የሚወነጨፉት ህዝብ በብዛት ከሚገኙባቸው አጉራባች አካባቢዎች ነው፡፡ የኢትዮጵያ እና የጊዜያዊ መንግስቱ ሃይሎች የሚሰነዝሯቸው አፀፋዊ ምላሾች የከተማዋ ነዋሪዎችን መኖሪያ ቤቶቻቸውን እና አካባቢዎቻቸውን አውድመዋል ... የጊዜያዊ መንግስቱ ሃይሎች አብዛኛውን ጊዜ በኢትዮጵያ ሰራዊቶች ትዕዛዝ ወይም አጋዥነት ጥቃቶችን፣አስገድዶ ደፈራዎችን፣ ግድያዎችን እና ቤት ለቤት በተደረጉ የፍተሻ ዘመቻዎች ሲቪሎችን ዘርፈዋል ... በሶማሊያ ውስጥ ያሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች ዲሲፕሊን በጎደለው ፤ሃይል በተቀላቀለበት ወንጀለኝነት በየጊዜው ተጠያቂነታቸው እስኪጨምር ድረስ የዘቀጠበት ሁኔታ አለ፡፡ ከ2007 መገባደጃ ጀምሮ፤የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወታደሮች ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች እና የጦርነት ህጎች ጥስቶችን በሱማሊያ ሲቪሎች ላይ ፈፅመዋል ተብለው በተደጋጋሚ ተወንጅለዋል፡፡

የሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት በወጣበት ተመሳሳይ እለት የስርአቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሪፖርቱን «የጥናት ዘዴ» እና «እያንዳንዱን ግኝቶቹን» የሚተች የተደናገረ እና ዝብርቅርቅ ያለ ምላሽ በፍጥነት ሰጥቷል፡፡ ሪፖርቱ የተመሰረተው «በተጣረሰ የጥናት ዘዴ፣መሰረት በሌላቸው ውንጀላዎች፣ስማቸው ከማይታወቅ መረጃ ሰጭዎች ጋር በተደረጉ የሁለተኛ ወገን መረጃዎች እና በሰሚ ሰሚ» በመሆኑ በሚል ምክንያት የዘቡን ሪፖርት ተቀባይነት የለውም በማለት እንደተለመደው በሙሉ ውድቅ አድርጎታል ፡፡ በተጨማሪ መግለጫው፤በሶማሊያ በውጊያ ላይ ለሚገኙት አንጃዎች ሰላም ማምጣት የኢትዮጵያ ግልፅ ግብ እንደሆነ እና አሁን ሶማሊያን የሚለቀው በአገሪቱ ሰላም ቀቢፀ ተስፋ በመሆኑ እንደሆነ ያውጃል፤ «በሶማሊያ ህዝቦች መካከል ላሉት ችግሮች ሰላማዊ መፍትሄ ለመስጠት ኢትዮጵያ ያለማቋረጥ ጥረት አድርጋለች፤ ከ1992 ጀምሮ ተከታታይ የሰላም ኮንፈረንሶችን አካሂዳለች ... ከሶማሊያ መንግስት ጥሪ በቀረበ ጊዜ ኢትዮጵያ የሚቻላት ከሆነ ማንኛውንም ድጋፍ መስጠትን የምትቀበለው ነው፡፡ ዘላቂ የሰላም ሂደት ለመፍጠር ስላልተቻለ ... በዚህ አመት መገባደጃ ኢትዮጵያ

ሃይሎቿን ማስወጣት አለባት የሚል ስሜት ተሰምቷታል።» ይላል። ለሪፖርቱ የተሰጠው ምላሽ

የሚገርመው በመንግስት የተሰጠው መግለጫ ከፍተኛ የጦር ወንጀሎች ጥሰቶች ተፈፅሟል የሚሉ ውንጀላዎችን ሳይዳስስ በዝምታ የሚያልፈው ሲሆን የሶማሊያ ሲቪሎች መገደልን አስመልክቶ ምንም አይነት ተጠያቂነት እንደሌለበትም ይክዳል። ይባስ ብሎ ከ2006 ጀምሮ በተከሰቱ አብዛኞቹ የሶማሊያ ግጭቶች፤የሞቱ ሲቪሎች በትክክል «ሲቪሎች» አልነበሩም ይልቁንስ «ሞተዋል የተባሉት አብዛኞቹ ተዋጊዎች የነበሩ ናቸው . . . ።» የሚል አስቂኝ መከራከሪያም ያቀርባል። በ«ኢትዮጵያ» ሃይሎች በተካሄዱ የውጊያ ዘመቻዎች የደረሰ ምንም የተለየ ያልታሰበ የሲቪሎች ሞት የለም ብሎ ይክዳል። የጉሮሮ የመቁረጥና ሰውነት መተልተልን የመሳሰሉ ጭካኔ የተሞላባቸው እርምጃዎች በጦርነት ዘመቻዎቻቸው አለመከሰታቸውን በቁጣ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፤ያን መሰል ጋኔናዊ እርምጃዎችንም በጠቅላላ በአል-ሻባብ ተወጊዎች ላይ ያላክካል። «የኢትዮጵያ» ሰራዊት እንደዚያ አይነት ጭፍጨፋዎችን አይፈፅሙም ምክንያቱም «እንደ ሞቃዲሾ ላሉ የጦርነት ቀጠናዎች ኢትዮጵያ በቂ ስልጠና ያላገኙ ወታደሮችን አታዘምትም . . .ስለ ሰብአዊ መብቶች እና የጦርነት ህጎች በወታደራዊ ስልጠና ሰጭ ተቋማቶቻችን ውስጥ የሚሰጥ ማዕከላዊ የትምህርት አካል ነው ... »

ስርአቱ ዘቡ የተጠቀመበትን የጥናት ዘዴ መተቸቱ ሆን ብሎ እውነታዎችን አውቆ ያላወቀ ለመምሰል እና ከከፍተኛ የጦር ወንጀሎች ውንጀላዎች ሞኛ ሞኝ የማምለጫ ሙከራ ማድረጉን የሚያመላክት ነው። በማንኛውም ሁሉን-አስማሚ መመዘኛ ዘቡ የተጠቀመበት «የጥናት ዘዴ» ያልተለመደ እና የተሳሳተ ምንም አይነት ነገር የለም። «So Much to Fear» በሚለው ሪፖርት ውስጥ፤ዘቡ የተጠቀመው በሁሉም በተጠረጠሩ የጦር ወንጀሎች/ኢሰብአዊ ወንጀሎች ጉዳዬች ላይ የተጠቀመባቸውን የምርመራ ቴክኒኮችንና ዜዴዎችን ነው። በሶማሊያ ምርመራውም ምንም ጥያቄ የሚያጭሩ ቴክኒኮችን አልተጠቀመም። እንደውም በተጨባጭ የዘቡ መሰረታዊ የምርመራ ቴክኒኮች በተራ የወንጀል ምርመራ ወቅት በጥቅም ላይ ከሚውሉት ማለትም ማስረጃዎችን ከተጠቂዎች፣ከአይን እማኞች፣ከማናቸውም በምስጢር ከሚጠበቁ ጠቋሚዎች፣ከባለስልጣናት፣ጠበብቶች እና ሌሎች ወሳኝ እና ከተያዘው ጭብጥ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እውነታዎችን ማግኘት ከሚያስችሉ ምንጮች ጋር ይህን ያህል የሚለዩ አይደሉም። በሶማሊያ ሪፖርቱ ዘቡ «በሪፖርት የተካተቱትን ጥሰቶች በተመለከተ ከ80 የሚበልጡ የአይን ምስክሮችንና ተጠቂዎችን ቃለ መጠይቅ አድርጓቸዋል።» «ደርዘን ተኝታኞችን፣የሶማሊያ ሲቪል ማህበራት ተማጋቾችን፣ሰብአዊ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ሰራተኞችን፣ዲፕሎማቶችን የህክምና አገልግሎት ሰጪ አባላትን እና የተወሰኑት በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱ ክስተቶችን የተመለከቱ ጋዜጠኞችን» የዘቡ መርማሪዎች ቃለ መጠይቅ አድርገዋቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ጠ/ሚ ኑር ሃሰን ሁሴንን ጨምሮ ከሌሎች የጊዜያዊ ፌዴራል መንግስቱ ባለስልጣናት

ጋር፣ሼክ ሸሪፍ አህመድን እና ሸሪፍ ሃሰን ሼይክ አደንን ጨምሮ ከ«ጥምረት ለሶማሊያ ዳግም ነፃነት» ባለስልጣናት ጋር፣የተባበሩት መንግስታት ድርጅት(ተመድ) ሴክሬተሪ ጄኔራል ልዩ ተወካይ አህመድ ኦላድ አብደላህን ጨምሮ ከሌሎች የተ.መ.ድ ባለስልጣናት ጋር እና በናይሮቢ የአውሮፓ ከሚሽን ባለስልጣናት ጋር ዘቡ ተገናኝቷል። ከእነዚህ የማስረጀ አሰባሰብ ቴክኒኮች በላይ ዘቡ ከሰማይ እና ከምድር የተነሱ ምስሎችን የመያዝ ልምድ አካብቷል።

የጉዳዩ እውነታ ዘቡ አግባብነት ያላቸው ጠንካራ መሰረት ያላቸውን የወንጀል ምርመራ ቴክኒኮችን እና ስነ ስርዓት የተከተለ መሆኑ ነው። ለራስ ጥቅም ሲባል መንግስት ያወጣውን ትችት፤እውነትነት ባላቸው ጥያቄዎች መዳሰስ ይቻላል። በአለም እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል አይነት በጦር ወንጀሎች/ኢሰብአዊ ወንጀሎች ዙሪያ የምርመራ ተመኩሮ ያላቸው ድርጅቶች በጣም ጥቂት ናቸው። መጀመሪያ፤ባለፈው አስር አመት ብቻ ሩዋንዳን ፣ ላይቤሪያን፣ ዩጋንዳን ፣ ሱዳንን ፣ ኢራቅን ፣ የቀድሞ ዩጉዝላቪያን ፣ ምስራቅ ቲሞርን ፣ ዚምባቡዌን ፣ቼቺኒያን፣ ቻይናን፣ ኢራንን፣ ሰሜን ኮሪያን ፣ ኩባን፣ ስሪላንካንና ሌሎች በርካታ አገሮችን ጨምሮ በሁሉም የአለማችን ጠርዞች የተፈፀሙ የጦር ወንጀሎችን እና ከፍተኛ የስብአዊ መብት ጥሰቶችን ዘቡ በስፋት እና በጥልቀት መርምሮ ለታሪክ ያስቀመጣቸው ሰነዶች ምስክሮች ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ፤ዘቡ በአድሎ የሚሰራ ባለመሆኑ፣በገለልተኛ ነቱና ህልውናውን በማስጠበቅ የፀና ዝና አለው። በአለም ውስጥ በአብዛኞቹ ዲሞክራሲያዊ አገሮች የዘቡ ሪፖርቶች ተቀባይነት ከማግኘታቸውም በላይ በመንግስት ከፍተኛ የህግ አውጭ፣ህግ አስፈፃሚና ህግ ተርጓሚ አካላት ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ የሚውሉ ናቸው። ሶስተኛ፤በታላቅ ቁጣ ዘቡን የሚቃወሙ አገሮች መጠነ ሰፊ እና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሪከርድ የተያዘባቸው ናቸው። ለምሳሌ ቻይና ዘቡ ያቀረበባትን ሪፖርት «ከአየር የተገኘ» በማለት ተችታዋለች። በሱዳን የዳርፉርን ግድያዎች ያስተባበሩ የሱዳን ባለስልጣናት ቅጣት ሊጣልባቸው ይገባል የሚል ጥሪ በማቅረቡ የአልበሽር መንግስት በዘቡ ላይ ከፍተኛ ውግዘት አቅርቧል። ባለፈው ወር ዘቡ ያወጣውን አንድ ሪፖርት ሮበርት ሙጋቤ «ቆሻሻ» በማለት አጣጥለውታል። ከጥቂት ወራት የዘቡን ተወካይ ከአገራቸው ያባረሩት ሁጎ ቻቬዝ ምክንያት ያደረጉትም « ዘቡ የሰብአዊ መብት ተከላይነት ጭምብል በመልበስ፤በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ የሚደጎም ነው። አዲስ የኢኮኖሚ ሞዴል የሚገነቡ አገሮችን ከሚያጠቃ ፖሊሲ ጋር ራሱን የወገነ ነው።» ሲሉ ነበር ትችት የሰነዘሩበት።

እነዚህ ግልፅ የምርመራ አካሄድ ስርአቶች ቢኖሩም፣ዘቡ በመለስ ስርአት ከተወገዘባቸው ቀዳሚና ተጠቃሽ ምክንያቶች አንዱ ለዘቡ ማስረጃዎችን የሰጡ ተጠቂዎችን ስም እና አድራሻ ለአገዛዙ ባለስልጣናት አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑ ነው፤ «ምንም እንኳን በሞቃዲሾ የሚገኙ የተወሰኑ ሰዎችን በስልክ ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸዋለሁ ቢልም መረጃ የሰጡትን ሰዎች ስም እና አድራሻዎቻቸውን

አልሰጠም፡፡» የአገዛዙ ባለስልጣናት የተጠቂዎችን ስም እና አድራሻ አገኙ ማለት ደግሞ ቀጣዩ እርምጃ ምን ሊሆን እንደሚችል ማንም እየሰቀጠጠውም ቢሆን የሚገምተው ነው!

ከዚህ በተጨማሪ ይፋ በተደረገው ሪፖርት ከላይኛው ጋር እኩል እንቆቅልሽ የሚሆነው ስርአቱ አዝኖ እርግጠኛ ሆኖ እንዲህ ማለቱ ነው፤ «ግልፅ መሆን ያለበት ዘቡ በሞቃዲሾ ውስጥ በአልሻበብ እና በሌሎች ፅንፈኛ ሃይሎች የተፈፀሙ ጥፋቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማጋለጥ ሙከራ ማድረጉ በኢትዮጵያ ላይ የተሰነዘሩ በማስረጃ ያልተደገፉ ውንጀላዎችን ታማኝ የሚያደርግ አይደለም፡፡» በቀላሉ ሲቀመጥ ዘቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ አል-ሸበብ እና ሌሎች ሰርጐ ገቦች እውነታውን መንገሩ አሁን ስለ «ኢትዮጵያ ሃይሎች» እውነታውን እየተናገረ ነው ማለት አይደለም፡፡ አንጊ በሆነ መልኩ የስርአቱ አመክንዮ በጣም የተለየ ድምዳሜን መከተል የሚያስገድድ ነው፤በ«ኢትዮጵያ ሃይሎች» ላይ የተሰነዘረው የጦር ወንጀሎች/ኢሰብአዊ ወንጀሎች ማስረጃዎች እና ክሶች ውሸት ከሆኑ /ሌሎች ተለዋዋጭ ነገሮች እንደሁኔታው እንዲለዋወጡ ሆነው እንዳሉ/ ዘቡ በአል-ሻባብ እና በሌሎች ሰርጐ ገብ ቡድኖች ላይ ያቀረባቸው ውንጀላዎች እና ማስረጃዎች በተመሳሳይ ሃሰት መሆን አለባቸው፡፡ በሌላ ቃላት ሲቀመጥ ዘቡ አል-ሻባብ ሲቪሎችን «ሰብአዊ ጋሻዎች» አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል፣ ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች በጅምላ ሞርታሮችን እና በርቀት መቆጣጠሪያ የሚፈነዱ ፈንጂዎችን በጥቅም ላይ አውሏል፣የተነጣጠሩ ግድያዎችን በመፈፀም ተሰማርቷል፣አስገድዶ መልምሏል እንዲሁም ህፃን ወታደሮችን ተጠቅሟል እና ወዘተ የሚሉ የዘቡ ውንጀላዎች የግድ ውሸት መሆን አለባቸው፡፡ አል-ሻባብ የፈፀማቸውን ጭፍጨፋዎች በተሸፋፈነ እውነታ መናገር እና የ«ኢትዮጵያ» ሃይሎች የፈፀሟቸውን ጭፍጨፋዎችን አስመልክቶ የማይታረቁ ውሸቶችን መፍጠር ለዘቡ ትርጉም የሚሰጠው አመክንዮ አይደለም፡፡ ልክ ቆየት ያለው አባባል እንደሚያስቀምጠው ለሴቷ ዳክዬ መልካም የሆነ ለወንዱም መልካም ነው!

## የጦር ወንጀሎች

በአለም አቀፍ ህግ «የጦር ወንጀሎች» ሰፊ የወንጀሎች ምድብ ያለው ነው፡፡ ቢያንስ አራት ራሳቸውን በቻሉ ምድቦች ይቀመጣሉ፤1ኛ በነሃሴ 12ቱ 1949 «ጄኔቫ ኮንቬንሽኖች» የተካተቱ ድንጋጌዎችን በከፍተኛ ደረጃ መተላለፍ 2ኛ «የጦርነት ህጐችን እና ልማዶችን» መጣስ 3ኛ ዘር ማጥፋት እና 4ኛ በሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች መፈፀም (ግድያ፣ ግርፋት፣አስገድዶ ደፈራ ወዘተ ጨምሮ በሲቪሎች ላይ ያነጣጠሩ መነጠ ሰፊ ጭፈጨፋዎች)፡፡ በ«አለም አቀፍ የወንጀለኛ ችሎት ለቀድሞዋ ዩጐዝላቪያ»፣«አለም አቀፍ የወንጀለኛ ችሎት ለሩዋንዳ» እና በ«ልዩ ፍርድ ቤት ለሴራሊዩን» እንደተከሰተው የጦር ወንጀሎችን የፈፀሙትን ወደ ፍትህ መድረክ ማምጣት ብዙ ቴክኒካዊ፣ህጋዊ እና የስነስርአት ጉዳዮችን የሚያስነሱ ናቸው፡፡

ከጉዳዮቹ መካከል የተወሰኑት ክሱን የት ማቅረብ እንደሚቻል፣አዲስ ለዚሁ አላማ ተብሎ የሚቋቋም ችሎት ወይስ አለም አቀፍ የወንጀል ችሎትን መጠቀም የሚሉ ይገኙበታል። ሌሎቹ ግብአቶችን የሚመለከቱ ናቸው። ለምሳሌ ተጠርጣሪዎችን መለየት፣ በቁጥጥር ስር ማዋል፣ማሰርና ችሎቱ ወደ ሚውልበት ቦታ ማጓጓዝ እንዴት እንደሚቻል። አሁንም የቀሩ ሌሎች ጉዳዩች አሉ። የሚያተኩሩትም በክስ ሂደት ስትራቴጂ ላይ ነው። ለምሳሌ ማናቸውም በጭፍጨፋው ተሳትፈዋል የተባሉ ሰዎች ናቸው ወይስ ከፍተኛ ተጠያቂነት ያለባቸው ናቸው መከሰስ ያለባቸው፤የጦር ወንጀሎች እንዲፈፀሙ ትዕዛዝ ያስተላለፉ አመራሮች ወይንስ ጥፋቱን በቀጥታ የፈፀሙት፤እና ከባድ ያልሆኑ ወንጀሎችን የፈፀሙት እንዴት መለየት እንደሚቻል የሚጠቀሱ የሂደቱ ጥያቄዎች ናቸው። ለምሳሌ አብዛኞቹ እነዚህ ጉዳዮች በሩዋንዳው የዘር ማጥፋት ወንጀል ጉዳይን ለመመልከት በተሰየመው ችሎት ላይ የተነሱ ናቸው። ከ100 ሺ የሚበልጡ ተጠርጣሪ የጦር ወንጀለኞች ሩዋንዳዊያንን በአንድነት መክሰስ የሚቻል እንዳልሆነ የታየ ነው። ለዚህም ሲባል የሩዋንዳው የክስ ሂደት ያተኮረው የዘር ማጥፋቱን ባቀናበሩት እና በመሩት ላይ ነበር። ይህም ማለት በስልጣን ላይ ሆነው የሚደረገውን እውቅና የሰጡ፣የዘር ማጥፋት ወንጀሎች እንደፈፀሙ የረዱ፣ታዋቂ ገዳዬችን እና ሌሎችን ያካተተ ነበር።

## *ያልታቀደበት አደጋ እና «ስውር ውጊያ»*

በዘቡ ውንጀላዎች በቀዳሚነት በግላጭ የሚታየው ጉዳይ፤ሁለት ማዕከላዊ ጭብጦች ይገኛሉ፤1ኛ ላልታቀደበት ጉዳት የወንጀል ተጠያቂነት እና 2ኛ ለ«ስውር ውጊያ» ህጋዊ ምላሾች ናቸው። በአጠቃላይ «ያልታቀደበት አደጋ» ታስቦበት ያልተደረገ ወይም በአጋጣሚ በሲቪሎች ላይ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ወይም አደጋ ማድረስን የሚያጠቃልል ነው። አቅዶ ሲቪሎችን የጦር ጥቃት ኢላማ ማድረግ የጦር ወንጀል ነው። ለጦር ወንጀሎች ያልታቀደበት ጉዳትን ለማመዛዘን ተብሎ የ1949ኙ «ጄኔቫ ኮንቬንሽኖች» አካል በሆነው «ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች አንድና ሁለት» ውስጥ እንዴት ወታደራዊ ኢላማን ከሲቪሉ መለየት እንደሚቻል፣ስለ አስገዳጅነት፣ ስለ ተመጣጣኝነት፣ ስለ ሰብአዊነት የሚናገሩ መርሆች ይገኛሉ።

እነዚህ ፕሮቶኮሎች የጦር ጥቃት ከመፈፀሙ አስቀድሞ ወታደራዊ ቁሶች ከሲቪሎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው የሚል ቅድመ ሁኔታ አስፍረዋል። ለምሳሌ «ተመጣጣኝነት» የሚለው መርህ ተለይቶ በሚታወቅ ወታደራዊ ኢላማ ላይ ጥቃት መሰንዘር የማይቻልበትን ሁኔታ እንዲህ ያስቀምጠዋል፦ የሚሰነዘረው ጥቃት «ያልታሰበ የሲቪል ህይወት ይቀጥፋል ወይም ይጎዳል ተብሎ ከተገመተው ተጨባጭ እና ቀጥተኛ ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ከመጠን ያለፈ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ወታደራዊ ጥቃቶች መሰንዘር የተፈቀደ አይደለም።» ሃላፊነት የሚሰማው አዛዥ ኢላማው ወታደራዊ ኢላማ መሆኑን አስቀድሞ ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ሲሆን ከዚያም ኢላማ የተደረገው

ከሚያደርሰው ያልታሰበ አደጋ ከሚወድመው ንብረት የሚያስገኘውን ወታደራዊ ጥቅም አመዛዝኖ መወሰን ይችላል፡፡ «ስውር ውጊያ» አብዛኛውን ጊዜ በሲቪሉ ህዝብ ውስጥ በመሸሸግ ጥቃት የሚሰነዝሩ ሰርጎ ገቦች የሚጠቀሙበት የውጊያ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በከተማዎች የሚንቀሳቀሱ ሰርጎ ገቦች ሲቪሉን የውጊያው አውድማ ማዕከል የሚያደርጉ ታክቲኮችን በመጠቀም በይበልጥ አመቺ የውጊያ አውድማ ለማግኘት ሙከራ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ሊውጡት ከሚያዳግታቸው የተደራጀ ወታደራዊ ሃይል ከሚደርስባቸው ጥቃት አምልጠው ለረዥም ጊዜ ቆይታ ለማድረግም የሚጠቀሙበት ነው፡፡ «ስውር ውጊያ» ወታደራዊ እና ሲቪል ኢላማዎችን በጦር አውድማ የሚያጣምር በመሆኑ ከፍተኛ ሲቪል አደጋዎችን የማድረስ አጋጣሚን በእጅጉ ያሰፋል እንዲሁም ለተደራጀ ጦር ሰራዊት የተለየ ችግር ይደቅናል፡፡

በመጭዎቹ የሶማሊያ ጦር ወንጀሎች የክስ ሂደት ሊከሰቱ ከሚችሉ ህጋዊ ጭብጦች መካከል አንዱ ቁልፍ ጭብጥ የ«ኢትዮጵያ» ሃይሎች አዛዦች፣በህዝቡ ውስጥ የተጠለሉ ሰርጎ ገቦች ላይ ጥቃት በሚሰነዝሩበት ወይም አፀፋዊ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ከተጨበጠውና ከተጠበቀው አጠቃላይ ወታደራዊ ጥቅም ጋር በተያያዘ ድርጊታቸው ከመጠን ያለፈ የሞት ወይም የማቁሰል አደጋ በሲቪሉ ማድረስ አለማድረሱን ያውቁት ነበር ወይ? ወይስ የግዴታ ማወቅ ነበረባቸው፣ነገር ግን አስፈላጊ ማስታረቂያ እርምጃዎችን ሳይወስዱ ቀርተዋል፣ የሚለው ነው፡፡ ሌላው የወንጀለኝነት ተጠያቂነት ጉዳይ በ1949ኙ «ጄኔቫ ኮንቬንሽኖች» አካል በሆነው «ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች አንድ እና ሁለት»-1997- ውስጥ የተካተተው የጦር አዛዥነት ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችለውን የሚዳስስ ነው፡፡ የኮንቬንስኖቹን ወይም የፕሮቶኮሉን ድንጋጌዎች መተላለፍ የፈፀመው ከበታች ያለ አዛዥ መሆኑ የበላዬቹን ከተጠያቂነት ነፃ የሚያደርጋቸው ነው ማለት አይደለም፡፡ አዛዦቹ መተላለፉን ያውቁ የነበረ ከሆነ ወይም በወቅቱ በነበሩበት ሁኔታ ውስጥ እያሉ ውሳኔ እንዲወስዱ የሚያስችላቸው መረጃ የነበራቸው ከነበረ፣የበታቹ ጥፋቱን እየፈፀመ መሆኑ ወይም ሊፈፅመው እንደሆነ እያወቁ ባላቸው ስልጣን ተጠቅመው ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ወስደው አደጋውን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ ከተሳናቸው ከተጠያቂነት አያመልጡም፡፡ በዚህ ድንጋጌ የጦር አዛዥነት ሃላፊነት ተጠያቂነት «የኢትዮጵያ ወታደራዊ አዛዦች በጦርነት አውድማ ከወሰዱት ወይም መውሰድ የነበረባቸውን እርምጃዎች ካለመውሰዳቸውም በላይ ሊሄድ የሚችል ነው፡፡ እርግጥ ነው በመጭዎቹ የጦር ወንጀሎች የፍርድ ሂደቶች የሚነሱ ብዙ ህጋዊ ጉዳዬች ይኖራሉ፡፡

**/አለማየሁ ገብረማሪያም፣ በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ /ሳንበርናርዲኖ/ የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰርና መቀመጫውን ሎስአንጀለስ ባደረገ ተቋም ውስጥ የህግ ኮንሰልታንት ናቸው/**

# ከእንግዲህ ከህሊናዬ በስተቀር ሌላ ዳኛ የለኝም

**በታምራት ላይኔ**

በቀጠሮዬ መሰረት፣ ወደ ፍርድ ቤት ከመምጣቴ በፊት አንድ መላ-ምት (hypothesis) መሰረትኩኝ:: ሊሞከር የሚችል መላ-ምት (testable hypothesis) ነው:: መላ-ምቱ የሚከተለው ነው::

በአንድ በተወሰነ የዳኝነት ሂደት ውስጥ አጠቃላዩን የዳኝነቱን ባህርይ ፍትሀዊ ይሆናል ወይም አይሆንም ብሎ ከመገመት አልፎ እያንዳንዱን ተናጠል ብይን ምን ሊሆን እንደሚችል ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ፤ ሁለቱም ወይም አንዱ ወገን በእርግጠኝነት የሚገምቱት (accurately predictable) ከሆነ የዳኝነቱ ሂደት ፍትህ አልባ ነው ወይም ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ ነው ማለት ይቻላል፤ የሚል ነው::

በዚህ መላ-ምት መሰረት የዳኝነት ሂደት አጠቃላይ አዝማሚያው ወይም በመጨረሻ ሊደረስባቸው የሚቻሉ የተለያዩ የፍርድ ውሳኔ አማራጮች፣ ሊሆን ይችላል በሚባል መልካቸው ሊገመት ይችላል እንጂ፣ በየደረጃው የሚኖሩት የዳኞች ብይንና አቋም ኢ-ተአማኒ (unpredictable) ነው:: ተቃራኒዎቹ ወገኖች፣ ሁሉም ወይም አንዱ ወገን በየደረጃውና በየወቅቱ ዳኞች ሊሰጡ የሚችሉትን ብይን በእርግጠኝነት ማወቅ ከቻሉ ግን ትክክለኛው የዳኝነት ሂደት በመሰረቱ የተፋለሰ መሆኑንና ለአንዱ ወይም ለሌላው ወገን ሊያደላ የሚችልበት ክፍተት መኖሩን ያመለክታል::

ይህን መላ-ምት ለማረጋገጥ የሞከርኩት በሁለት መንገዶች ሲሆን፣ አንደኛው Quantum Theory በሚባለው ሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳብ ላይ የተመሰረተውን እርግጠኛ ያለመሆን መርሆ (uncertainty principle) በመጠቀም መመዘን ነው:: ሁለተኛውና በዚሁ መርሆ መለኪያነት የሞከርኩት እስከአሁን ያለኝን የፍርድ ቤቱን ሂደት እንደተጨባጭ ማስረጃ (empirical evidence) በመጠቀም ነው::

እርግጠኛ ያለመሆን መርሆ (uncertainty principle) በሚያስተምረው መሰረት ማንኛውም ነገር የወደፊት ምንነቱንና ባህርዩን በሚመለከት አንድም በአጠቃላይ መለኪያ ወይም ደግሞ ሊከሰቱ በሚችሉ የተለያዩ ኩነቶች (probabilities) መልክ ካልሆነ በስተቀር በእርግጠኝነት ማመን (accurate prediction) አይቻልም:: ይህ የሚሆንበት ምክንያት ማንኛውም ምሉዕ ነገር (wholistic entity) በብዙ ተናጠል ነገሮች (quantum particles) የተገነባ ሲሆን፤ እነዚህ ተናጠል ነገሮች የማይመሳሰል የይዞታና የልኬታ (position and velocity) ባህርይ ያላቸው እጅግ ተለዋዋጭ ክስተቶች በመሆናቸው ሁሉንም በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ መለካትና ማወቅ ስለሚያስቸግር ነው::

የነገሮችን የወደፊት ምንነት ለማገመት በሚፈለግበት ጊዜ በአሁኑ ህልውናቸውና በወደፊቱ ማንነታቸው መካከል እየተወራረሱ በመግባት ተፅእኖ የሚፈጥሩ የሚታወቁና የማይታወቁ የለውጥ ጫናዎች (variables) የግድ መኖራቸው ስለማይቀር በእርግጠኝነት ማመን (accurate prediction) እንዳይቻል ያደርጋሉ:: ስለሆነም፣ ስለነገሮች መፃኢ ሁኔታ ማመን የሚቻለው በተነፃፃሪ ብቻ ነው፤ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን የለውጥ ጫናዎች (variables) በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ መለካት ስለማይቻል::

እርግጠኛ ያለመሆን መርሆ (uncertainty principle) የተመሰረተው በዚህ አጠቃላይ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ነው:: ይኸው መርሆ እንደሚያስገነዝበው ይልቁንም በምሉዕ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ተናጠል ነገሮች ወይም ክስተቶች ምንጊዜም ቢሆን በተቃራኒዎች አንድነት (particles and anti-particles) የሚገኙ በመሆናቸው የሁኔታዎቹን የወደፊት ለውጥና ማንነት ይበልጥ ኢ-ተአማኒ (unpredictable) ወይም እርግጠኛ ያልሆነ (uncertain) ነገርን ያመለክታል:: እርግጠኛ ያለመሆን መርሆ የሚሰራው ግን ከላይ በአጭሩ ለማሳየት እንደሞከርኩት በተፈጠሮ ሳይንስ ብቻ አይደለም:: በማህበራዊ ሳይንስ

ውስጥ የሚሰራ ለመሆኑ ሊቃውንቱ ተጠቅመውበት አረጋግጠዋል:: ስለዚህም የማህበራዊ ሳይንስ አካል በሆነው በፍትህ ስርዓት በአጠቃላይና በዳኝነት ጉዳዮች ውስጥ ደግሞ በተለይ የማይጠቅምበት ምክንያት የለም::

አንድ የተወሰነ የዳኝነት ሂደት ተጠቃሎ አንድ ምሉዕ (wholistic) ውጤት የሚያመጣ ሲሆን ከአጀማመሩ እስከ መጠናቀቂያው ድረስ ግን በውስጡ በርካታ ተናጠል ደረጃዎችን (quantum stages) ያካተተ መሆኑ ግልፅ ነው:: ከእነዚህ ተናጠል ደረጃዎች ጉዳዮች ጋር በተገናኘቶ ደግሞ ተናጠል ውሳኔዎች ወይም ብይኖች ይኖራሉ::

ተናጠል ጉዳዮች ላይ ለመበየን ይቻል ዘንድ በተቻለ መጠን የሚረዱ ህጐች ቢኖሩም፤ ህጐቹ ራሳቸው ክፍተት ያላቸው ሁኔታዎችን የሚያስተናግዱ ስለሆኑ፤ እንዲሁም የጉዳዮቹና የህጐቹ አተረጓጐምና ውርሰ- ዝምድና (correlation) በዳኞች ስነ ባህርያዊና ፖለቲካዊ አቋም፣ በልምዳቸውና በእውቀታቸው፣ በከሳሽና በተከሳሽ ሙግታዊ ጭብጦች ላይ የሚመሰረት በመሆኑ፤ በወቅቱ በሚኖረው ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ስርዓቱ በፍትህና በፍርድ ቤቶች ላይ በሚኖረው አመለካከት፣ በዳኝነት ነፃነት ደረጃው ወ.ዘ.ተ ተፅእኖ ውስጥ የሚሰሩ በመሆናቸው ብይኖችን አስቀድሞ በማያጠራጥር ሁኔታ ለመገመት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ አይቀርም:: ማህበራዊ ግንኙነቶች ከፊዚካል (አካላዊ) ነገሮች ውስብስብነት በላይ የሰዎች አስተሳሰብ መለኪያቸው ስለሆኑ ይበልጥ ይወሳሰባሉ:: ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጫናዎች (variables) ተፅእኖ ስለሚያደርጉባቸው በብዙ ሁኔታዎች እንኳንስ ተቃራኒ ወገን የያዙ ተከራካሪዎች ቀርቶ ራሳቸው ዳኞቹም ቢሆኑ የአንድን ተናጠል ጉዳይ ብይን (quantum decision) አስቀድመው በእርግጠኝነት ሊያምኑ (accurate prediction) ያስቸግራቸዋል:: ዳኝነት ደግሞ በተቃራኒ የሚቆሙ ወገኖች መከራከሪያ ሀሳቦችን የሚያካትት በመሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ ኢ-ተአማኒ (unpredictable) የማድረግ እድሉን ያሰፋዋል::

ይህ የሚያሳየን በራሱ ስርዓት ብቻ የሚመራ ጤናማ ዳኝነት እርግጠኛ ባለመሆን መርሆ (uncertainty principle) የሚገዛ መሆኑን ነው:: በዚህ መርሆ እስከተገዛ ድረስ ደግሞ አንድ የዳኝነት ሂደት በአጠቃላይ አነጋገር ፍትህና በጐነት (Justice and fairness) ያለው ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል::

የተከበረው ፍርድ ቤት፤

የዚህ ክስና የዳኝነቱ ሂደት ግን ከዚህ ሳይንሳዊ መርሆ ባፈነገጠ አኳኋን በመመራት ላይ ይገኛል የሚል እምነት አድሮብኛል:: የክሱ ሂደት ከተጀመረ ጀምሮ እስከአሁን በነበረው አጭር ጊዜ ውስጥ እንኳን ማሰባሰብ በቻልኩት ተጨባጭ ማስረጃ መሰረት ብይኖቹ የሚሰጡት በእርግጠኝነት ተአማኒ (accurately predictable) በሆነ ዝንባሌ ነው::

ዳኝነቱ ከተጀመረ እስከዛሬ በአምስት ያህል ተናጠል ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ተሰጥቶ አራቱ ውድቅ ተደርገዋል:: ጉዳዮቹ ውድቅ እንደሚደረጉ እኔና ሌሎች ተከሳሾች አስቀድመን አምነን (predict) ነበር:: ይቺን ትንሽ ሰርቬይ በጠበቆቹ ውስጥ አልሰራሁም እንጂ እነሱም ቢሆኑ በተመሳሳይ አስቀድመው እንደገመቱ ጠንካራ ግምት አለኝ:: ውድቅ እንደሚደረጉ ያመነው በህግም ሆነ በፍትህ አንፃር ውድቅ ሊደረጉ ይገባል ብለን በማመናችን ሳይሆን ፍርድ ቤት ውድቅ ሊያደርጋቸው ስለሚፈልግ ነው በሚል ግምት ነው:: ግምታችን ግን ትክክል ሆኗል::

ለራሴም እንኳን ሳይቀር በጣሙን የሚገርመኝ ነገር፤ ይህን ማመልከቻ በፃፍኩበት ወቅት ለፍ/ቤቱ ባቀረብኩትና ፍ/ቤቱም በተቀበለው የመብት ረገጣ አቤቱታዬ ብይን ገና አልተሰጠውም ነበር:: እኔ ግን የፍ/ቤቱ ብይን መብትህ አልተረገጠም የሚል መሆኑ አይቀርም ብዬ አስቀድሜ በማመኔ ይህን ፅሁፍ አዘጋጀሁ:: በጤናማ የዳኝነት ሁኔታ ውስጥ ብሆን ኖሮ ይህንን ማድረግ አልነበረብኝም:: ብይኑን ሳላውቅ ውድቅ እንደሚደረግ በማመን ማመልከቻዬን ያዘጋጀሁት ሂደቱ ማንኛውም ጤናማ በጐ የዳኝነት ሂደት

ሊከናወንበት የሚገባው እርግጠኛ ያለመሆን መርሆ (uncertainty principle) እንደማይመራ በመገንዘቤ ነው። የዳኝነቱ ስርዓት እርግጠኛ የማይሆን (uncertain) እና ኢ-ተአማኒ (unpredictable) ቢሆን ኖሮ እኔም ይህን ማመልከቻ ለመፃፍ እርግጠኛ ስለማልሆን የተለያዩ ግምቶችን በአእምሮዬ እየጠነሰስኩ ብይኑን እጠብቅ ነበር።
እዚህ ላይ፣ ራስህ ተከሳሽ በመሆንህ የብይኖቹን ውጤት አስቀድመህ በአሉታ ስለምታስባቸው ትክክለኛውን ውሳኔ ሳይቀር የዳኝነት መዛባት አድርገህ ስለምትወስድ ነው የሚል ዋጋ ያለው ነጥብ በማንም አእምሮ ውስጥ ሊነሳ እንደሚችል እገምታለሁ። ሆኖም ጉዳዩ ዳኝነቱን የተዛባ አስመስዬ በማሰብ እንዳልሆነ በጥቂት ንድፈ ሀሳባዊና ተግባራዊ ማስረጃዎች ማሳየት ይቻላል።
1) በኳንተም ቲዎሪ (quantum Theory) መሰረት አስተሳሰብና እውነታ (thought and reality) ተነጣጥለው የሚታዩ ሳይሆን አንዱ የሌላው አካል ናቸው። አስተሳሰብ ከአንጎል የሚመነጭ ይሁን እንጂ የሚፈጠረውና የሚመሰረተው ግን ከአንጎል ውጭ በአካባቢያችን በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ምክንያት ነው። በልምድ፣ በእውቀትና በሌሎች ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ የመቀናበር ጠባይ ይኖረዋል እንጂ አስተሳሰብ በመሰረቱ የእውነታ ነፀብራቅ ነው። ስለክሱ የሚኖረኝ አስተሳሰብም በመሰረቱ ከዳኝነቱ ስርዓት እውነታ የማገኘው እንጂ እንዲሁ ከባዶ ነገር በአእምሮዬ የማፈልቀው አይደለም ማለት ነው።
2) ጤናማ ባልሆነ የፍርድ ስርዓት ውስጥ እንኳ ቢሆን ተከሳሾች ስነ ባህርያዊ መግለጫ (psychological make-up) በአብዛኛው ብይኖች ለራሳቸው እንደሚጠቅሙ የሚመኙበት ተስፋኛ አስተሳሰብ እንጂ አይበየንልኝም የሚል አሉታዊ አስተሳሰብ እንዳልሆነ በጥናት የተረጋገጠ ነው። ተከሳሽ በአብዛኛው አሉታዊ የማመን አስተሳሰብ (negative prediction) የሚያይ ከሆነ በዳኝነት ስርዓቱ ላይ ጤናማ ያልሆነ ሂደት ለመኖሩ ጠንካራ ምልክት ሊሆን እንደሚችልም ይታወቃል። በዚህ መሰረት እኔ በብይኖቹ ላይ የያዝኩት የግርምቢጥ (paradoxical) አስተሳሰብ በመሰረቱ ከዳኝነቱ ባህርይ የመጣ እንጂ በተከሳሽነት ስነ-ባህርይ ሊኖረኝ የሚገባ አስተሳሰብ አይደለም ማለት ነው።
3) በብይኖቹ ላይ የያዝኩት አሉታዊ ማመን በአንድ ወይም በሁለት ተናጠል ብይኖች ላይ ብቻ ተመስርቼ የያዝኩት ሳይሆን በተደጋጋሚ የታዘብኩት ነው። የፍርድ ቤቱን ጊዜ ማጥፋት አልሻም እንጂ ከአሁን በፊት በተከሰስኩበት የዳኝነት ሂደትም ያጠናሁትም ጭምር ነው።
4) የዳኝነት ስርዓቱን ጤናማ አለመሆን የሚያመለክተው ግን በእኔ በኩል በመገለፁ ብቻ አይደለም። በተቃራኒ ወገን የቆሙት አቃቤ ህጉም ቢሆኑ የዳኝነቱን ሂደት አስቀድመው በእርግጠኝነት እንደሚያምኑ (accurate prediction) ግልፅ ይመስለኛል።
አቃቤ-ህጉ በሁሉም ብይኖች ላይ ፍርድ ቤቱ ለሳቸው እንደሚፈርድላቸው ሳይጠራጠሩ አስቀድመው የሚያምኑ መሆናቸውን፤ ህሊናቸውን ከታሰረበት ሰንሰለት ነፃ አውጥተው ሊያምኑልኝ ይችላሉ ብዬ ባልገምትም፤ በጥቆማ ወይም በመረጃ ሳይሆን በማስረጃ ያገኘ ሁባቸውን አስተሳሰባቸውን በማጠየቂያነት ላቀርብ እችላለሁ። ህዳር 20 ቀን 1994 ዓ.ም ለዚሁ ፍ/ቤት ባቀረቡት «የክስ መቃወሚያ መልስ» ፅሁፋቸው ገፅ 5 ውስጥ «..ሌሎቹ የተከሳሾች መቃወሚያዎች በክስ መቃወሚያነት ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆናቸው የምናቀርበው መልስ ሳይጠበቅ <u>መሉ ለሙሉ የተከበረው ፍ/ቤት ውድቅ እንደሚያደርግልን የምንተማመን ቢሆንም</u>..» የሚል አስተሳሰብ ተገልጿል።
አገላለፁ የህግ አነጋገር ነው አይደለም የሚለው አከራካሪ ቢሆን እንኳ ግራና ቀኝ የሌለው ማመን (accurate prediction) በመሆኑ ግን የሚያከራክር አይደለም። የተከበሩ አቃቤ ህግ በዳኝነት ሂደቱ ላይ ያላቸው አስተሳሰብ እንደማንኛውም እኩል ከሳሽ የእኩል ዜጎች ነፃነት («liberty of equal citizenship») ቢሆን ኖሮ የሚጠቀሙበት አነጋገር፤ «ፍ/ቤቱ ውድቅ እንዲያደርግልን እንጠይቃለን»፣ ወይም «ውድቅ እንደሚሆን እንገምታለን» የመሳሰለ በሆነ ነበር። በእርግጠኝነት እንዲናገሩ የተገፋፉት ከዳኝነት ስርዓቱ እውነታ (reality) ያገኙት አስተሳሰባዊ ነፀብራቅ ቢኖር ነው ብሎ መገመት ይቻላል።
በእሳቸውና በእኔ ማመን መካከል ያለው ልዩነት የኔ አሉታዊ (negative prediction)፣ የእሳቸው አዎንታዊ (positive prediction) መሆኑ ብቻ ነው። ይህ ልዩነትም ከተቃራኒ ተከራካሪነታችን የመጣ ነው። በዚህም ሆነ በዚያ ያለው ሁኔታ የሚያረጋግጠው ግን

የዳኝነት ሂደቱ እርግጠኛ ባለመሆን መርሆ (uncertainty principle) መሰረት የማይሰራ መሆኑን ነው:: በዚህ መርህ የማይሰራ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ፍትህ-አልባና ተቀባይነት የሌለው ነው የሚለውን በመጀመሪያ ላይ የመሰረትኩትን መላ-ምት ትክክለኛነት ቢያንስ ለራሴ ያረጋገጥኩ ይመስለኛል::
የተከበረው ፍርድ ቤት፤
መላ-ምቴን መስርቼ፣ ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመዘርዘር የሞከርኩት የተከፈተብኝን ክስና የዳኝነቱን ሂደት፣ በዚህም ውስጥ የሚኖረኝን የራሴን ሚና በሚመለከት ወደ መደምደሚያ ከመድረሴ በፊት በተራ ግምትና በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን፣ በእውቀትና በምክንያት ላይ የተመሰረተ አቋም ለመያዝ እንዲመቸኝ ብዬ ነው:: በዚሁ የምክንያታዊነት ፈለግ የደረስኩበት አቋም ደግሞ፤ ለፍርድ ቤቱ ያለኝ ሙሉ አክብሮት ሳይቀንስ፤ ይህ ፍርድ ቤት በጉና ፍትሀዊ በሆነ ሂደት ክሱን ተመልክቶ ትክክለኛ ፍርድ ሊሰጠኝ አይችልም የሚል ሆኗል::
ይህንኑ አቋሜን በሌላ፣ ለየት ባለ ፈለግ ለመሞከርና ለመመርመርም ጥረት አድርጌያለሁ :: እሱንም በአጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁ:: ታላቅ የህግና የፍልስፍና ምሁር የሆኑት ፕሮፌሰር John Rawls, Theory of Justice በተባለ እውቅ መፅሐፋቸው እንዲህ ይላሉ:- Justice is The First virtue of social institution, as truth is of systems of thoght.A theory, however elegant and economical, must be rejected or revised if it is untrue; likewise lawa and institutions, no matter how efficient and well arranged, must be reformed or abolished if they are unjust. Each person possesses an inviolability founded on justice that even the welfare of society as a whole cannot override. For this reason justice denies that the loss of freedom for some is made right by a greater good shared by others. It does not allow that the sacrifices imposed on a few are outweighed by the larger sum of advantages enjoyed by many. Therefore, in a just society the liberties of equal citizenship are taken as settled; the rights secured by justice are not subject to political bargaining or to the calculus of social interests... Being first virtues of human activates, truth and justice are uncompromising. የ1971 እትም፣ ገፅ 3:: ትርጉሙ ደግሞ የሚከተለው ነው:- «የማህበራዊ ተቋማት ቀዳሚው ቅድስና ፍትህ ሲሆን የአስተሳሰብ ስርዓት ቅድስና ደግሞ እውነት ነው:: አንድ ንድፈ ሃሳብ፤ የቱንም ያህል ውበትና ጠቀሜታ ቢኖረው፤ እውነት እስካልሆነ ድረስ እንዲወድቅ ወይም እንዲሻሻል መደረግ ይኖርበታል:: እንደዚያውም ሁሉ ህጎችና ተቋሞች፤ ምንም እንኳ በውል የተደራጁና ቀልጣፋ ቢሆኑም፣ ኢ-ፍትሀዊ እስከሆኑ ድረስ ሊስተካከሉ ወይም ሊሻሩ ይገባል:: እያንዳንዱ ሰው የህብረተሰቡ ብልፅግና (ወይም ደህንነት) በአጠቃላይ እንኳ ቢሆን ሊከላው የማይችል የማይገሰስ መብት አለው:: በዚህም የተነሳ ጥቂቶች ነፃነታቸውን ቢያጡም ሌሎች በሚቀዳጁት የላቀ ጠቀሜታ ሊስተካከል ይችላል የሚባለውን አስተሳሰብ የፍትህ መርሆ አይቀበለውም:: ጥቂቶች እንዲከፍሉ የሚጫንባቸው መስዋእትነት ብዘሃን በሚደሰቱበት እርባና አማካይነት ይካካሳል የሚባለውን ስሌትም አይፈቅድም:: በመሆኑም ፍትሀዊ ህብረተሰብ ውስጥ የእኩሎች ዜግነታዊ ነፃነት እንደቅቡል የሚወሰድ ነው:: በፍትህ የተረጋገጡ መብቶች ለፖለቲካዊ እሰጥ አገባ የሚቀርቡ ወይም በማህበራዊ ፍላጎቶች ስር የሚወድቁ አይደሉም::... የሰው ልጆች እንቅስቃሴ ቀደምት ቅድስናዎች የመሆናቸውን ያህል እውነትና ፍትህ ለድርድር የማይቀርቡ ናቸው::»
የማምንበት አስተሳሰብ ከዚህ በላይ ቅልብጭ ብሎ የቀረበው መልክ የተነገረውን ነው:: ህዳር 6 ቀን 1994 ዓ.ም ለዚሁ ፍ/ቤት ባቀረብኩት የክስ መቃወሚያ አቤቱታዬ ላይ የገለፅኳቸው ህገ-መንግስታዊ መብቶቼ እነሆ እንዲረገጡ ተበይኗል:: ስልጣኑን የያዘው አካል ለራሱ ፖለቲካዊ መሻሻጫ ሲል ዜግነታዊና ህገ-መንግስታዊ መብቴን ረግጦ የፖለቲካ እስረኛ ሲያደርገኝ ያድነኛል ብዬ የገመትኩት ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ሊረዳኝ አልቻለም:: እንዲያውም «ሲቀብሩት ብትደርስ አፈር ለግስ» እንደሚባለው የጨቋኞች ተባባሪ ሆኖብኛል:: ለዚህ አይነቱ እሰጥ-አገባ አሳልፌ የምሰጠው መብት የለኝም የሚል ነው የኔ አቋም::
መብቴን በዳኞች ቁጥር፣ በዳኞች እውቀትና ልምድ ለውጠውና ወስነው፤ መብቴን ከዳኞች በጉ ፈቃድና ችሮታ ጋር አደራድረው ሊያስረግጡ የዳዱትን የተከበሩ አቃቤ

ህጉን የምልጃ አይሉት የሽንገላ፣ የህግ አይሉት የግብረ-ገብ አስተሳሰብ አሜን ብዬ የምቀበልበት ህሊና ከቶ እንዲኖረኝ አልመኝም።
እንዲሁም ደግሞ የይግባኝ መብቴ ይከበርልኝ ብዬ ባነሳሁ ከይግባኝ መብትህ ይልቅ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብትቀርብ ፈጣን ፍርድ ታገኛለህና ይጠቅምሀል የሚለውን፤ በይግባኝ መብቴና የተፋጠነ ፍርድ በማግኘት መብቴ መካከል ለድርድር እንድቀመጥ የሚገፋፋኝን፤ የተከበሩ አቃቤ-ህጉን እኔ አወቅልሀለሁ አይነት የጉልበተኞች የጨዋታ ህግ የማስተናግድበት የህሊና አምሮትም የለኝም። ሁለቱም መብቶች ሊረጋገጡልኝ የሚገቡ ተካካቢ መብቶቼ (complimentary rights) ናቸው እንጂ እርስ በእርሳቸው የሚተካኩ መብቶች (substitutable rights) አይደሉም። ደግሞም እኮ የሚሻለኝን መብት ለማወቅ ሞግዚት አያሻኝም። (የአቃቤ ህጉን «የክስ መቃወሚያ መልስ» ፅሁፍ፣ ህዳር 20/1994፣ ገፅ 9 ይመለከቷል)
በዚህ አይነቱ ኢ-ፍትሀዊ የአቃቤ- ህግ ፍርጃና ህሊናዬ በማይቀበለው የፍርድ ቤቱ ብይን መካከል እንደህውልት ተገትሬ ራሴን ሳየው ስሞክር ፕሮፌሰር Rawls የሰው ልጆች ህልውና ቀደምት ቅድስናዎች ፍትህ ናቸው የሚሉት መርሆ ውሉ ይጠፋብኛል። ሆኖም ውሉ ጠፍቶብኝ ነሁልዬ እንዳልቀር ያለኝ አማራጭ እንደ ሀውልት ከተገተርኩበት የአቃቤ ህጉና የፍርድ ቤቱ መቀራቅር በማፈትለክ የህሊና ነፃነቴን በራሴ ማወጅ ብቻ ነው።
በህዳር 6/1994 ዓ.ም የክስ መቃወሚያዬ ለማሳየት እንደሞከርኩት እኔ በፖለቲካ ልዩነት ምክንያት የታሰርኩ የፖለቲካ እስረኛ ነኝ። ይህ ክስ የሚታየው ህገ-መንግስቱን በፍፁምነት በረገጡ ጨቋኝና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ህጐች ነው። በእነዚህ አምባገነናዊ ህጐች የሚዳኘውን ዳኝነት ተቀብዬ እንኳን ብቀጥል የህጐቹን ፍትህ ሰጪነት ያመንኩ ያህል ይሰማኛል። እውነትንና ፍትህን ከመብቴ ጋር በዚህ ፍ/ቤት ፊት የማስከብርበት አንድ ማስሪያ ቀርቶኛል። እሱም ፖለቲካዊ ተውኔት እንጂ የህግ አስከባሪነት ክስ አይደለም ብዬ ከማምንበት ከዚህ የፍርድ ሂደት ሀቀኛ ፍርድ አገኛለሁ የሚል የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እንኳን እምነት እንደሌለኝ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያውቅልኝ ማድረግ ነው። በዚህ የማመጣው ለውጥ ባይኖርም የህሊና ሀብቴን ለማንም ሳልሸጥ መጠበቅ እችላለሁ። ከእንግዲህ ከህሊናዬ በስተቀር ሌላ ዳኛ የለኝምና።
የአሁኑን ሁኔታ በ15 ዓመቱ የበረሀ ትግሌ ማገናዘቢያነት (analogy) ሳየው እወዳለሁ። የደርግን ጨቋኝ ስርዓት ለመጣል ብሎም ፍትህንና ብልፅግናን ለማስፈን የታገልኩበት ጊዜ ፀፀቶች አያውቅም፤ ወደፊትም አይቆረቁረኝም። በዚያ መራራ ትግል ውስጥ ስሳተፍ መጨረሻው እንዳሰብኩት ይሆናል በሚል አምኜበትና መልካም ተስፋ ሰንቄ፣ ድብቅ አጀንዳና የተሸፈነ አላማ ሳይኖረኝ ነበር። ሌላ የጭቆናና የመከራ አዙሪት የሚታይበት ይህ የዛሬው ስርዓት ይመጣል ብዬ ጭራሽ አላሰብኩም። የትግሉ መድረሻ የአሁኑ ፍትህ-አልባ ስርዓት መሆኑና ለዚህም በመሳሪያነት ማገልገሌ ግን ይፀፀተኛል። ካለፈ በኋላ ቢሆንም እንኳ በዚህ ሁሉ የትግል ውጣ ውረድ ውስጥ ሰው ነኝና የተሳሳትኳቸውን ፖለቲካዊ ስህተቶች በተመለከተ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ወደፊት በዝርዝር በማውጣት የመጪው ትውልድ ማስተማሪያ አደርጋቸዋለሁ።
የዚህ ክስና የዳኝነት ሂደት ግን የተለየ ነው። ተከራክሬም ሆነ ሳልከራከር የመጨረሻ ውጤቱ ለውጥና ልዩነት እንደሌለው በብዙ ምልክቶች አምኛለሁ። ከአሁን በፊትም ተከስሼ በባለስልጣኖች ቀጥተኛ ግፊትና ጣልቃ ገብነት የተፈረደብኝ ለመሆን በህይወቴ አማካይነት ያገኘሁት ተሞክሮ ስለሆነ፤ አሁንም በድጋሚ ቀደም ሲል በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች ፍትህ የማላገኝበት ፍርድ ቤት መሆኑን ስለማምን፣ በገናው ፍትህ አገኛለሁ የሚል ተስፋ ለምን ይኖረኛል? ለምንስ ለሁለተኛ ጊዜ እጃጃለሁኝ? ይልቁንም ከዚህ ፍርድ ቤት ፍትህ አገኛለሁ የሚል ተስፋ ከያዝኩ ልብ ወለዱን የክሱን ድራማ እውነተኛ ታሪክ በማስመሰል እውቅና ሰጥቼ ስህተት ውስጥ የምገባ መስሎ ይሰማኛል። ፍትህ አለ በሚለው የአደናጋሪነት ሰልፍ ላይ ተመቲመኛ ሆኜ የቆምኩም ይመስለኛል።
ይህን ያህል ለራሴ ግልፅ ከሆንኩ ግን ከዚህ በኋላ ቢሆን በፍርድ ቤቱ ዘንድ የምከራከረው የሚፈረድብኝን ውሳኔ፤ ለህገ-መንግስቱ ክብርና ሉአላዊነት፣ ለዳኝነት ነፃነትና ለፍትህ ስርዓት መወለድ፣ ለዜግነት መብት መከበር፣ እንዲሁም ኢትዮጵያዊነትን መልሼ ለተላበስኩበት አላማ ስለተሟገትኩ የተዋለልኝ ውለታ እያልኩ፤

ፍፁም ለማይቀረው ነፃነቴ በውድ ቅርስነት ጠብቄው የምኖረው የመንፈስ ሀብት ስለሚሆነኝ ነው::
በተረፈ ለዚህ ያብቁኝን የቀድሞዎቹን ጓደኞቼን፣ እንደኔ ወህኒ ተወርውረው ከመማቀቅም በላይ ግፍና በደል እንዲፈፀምባቸው፤እንደኔ ልጆች፣ ልጆቻቸው ግድያ እንዲደገስላቸው፤ እንደኔ ቤተሰቦች፣ ቤተሰባቸው እየተሰደደ የቀሩትም በገዛ አገራቸው እየተሰቃዩ እንዲኖሩ ፍፁም አልመኝላቸውም:: ለእኔ እንደሚመኙት እነሱ በችጋር ተቆልተው እንዲፈገሙም ጭራሽ አልመኝም:: ይህ ሁሉ የሰዎች ሰይጣናዊ ገፅታ፣ የእነሱን መሳይ የአውሬነት ባህርይ እንጂ ሰብአዊ ባህርይ ከቶ አይደለም::
እኔ የምመኝላቸው ልብ እንዲያገኙ ብቻ ነው:: ለዚህች አገር የቆምንላት እኛ ብቻ ነን የሚለውን በግብዝነት የተሞላ ግትር አስተሳሰባቸውን አሽቀንጥረው፤ «ተሀድሶ» ብለው የጠሩትን የያእቆብ ጨዋታቸውን ረስተው፤ መላውን ህዝብ በአንድነት አላማዎች ዙሪያ በማስተባበር፤ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ደህንነትና ብልፅግና እንቆማለን የሚሉትን ምሁራንና ባለሙያዎች ሁሉ መጣፊያ ሳይጥፉባቸውና ክርስትና ስም ሳይሰጧቸው በማሰባሰብ ይቺን አገር ልትወጣ ከማትችልበት የውድቀት አፋፍ ለመመለስ የመጨረሻውን እድል እንዲጠቀሙበት ነው:: ፀሐይቱ አዘቅዝቃለች እንጂ ገና አልጠለቀችም:: የአስተሳሰብ ለውጥና የሚከፈት ልብ ግን እየጠየቀች ነው::
የምፅአቷ ቀን ግም ያለች እንደሆን፣
የነፍስ ዛንዝራን፣ የህይወት ብረት መዝጊያ...
አድኖም አያድን፤
ሱባዔም አያግዝ፣ ስጋ ወደሙ አይሆን፣
አሁን ነው ንሐሰ፣ አሁን ነው መፀለይ...
ዛሬ ነው መመነን፤
አሉ-አሉ መምህሩ
የነፍስ ልጃቸውን ሲመክሩ-ሲዘክሩ::

**/የቀድሞ የኢፌዲሪ ጠ/ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ከአምስት አመት በፊት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ/**

# ኢትዮጵያ የጠቀየችውን መፅሀፍ አይታችሁ መልስ ስጡኝ!

ከመርዓዊ ሜጌሶ

እንደ ዕድል ሆኖ በዚህ ዘመን የምንገኝ ዜጐች አገሪቱ ብዙ ጥያቄ በምታርብበት ጊዜ ላይ እንጂ ብዙ መልስ በምትሰጠን ዘመን ላይ አይደለንም:: አገሪቱ መልስ ስትጠይቅም በዋናነት መልሱ እኛን ለማሳደግና ፍሬ አፍሪ ለማድረግ እንጂ ለራሷ የክብር ስም ማግኘት ጥሟት አይደለም:: ይህንን ለማድረግ አገሪቱ በመቀነቷ የቋጠረችውን እየፈታች አንዳንድ ልጆቿ ለሌላው መልስ ይሰጡ ዘንድ አሰልጥናለች::
የማሰልጠኗ ዓላማ ሰልጣኞቹ መልስ እንዲያመጡ፣ መንግስቷ ለልጆቿ የመልስ ማህደሮችን እንዲያገኝ ይቻለው ዘንድ መሆኑ እሙን ነው:: በዚህ አይነቱ የመልስ ፍለጋ ጥረት ላይ ግን አገሪቱ አንድ የሚያሳዝን ነገር አይታለች:: ይኼንን ለእያንዳንዱ ዜጋ የገለፀች ቢሆንም ብዙ ያልሰሙ እንዳሉም ታውቃለች:: ስለዚህ ይህንን አሳዛኝ ሁኔታ አፍ ቢኖራት እንደሚከተለው የምትገልፀው ይመስለኛል:
«እኔ መልስ ታመጡ ዘንድ የፈለግኹት ሌት ተቀን ተጣጥራችሁ መልሶችን እንድታገኙ ነው፤ለጥያቄዬ መልስ ስጡ ስል እኔን እናታችሁን ለማበልፀግ የሚያስችል መልስ በዓለም ዙሪያ በየመፀሀፉ ይፋ ሁኖ እያለ፤ ያን መፅሀፍ አገላብጣችሁ እኔን ማበልፀግ የሚያችል ምላሽ ማግኘት ስላልቻልኩ መጥሪያው በፍ/ቤት ግቢ እንዲለጠፍ ተደርጓል::

ምላሽ ማግኘት የተሳናችሁ መሆኑ በእጅጉ አሳዝኖኛል:: በየትምህርት ቤቱ የምትፈተኑት ፈተና የኔን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ይመስለኝ ነበር:: ግን የሰጣችሁኝ ተጨባጭ መልስ የለምና የኔን ፈተና እንደምትፈተኑ መጠበቁ ስህተት ሁኗል ማለት ነው:: ምን ለማለት እንደፈለግሁ ትንሽ ላብራራላችሁ::
በት/ቤት የምትማሩት ትምህርት ሁሉ እኔ በተጨባጭ የጠየቅኩትን ጥያቄ መልስ ነው:: በየወረቀቱ መምህራኖቻችሁ ትምህርት ብለው ያስተማሯችሁ የኔን ጥያቄ በጥያቄነት አንስተው መልሱም ይኼ ነው በሚል አግባብ ካልሆነ መማራችሁን እንዴት ነው የማውቀው? በየትምህርት ቤቶቻችሁ የሚቀርቡ የትምህርት ገበታዎች የኔን ጥያቄ የሚመልሱ ካልሆኑ የእናንተ ዲግሪና ዲፕሎማዎች ምን ያደርጉልኛል? ወይስ አለአግባብ እየወቀስኳችሁ ይሆን እንዴ? ምናልባት ለጥያቄዬ መልስ በሚሰጥ አግባብ ዕውቀትን የማደራጀት ኃላፊነት የወሰደው መንግስት መልሶችን ለማቅረብ አላስችላችሁ ይሆን እንዴ? ብዬ አስባለሁ:: እሱም ቢሆን ለኔ ብልፅግና መልስ በሚቀርብበት ስርዓት የተማረ ይመስለኛልና ነው::
እንደምታውቁት መንግስትነትም ትምህርት ይፈልጋል:: የሱ ትምህርት ፍሬ አፍሪ /አምራች/ ዕውቀቶች ውጤታማ ሆነው ብልፅግና የሚረጋገጥበትን ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት:: ይኼን ይመስለኛል ፖለቲካ በሚል የግሪኮች ቃል የምትጠሩት:: ስለዚህ መንግስትም ቢሆን መፅሀፍ ገልጦ መልስ የሚሰጥበትን ትምህርት የመስራት ሚናን ነው የሰጠሁት:: የትኛውም ፖለቲካ ብልፅግናን የማረጋገጥ አብይ ሚና አለበት:: ይህ ደግ አግባብ ባላቸው ትምህርቶች የሚያረጋገጥ ነው:: ብልፅግናው የሚረጋገጥበት አግባብ ከተገኘ የሀብት ክፍፍሉን በተለያየ «ክራሲ» መጥራት ይቻላል:: ማንኛውም ክራሲያ የማምረቻው (የማፍሪያው) መንገድ አንድ ነው:: ክራሲያዎች የሚለያዩት ወይም ሊለያዩ የሚገባው በሀብት ክፍፍሉ እንደሆነ እኔም ራሴ ሰምቻለሁ ወይም የገባኝ መስሎኛል ብል ይሻላል::

በየትኛውም ክራሲያ የሚመረትበት መንገድ አንድ ነው ስል ምን ማለቴ እንደሆነ በአንድ ምሳሌ ባስረዳ ሳይሻል አይቀርም:: ለምሳሌ ሳሙና ማምረት ብሻ የኔ ክራሲያ ሳሙናን ለማምረት የሚጠቀምባቸው ጥሬ ነገሮች ከሌላው ክራሲያ የሳሙና አመራረት ሂደት የተለየ አይደለም:: አንድ ነው:: በዚህ ምሳሌ መሰረት የአመራረት ሂደቱ በማናቸውም ክራሲያ አንድ ነው:: ክራሲያዎቹ የሚለያዩት በሀብት ክፍፍል ስርዓቱ ሊሆን ይችላል:: ወይም መሰለኝ:: እንደዚህ አይደለም እንዴ!?
ስለዚህ የኔ ክራሲያ ብልፅግናን አይፈቅድም በማለት ለኔም ሆነ ለራሳችሁ መልስ የመስጠት ኃላፊነታችሁን ልትወጡ አልቻላችሁም:: መልሱ ሁሉ በወረቀት እያለ መፅሀፍ አይታችሁ ምላሽ አለመስጠታችሁ ምንኛ እንዳንገበገበኝ እኔ ነኝ የማውቀው» የምትል ይመስለኛል ይህቺ ሃገር::
በዚህ አጋጣሚ ስለ መልስ አምጣ ጥያቄ (Open book question) ያለኝን ግንዛቤ በማከል ያገሪቱን ጥያቄ ለመጋራት የበኩሌን ልበልና እናጠቃልል::
የኦፐን ቡክ ጥያቄ ማለት፤ መምህሩ በትምህርቱ ሂደት ካነበባቸው መፅሀፍት መካከል መልስ የሚገኝለት ጥያቄ ለተማሪው ያቀርብና ተማሪውን መፅሀፍ ገልጠህ መልስ አቅርብ የሚልበት የጥያቄ አግባብ ነው:: የአፐን ቡክ ጥያቄን የሚፈሩና አንጀታቸው የሚገለባበጥላቸው መፅሀፍ ማንበብ አቀበት ለሚሆንባቸው ተማሪዎች ነው:: መፅሀፍ ውስጥ መልሱ እያለ በምን ፍላጐት ይነበብ? በዚህም ምክንያት ይኼ ተማሪ ባንዲራ ያውለበልባል:: («ኤፍ»ን ይቀበላል ለማለት ነው) ኢትዮጵያና አገሬ የመበልፀግ መብት አላት እያለ ሊፎክር ይችላል:: አገሪቱ ግን አንተ ወስላታ! ከአንተ አልነበር መልስ የምጠብቀው ብላ በትዝብት ታዝንበታለች::
(ኦፐን ቡክ ጥያቄ አሳር ያበላው ይኼ 3ኛ ዓለም የተባለውን አህጉር ነው:: ለዚህ ሕዝብ ማንበብ ለምን ጣር እንደሚሆንበት ለብዙዎች ይገርማቸዋል:: በዚህ የተነሳ አንዳንዶች ከአፍሪቃዊ ሚስጥር መደበቅ ከፈለግሽ ጻፈው! የሚሉት ወደው

ላይሆን ይችላል:: በእርግጥ አሁን አሁን በማንበብ ረገድ በአገራችን መጠነኛ መሻሻል እየታየ ሊሆን ይችላል )
ስለዚህ አገሪቱ እያለች ያለችው እኔን የማልሚያ ዕውቀት በየመፅሀፉና በየሰው ጭንቅላትም እያለ ድህነትን መታገል አልቻላችሁም ነው:: መሀረቤን ፈትቼ አስተምሬ እኔን በድህነት ማሳፈራችሁን መታገስ አልችልም እያለች ነው::

**/አቶ መራዊ ሜጌሶ፣የህግ ኮንሰልታንትና ሌክቸረር ናቸው/**

# የአፍሪካ መሪዎች የባህሪ መመሳሰል

**በይልማ በቀለ**

እዚህ አሜሪካን ሀገር የኢሊኖይ ግዛት አስተዳዳሪ በፈላ ውሃ ውስጥ ይገኛሉ:: የህግ አስፈፃሚ አካላት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አማካኝነት የስልክ መስመራቸውን ጠልፈዋል፤ እንዲሁም አስተዳዳሪው በተመራጭ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ የተለቀቀውን የሴኔት መቀመጫ ከፍተኛ ገንዘብ ለሚያመጣ ሰው በጨረታ ለመሸጥ ሲሞክሩ የሚያሳይ ማስረጃም አግኝተዋል:: ብዙ ሰዎች የአስተዳዳሪው ወስላታ ፖለቲከኛ መሆን አልገረማቸውም::
አማካኝ ቁጥር ያለው ዜጋ አብዛኛዎቹ ፖለቲከኞች የማይታመኑ የመሆናቸውን እውነታ ተቀብሏል:: ነገር ግን ፖለቲከኞች በአላዋቂ መደብ ውስጥ አይጠቃለሉም፤ ሞራል የሌላቸው ሊሆኑ ቢችሉም ጅላጅል አይደሉም:: ስለዚህ አስተዳዳሪው ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ሁሉ ለኤፍ.ቢ.አይ. «ሂዱና ስልኬን ጥለፉ» ብለው ሲናገሩ ማድመጥ አስገራሚ ነበር::
የአስተዳዳሪውን ያልተለመደ ፀባይ ተመልክተው የማያውቁ ሰዎች ምናልባት ሳያብዱ እንዳለቀሩ አስተያየታቸውን እየሰጡ ነው:: ለአንዳንዶች ይህ (እብደት) እንዲህ ላለ ሀፍረት የለሽ የህገ ወጥነት ተግባር ብቸኛው ተቀባይነት ያለው አስረጂ ነው:: ጠበቆቻቸውም «የአይምሮ ጤና መጓደልን» በፍርድ ሂደቱ ላይ እንደመከላከያ ለማቅረብ እየተዘጋጁ ሊሆን ይችላል::
ለእኔ የተስማማኝ ማብራሪያ በኒው ዮርክ ታይምስ መፅሔት ላይ በሚስተር ዲክ ካቬት የተቀመጠው ነበር:: «**How is that again Gov?**» በተሰኘ ርዕስ እንዲህ ተፅፏል::

«በዚህ ጉዳይ ቀልድ ቦታ የለውም ይሆን? ምናልባት:: የባለሙያ አስተያየት ማግኘት አስፈላጊ እንደሆነ ተሰማኝ፤ የረጅም ጊዜ ልምድ ያካበቱትንና በእንዲያ ዓይነት ጉዳዮች መፅሃፍት የፃፉትን ዶክተር ዊላርድ ጌይሊንን አማከርኩ ... በደንብ አስረዱኝ:: ቀድሞ «**Psychopath**» የነበረው አሁን ግን «**Sociopath**» (በሰዎች ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል የዓይምሮ በሽተኛ) ተብሎ ሊጠራ ስለሚችለው ገለፃ አደረጉልኝ:: ውስብስብ፣ ለማከም ከባድ፤ እናም «ፀረ ህብረተሰብ» ሊባል የሚችል:: በዚህ በሽታ በተያዘ ሰው ላይ ሊታዩ ከሚችሉት ስሜቶች መካከል አንዱ የጥፋተኝነት ወይም የሀፍረት ስሜት አለመኖር ነው:: ማዘን የሚባል ነገርም አይታወቅም::
«የአስተዳዳሪው አስደናቂ ድፍረት ሂዱና ስልኬን ጥለፉ እንዳይያዙ በተወሰነ መልኩ ከለላ እንዳላቸው ሁሉ ባሳዩት ፍፁም የሆነ የራስ መተማመናቸው ተብራርቷል:: ይህ ውሸታቸውንና እውነታቸውን ከሚቀላቅሉት የዓይምሮ በሽተኛ (**Sociopath** ) ችግሮች ጋር ተያያዥነት አለው:: ሁለቱን መለየት ባለመቻል ሀፍረት የለሽ በሆነ መንገድ ይቀጥላሉ፣...
«እንዲህ ዓይነት ሰዎች ያሉበት ሁኔታ እንደሚያሳየው፣ ለምሳሌ ዋና ዋና ተቋማትን በመምራት፣ ከማህበረሰቡ የተገለሉ አንዳልሆኑ ጌይሊን ያስታውሱናል:: ብዙ ጊዜ የአዋርድ ተሸላሚ አክተር ዓይነት የመተወን ክህሎት አላቸው፣ ታላቅ የሆነ መስህብ ሊያሳዩና ኤክስፐርቶችን እንኳን ሊያታልሉ ይችላሉ::»

ሚስተር ካቤት አንድ ነገር ሊያሳይ እንደፈለገ አምናለሁ:: የ«ሶሺዮፓት» ማንነት ከአብዛኛዎቹ የአፍሪካ መሪዎች ጠባይ ጋር ይተካከላል:: በህዝባችን ላይ ቀውስ እየፈጠሩ ያሉ አምባገነን አገዛዞቻችንን ያልተለመደ ፀባይ ያስረዳል:: ስለለየላቸው ጨካኞቹ ኢዲ አሚን፣ ዣን ቢ. ቦካሳ፣ መንግስቱ ኃ/ማርያም፣ ሞቡቱ ሴሲሴኮ እና ስለ ቻርልስ ቴይለር በስልጣን ላይ ያሉ የእብድ ሰዎች ተምሳሌቶች ከማለት በቀር ምን ማለት ይቻላል?

እናም ዛሬ የዝምባብዌው ሮበርት ሙጋቤ በዚህ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ:: ባለፈው መጋቢት ወር በዝምባብዌ ጠቅላላ ምርጫ ተካሄዶ ነበር:: በማንኛውም እማኝ መስፈርት በሞርጋን ቻንጋራይ የሚመራው ንቅናቄ ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ (MDC) ፓርቲ አሸንፏል:: ነገር ግን በሙጋቤ የሚመራው ገዢው ፓርቲ «ሚስተር ቻንጋራይ አብላጫ ድምፅ አላገኙም» በማለት የህዝቡን ውሳኔ አልቀበልም አለና ሁለተኛ ምርጫ እንዲካሄድ ፕሮግራም ተያዘ:: በስልጣን ላይ ያሉት በመሀል ያለችውን ጊዜ የተቃዋሚ አመራሮችን ለመግደል፣ ለማስቃየት፣ ለማሰደድ እና ለማሰር ተጠቀሙባት:: የሁለተኛ ዙር ምርጫ በሰኔ ወር ላይ ሲደረግ ሙጋቤ ማሸነፋቸው ታወጀና ሰኔ 22 ለስድስተኛ ዙር የመሪነት ዘመናቸው ቃለ መሃላ ፈፀሙ:: ይህንን አስቂኝ ሁኔታ ከአፍሪካዊያን አምባገነን ወዳጆቻቸው በቀር ማንም አልተቀበለውም ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ይህን ጉዳይ ለምን የምናውቀው የምናውቀው እንደመሰለን ለመገመት ከባድ አይደለም:: ሁሉንም አይተነዋልና::

በዝምባብዌ ወደታች ያዘቀዘቀው ቀስት ተጧጡፏል:: የዋጋ ንረት መገንዘብ እስከሚያቅተን ደረጃ ደርሷል፣ (231 በመቶ፣ ማለትም የአንድ ዳቦ ዋጋ 1.6 ትሪሊዮን የዝምባብዌ ዶላር) ወደ ውጭ ሀገር የሚሰደደው ህዝብ ቁጥር ከተባበሩት መንግስታት ቁጥጥር ውጭ ሆኗል፣ በሀገር ውስጥም የህዝቦች መፈናቀል አይሏል፣ እንዲሁም በሀገሪቱ መሰረታዊ የመንግስት ተግባሮች ሙሉ ለሙሉ ተቋርጠዋል::

ከበስተጀርባ ይህ ሁሉ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ በውሃ አማካኝነት የተስፋፋው የኮሌራ በሽታ ከነሃሴ ጀምሮ ከ16,000 የሚበልጡ ዝምባብዌያዊያንን አጥቅቶ ከ780 በላይ የሚሆኑትን ለህልፈት ዳርጓል:: በተፍረከረከ መንግስት የተለመደ እንደሆነ ሁሉ መቋጫው በቅርብ አይታይም:: ደቡብ አፍሪካ ዜጐቿን ለመጠበቅ ስትል ከዝምባብዌ ጋር ያላትን ድንበር ዘግታለች፤ የተባበሩት መንግስታት(UN)፣ የዓለም የጤና ድርጅት(WHO) እና የጤና አክስፐርቶች ሊጠቃ የሚችለው ህዝብ ቁጥር ወደ 60,000 ሊደርስ እንደሚችልና የሀገሪቱ 12 ሚሊዮን ህዝብ ግማሽ የሚሆነው አደጋ ላይ እንደሆነ እያስጠነቀቁ ይገኛሉ::

ግራ የተጋቡት መሪ እንዲህ ዓይነቱን ሰቅጣጭ ዜና ሲጋፈጡ ምላሻቸው ምን ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ? ከሁለት ሳምንት በፊት ባደረጉት የቴሌቭዥን ንግግራቸው የኮሌራ በሽታ ማብቃቱን ገለፁ:: «ኮሌራ የለም ... ብዬ ስገልፅ ደስተኛ ነኝ::»

ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን ምክንያታዊ ለማድረግ ሙከራ መሰረት ለሌለው ሀሜታቸው ምዕራባዊያንን በመውቀስ «አሁን ኮሌራ ስለሌለ የጦርነት አስፈላጊነትም የለም::» በማለት ደመደሙ::

አሁንም ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አዲስ አይደለም:: በሀገራችን ዩኒሴፍ(UNICEF) ስለርሃብ አስጠንቅቆ ከነበረ ጥቂት ወራቶች ብቻ ነው ያለፉት:: ዓለም ትኩረት ሰጥቶት አንድ ነገር እንዲያደርግ የማስጠንቀቂያ ደውሉን ለመደወል እየሞከሩ ነበር:: ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት ይገልፀው ከነበረው ታይቶ የማይታወቅ የ«ደብል ዲጂት» እድገት እና ብልፅግና ጋር የተቃረነ ነበር:: ለርሃብ የምግብ አለመመጣጠን ትርጉም ሰጡት:: በአሁኑ ሰዓት አብዛኛው ህዝባችን በእርዳታ ምግብ ላይ ጥገኛ ነው:: የትኛውም የሀገሪቱ ክልል ከዚህ ሰው ሰራሽ አደጋ እራሱን የሚያድንበት መከላከያ የለውም::

ከሁለት ዓመት በፊት ስርዓቱ ለቡሽ አስተዳዳር ውለታ ለመዋል ሀገራችንን ሊወሩ ተዘጋጅተዋል ያሏቸውን ኢስላማዊ ጂሃዲስቶችን ለመዋጋት የኢትዮጵያ ወታደሮችን ወደ ሶማሊያ ሰደደ:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፖርላማቸው ውስጥ ይህንን ድርጊት የተቃወሙትን ከ«አህያ» ጋር አነፃፀሯቸው «ሁለቱም ትላልቅ ዓይኖች አሏቸው፣ ግና ሩቅ መመለከት ይሳናቸዋል፤ ትላልቅ ጆሮዎች አሏቸው፣ ግና አይሰሙም::» ነገር ግን የሁለት ሳምንቱ ድንበር ዘለል አጭር ጉዞ በሺህ ለሚቆጠሩ ሶማሌ ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችን ለሞት እንዲዳረጉ ምክንያት ሆነ፤ ድህነትንና ርሃብን ለማጥፋት ሊውል የነበረው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እያወደመ ቆይታው ለሁለት ዓመት ተሸጋገረ::

ነገር ግን ይህን የተገነዘበው መንግስት መቋጫ አለመኖሩንና የካዝናውን ባዶነት በመመልከት በክብር የሚወጣበትን መንገድ እየፈለገ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ::
ከዚህ በኋላ አቶ መለስ «የሶማሊያ ተልዕኮአችን በስኬት ተገባዷል» በማለት በፓርላማቸው ፊት ሲያውጁ ብሰማ አያስገርመኝም::

## ቃለምልልሶች

# «ፖለቲከኛው ታምራት የክርስቶስ አገልጋይ ሆነ ብለህ ብትፅፍ ደስ ይለኛል»

**አቶ ታምራት ላይኔ**
**የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር**

---

***አሁን የ54 ዓመት ጐልማሳ ናቸው:: ከዚሁ ዕድሜያቸው ውስጥ 27 ዓመት ያህሉን እጅግ በጣም ፈታኝና መራር የሆነ ህይወትን ለማሳለፍ ተገደዋል:: የእኒህ ሰው የ15 ዓመታት የትግል ፅናትና አልበገር ባይነት መቼም እንደማይዘነጉት በቀድሞ ኢህዴን ውስጥ አብረዋቸው የታገሉ የቀድሞ ጓዶቻቸው ዛሬም ይመሰክራሉ:: በተለይ ከአቶ ስዬ አብርሃና ሌሎች የትግል ጓዶቻቸው ጋር በሀገረ ሰላም የኢህአዴግ ጦር ማዘዣ ጣቢያ ሆነው በሰጡት ትዕዛዝና ቆራጥ አመራር ግንባሩ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም አዲስ አበባን እንዲቆጣጠር ያስቻሉ ግንባር ቀደም ባለውለታ ናቸው::***

***ከዚህ በኋላ የሀገሪቱ ጠ/ሚኒስትር የሆኑት እኚህ ሰው ባልተጠበቀና ባልተገመተ ወቅትና ሁኔታ «ያለአግባብ ስልጣንን የመጠቀም ክስ» ተመስርቶባቸው ፍርድ ቤት በ18 ዓመት እንዲቀጡ ወሰነባቸው::***

***እነሆ 1/3ኛው የእስራት ጊዜ በአመክሮ ተነስቶላቸው ከ12 ዓመት በኋላ ባለፈው አርብ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ከእስር ለመፈታት በቁ - የዛሬው እንግዳችን አቶ ታምራት ላይኔ::***

***አቶ ታምራት የኮሚኒስት ስርዓት አቀንቃኝ ፖለቲከኛ፣ወታደር እንዲሁም ከፍተኛ ባለስልጣንም ነበሩ:: ከ12 ዓመት የእስር ዘመን በኋላ ግን «የፍቅር» ሰባኪ ሆነዋል:: አሁን እንደበታቸው ስለፍቅር መስክሮ የሚጠግብ አይመስልም:: የህይወት ሁሉ መሰረት «አምላክ ብቻ» መሆኑን ይናገራሉ:: «ለአምላክ ልቦናችንን፤ ለፍቅር በራችንን እንክፈት በዚህ መንገድ ብቻ ነው ኢትዮጵያን የምናሳድጋት» ይላሉ ደግመው ደጋግመው::***
***«ፍቅር ሁሉም ነገር ማለት ነው:: እስከዛሬ ያለፍናቸውን የብጥብጥ ታሪኮች ረስተን ለፍቅር በራችንን እንክፈት:: አምላክ የሰጠንን የፍቅር አንቀልባ እንጠቀምበት» ይላሉ በአፅንኦት::***

**የቀድሞ ጠ/ሚ/ር አቶ ታምራት ላይኔ ከ12 ዓመታት በኋላ ከእስር ሲፈቱ የመጀመሪያ የሆነውን ቃለ ምልልስ ከአውራአምባ ታይምስ ጋር አድርገዋል:: በዚሁ የመጀመሪያ ቃለምልልሳቸው «በመታሰሬ እድለኛ ነኝ» ሲሉም ተደምጠዋል:: እንዴት? በሚሰጡት ምላሽ ቃለምልልሳችንን እንጀምር:-**

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

*በአጠቃላይ ከእስር ቤት በፊትና በኋላ ያለው የእኔ የአስተሳሰብ ሁኔታ ተለውጧል አዎ! አመለካከቴ በብዙ መልኩ ተለውጧል እስር ቤት ውስጥ ያገኘሁት አንዱ ነገር እኔ ስጦታ ነው የምለው:: በእርግጥ ሰዎች ላይገባቸው ይችል ይሆናል አጠቃላይ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ማድረጌ ነው:: ምን ለማለት ነው ድሮ ኮሚኒስት ነብርኩኝ አሁን አይደለሁም ድሮ እግዚአብሔርን አላውቅም ባይ ነብርኩ:: የእየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠራ መስማት አልፈልግም ነበር አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ሆኛለሁ እግዚአብሔርን የማምንና የማመልክ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኛለሁ:: ድሮ በአመፅ የማምን ሰው ነበርኩኝ በአመፅ ለውጥ ይመጣል የሚል እምነት ስለነበረኝ እንደምታውቀው በዚያም ታግያለሁ:: አሁን ይህንን አላምንም በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን አመፅ እውነተኛ ለውጥ ያመጣል የሚል እምነት አሁን የለኝም:: ሲመች በአመፅ ሳይመች በሰላማዊ ሁኔታ የሚለውንም ጭምር አላምንም ድሮ ራሴ የያዝኩትን አስተሳሰብ እንደትክክለኛ መቁጠር የሌላውን አስተሳሰብ ስህተት አደርጌ እመለከት ነበር አሁን ግን ብዙ ስለተማርኩኝ ሌላውንም ማድነቅና መስማት ችያለሁ:: እነዚህ እነዚህ ለውጦች ስላሉኝ በነዚህ አንፃር ነው የምንነጋገረው::*

**በአንድ ወቅት ለፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ደርግን ለመጣል ያካሄድኩት የ15 አመት ትግል አሁንም አይቆጨኝም ወደ ፊትም አይቆጨኝም የሚል ነገር ገልፀው ነበር የአሁኑ አቋምዎትን ከያኔው ጋር ቢያነፃፅሩት?**

*ያኔ እንዲህ ያልኩበት ጊዜ በመሰረቱ ለህዝብ ነው የታገልኩት:: ህዝብ መልካም ሁኔታ እንዲያገኝ ነውና ለዚሁ ዓላማ የከፈልኩት ዋጋ አሁንም አይቆጨኝም:: ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ በዚያን ጊዜ ከነበሩት ውስጥ እግዚአብሔርን መካዴ ያሳዝነኛል:: የዛኔ እንደአሁኑ እግዚአብሔርን የማውቅ ሰው ብሆን ኖሮ አሁን የበለጠ ደስታ ይሰማኝ ነበር:: ወደኋላ ተመልሰህ ልታስተካክል የምትችለው ትልቅ ነገር ምንድነው ብለህ ብትጠይቀኝ በአንደኛነት አስተካክለዋለሁ ብየ የምለው ኮሚኒዝም የሚባለውን ነገር ትቼ እግዚአብሔርን ማመን የሚለውን እከተል ነበር:: ይህንን ማለቴ ነው ግን አሁንም ደግሞ ህዝብ ጥሩ ነገር እንዲያገኝ ፍቅር እንዲኖረው ሰላም እንዲያገኝ እንድነት እንዲኖረው አሁንም እለምናለሁ:: እንዴት ያግኝ የሚለው ላይ ነው ለውጡ ያለው::*

**እንደሚታወቀው 12 አመት በእስራት አሳልፈዋል:: 15 አመት ደግሞ በትግል እነዚህ የተለያዩና በጣም ተቃራኒ የሆኑ ሁለት ፈተናዎች ቢያነፃፅሩልኝ ከባዱስ የትኛው ነበር?**

*ሁለቱም ከባድ ናቸው:: ነገር ግን ሁለቱም የየራሳቸው የክብደት ባህሪ አላቸው:: ሁለቱም ደግሞ አስተማሪዎች ናቸው:: የትምህርታቸውም አይነት ይለያያል ለእኔም ሆነ ለሚሰማው ማንም ሰው እጅግ ከባድ ነው:: 15 አመት በረሀ 12 አመት እስር ቤት 27 አመት አሁን ደግሞ 54 አመቴ ነው:: እና እንደው ነፍስ ካወቅኩ ከ18 አመቴ እንኳን ጀምረህ ብትቀናንሰው የመከራው ጊዜ ሳይበልጥ አይቀርም በተለይ ደግሞ የወጣትነት ጊዜ የሚባለው አለ በተለይ ያ ወቅት በብዙ መከራዎች ውስጥ ነው ያለፈው ለሰው ላይገባው ይችል ይሆናል ግን እኔ 12 አመት መታሰሬ ልዩ ሊሆን ይችላል ከትግሉ ጋር ሲታይ ግን እኔን ጠቀመኝ እንጂ አልጐዳኝም ይህ ነግር ምናልባት ለእናንተም ግራ ሊገባችሁ ይችላል:: እስር ቤት ለማንም አልመኝም:: ማንም እንዲታሰር አልመኝም:: ግን ደግሞ መፀሀፍ ቅዱስ ምን ይላል «እግዛብሔር ለክፉ የሆነውን ነገር ወደ በጎ ይለውጣል» ይላል:: ለእኔ ይህንን ከፉ ነገር እግአብሔር ወደ በጎ ለውጦልኛል ብዬ ስለማምን ነው ይህን ያልኩት ሁለተኛ ምናልባትም እኔ ልረዳው በማልችለው መንገድ ከአንዳንድ ነገሮችም ሊያርቀኝ ፈልጎ ነው ብዬ አምናለሁ:: ስለዚህ የእስር ቤቱ ጊዜ*

ረጅም ነው ከባድም ስለሆነ ለማንም የሚመኙት አይደለም እኔም ብሆን መታሰር ትመኛ ለህ ወይ ብባል አልመኘም ነው መልሴ:: ግን ቢሆንም ደግሞ ለእኔ ትልቅ ጠቀሜታ ነው ያስገኘልኝ:: ጠቅሞኛል ብዬም ነው የማምነው:: በአካል እንደዚህ ተለውጠሀል የሚባለው ቅድም እንዳልኳችሁ እነዚህን ለውጦች ያገኘሁት እስር ቤት ውስጥ ነው:: ለዚህ ነው ጠቅሞኛል የምለው እና እንደዚያ ነው የማየው::

**ከዚያ በፊትስ የነበረው 15 አመት?**

ከዚያ በፊት የነበረው 15 ዓመት በተደባለቀ ስሜት ነው የማየው አንደኛው ስሜት ቅድም ያልኳችሁ ልለውጠው የምፈልገው ነገር በውስጡ ቢኖርም ለህዝብ ብዬ ያደረግኩት ስለሆነ መልካም ጐኑ የሚያመዝን ይመስለኛል እነዚህን ሁለት ወቅቶች ጠቅለል አድርጌ ስመለከት 27 አመት በጣም ትልቅ የህይወት ልምድና ተሞክሮ ተማርኩኝ ነው የምለው እኔ እንደሚመስለኝ ባለፉት 27 አመታት ከሰራኋቸው ነገሮች ይልቅ ከዚህ በኋላ የምሰራው ስራ የሚበልጥ ይመስለኛል ሳስበው:: አሁን በያዝኩት ሀሳብ ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜ ነው የበለጠ የምሰራው የሚል አቋም አለኝ ይህም የሚሆነው በሁለት መስኮች ነው አንደኛውና ዋናው መስክ ይህንን እምነት ይገፔ ኢየሱስ ክርስቶስን ማገልገል እፈልጋለሁ ፖለቲከኛው ታምራት የክርስቶስ አገልጋይ ሆነ ብለህ ብትፅፍ ደስ ይለኛል:: (ሣ.....ቅ) ከዚህ በኋላ ስለ እግዛብሔር ማስተማር እፈልጋለሁ ይህንን አምላክ ሰዎች እንዲያገኙት በእውነት እፈልጋለሁ:: አንተም ጭምር ማለቴ ነው:: በእርግጥ አንተ በምን እምነት ላይ እንዳለህ አላውቅም ግን በበኩሌ ማንንም ጌታን አግኙ ከማለት አላርፍም እባካችሁ ኢየሱስ ክርስቶስን እመኑ ነው ጥሪዬ በነገራችን ላይ ክርስትና የሀይማኖተኝነት ጉዳይ አይደለም:: በመሰረቱ የህይወት መንገድ ጉዳይ ነው:: ህይወትን እንዴት መምራት እንዳለብን የሚያሳይና የሚያስተምር እይታ ነው ክርስትና ማለት ብዙዎች እንደሚረዱት ዝም ብሎ ሀይማኖት በማለት አንዳንድ ነገሮችን የመስራት የመፈፀም ወይም ያለመፈፀም የህግ ጉዳይ አይደለም ለዚህ ነው መፀሀፍ ቅዱስን የወደድኩት ለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስን የወደድኩት እርሱም ቢሆን እኔን መከተል ሀይማኖተኝነት ነው አይደለም ያለው:: «እኔን መከተል እውነተኛውን የህይወት መንገድ ማግኘት ማለት ነው» ነው ያለው:: ሰው ሁሉ ደግሞ ይህንን እውነተኛ መንገድ ቢያገኘው በጣም እመኛለሁ:: የቀድሞ ጓደቼ እንኳ ይህንን እንዲያገኙት ነው የምጥረው:: ይህንን መንገድ እንዲያገኙ ነው የምፀልየው እስር ቤት ሆኜም እፀልይላቸው ነበር አሁንም እፀልይላቸዋለሁ::

**ለመሆኑ ወደዚህ የህይወት መስመር ለመግባት ምክንያቶችዎ ምንድናቸው? መቼም አንድ ነገር መነሻ አለውና**

አዎ አለው! በትክክል መነሻ አለው ወደዚህ ህይወት መንገድ ለመግባት ዋናው መነሻ ያው እስር ቤት ነው ብያችኋለሁ:: ይሄንን መንገድ የያዝኩት እስር ቤት ውስጥ ነው አሁን ይህንን መንገድ ከያዝኩኝ የፊታችን ጥር ሰባት አመት ሊሞላኝ ነው:: ከዚያ በፊት ያለውን አምስት አመት በዚያው በድሮው ስሜት ውስጥ ስንገዳገድ ነው ያሳለፍኩት:: ዋናው ምክንያት ምን መሰለህ ራስህን መመርመር ነው እስር ቤት ስገባ ራሴን መመርመር ጀመርኩኝ የመጀመሪያው የሚመስለኝ ደግሞ እሱ ነገር ነው:: ወደ ውጭ ከማየትህ በፊት ራስህን ወደ ውስጥ እይ:: የት ነው ያለሁት ብሎ እራስን ማየት ጥሩ ነገር ነው:: እኔ ከዚህ ነው የጀመርኩት:: ከዚህ የጀመርኩበት ምክንያት ደግሞ መታሰሬ ነው:: መታሰሬ ራሱ ያሳደረብኝ ተፅዕኖ አለ:: ይሄ ምንም ጥያቄ የለውም ስለዚህ የእኔ መንገድ ምንድነው ብለህ ራስህን ትጠይቃለህ:: መጠየቅ ግድ ነው በእንደዘህ አይነት ጊዜ ውስጥ ሁሌም ጥያቄ ታነሳለህ:: ምናልባት አንተም እዛ እያለህ ሞክረኸው ይሆናል:: ሣ...ቅ

**እርስዎ እስር ቤት በቆዩባቸው 12 አመታት ውስጥ ብዙ አገራዊና ፖለቲንዊ ክስተቶች ተፈጥረዋል:: ለምሳሌ የኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ነው አንዱ:: እዛ ሆነው ይህን ሲሰሙ ምን ተሰማዎት?**

የኢትዮ- ኤርትራን ጦርነት ስላነሳህልኝ ደስ ይለኛል ስሰማ በጣም ነው ያዘንኩት ምክንያቱም የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ወደ እንደዚህ አይነት ጦርነት ውስጥ ይገባል ብዬ አላስብም ነበር። ከዚያ ሁኔታ በኋላ በቃ ተለያይተናልና ሁላችንም በየራሳችን ሰላም እንቀጥላለን የሚል እምነት ነበረኝ። ግን ጦርነቱን ስሰማ በጣም ነው ያዘንኩት እንግዲህ እኔ እስር ቤት ነውና የነበርኩት ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ባልገባ ነው የሚሻለኝ ግን ቀደም ሲል ካነሳሁላችሁ አስተሳሰብ አንፃር የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እንዴት ይፈታ ብላችሁ ብትጠይቁኝ ያለፈውን እንተወውና የወደፊቱን ቢያስቡት ነው የሚሻል የሚመስለኝ። መፀሀፍ ቅዱስም ያለፈውን እየረሳህ ወደፊት መራመድ እንደሚሻል ነው እያስተማረኝ ያለው። እናም የኢትዮ- ኤርትራም ጦርነት የሚፈታው በፍቅር ነው ባይ ነኝ። ይሄ ፍቅር የሚለው ምን ማለት ነው ምናልባት መፅሀፉ ላይ አወጣው ይሆናል። ግን ጠቅለል አድርጌ ስነግራችሁ ምን ማለቴ ነው። ማንኛውም ወገን በሀይል ሊፈታው አይችልም ብዬ ነው የማምነው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ደግሞ ብዙዎቹም ይሉታል በብዙ ነገር የተሳሰረ ነው። ይሄ ህዝብ ከዚህ በኋላ ብዙ አመታት ቢቆይ እንኳን ተለያይቶ ይቀራል ብዬ አላምንም ተመልሶ አንድ ይሆናል የሚል እጅግ ጠንካራ እምነት አለኝ። በተለይ ከእስር ቤት ቆይታዬ በኋላ ይሄ እምነቴ በጣም ጨምሯል። ስለዚህ ይሄ ህዝብ ተመልሶ አንድ ለመሆን የሚያስችለውን ፍቅር ለማግኘት እኛም ደግሞ ከኤርትራም ሆነ ከኢትዮጵያ ወገን ሀላፊነት አለብን ስለዚህ ውጤት ሊያመጣ የሚችለው የፍቅር መንገድ እንዲይዝ ማስተማር አለብን። ሁሉም በዚህ መንገድ ነው ማሰብ ያለብን። ይህ የፍቅር አንድነት መንገድ እንዳልኩት ደረጃዎች ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን ይሄ ህዝብ ተመልሶ አንድ የሚሆንበት መንገድ በዛ ብቻ ነው የሚፈታው የሚል እምነት ነው ያለኝ። ይሄ ደግሞ ይሆናል። በታሪክም አይተናል። ዝም ብሎ ትምኒታዊ አይደለም። ምስራቅና ምዕራብ ጀርመን ሊዋሀዱ ይችላሉ ብሎ ያሰበ በጭራሽ አልነበረም ቻይናና ታይዋን ምናልባት በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንዳንድ ጥሩ ጥሩ እርምጃዎች ይወስዱ ይሆናል። ሌላው ቀርቶ እነ ኮሪያ እንኳን ተስፋ የሚቆረጥባቸው አይደሉም። እንደውም ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው የኢትዮጵየና የኤርትራ ህዝብ ገመድ ደግሞ አሁን ከላይ ከጠቀስኳቸው ህዝቦች ገመድ ምናልባት ከአንዳንዶቹ ይበልጥ ይሆናል እንጂ የሚያንስበት ምክንያት የለም። የብዙ ሺህ አመት የጋራ ታሪክ አለ። ስለዚህ የማይመጡበት ምክኒያት የለም ደግሞ ይመጣሉ የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ በዚህ መንገድ ብቻ ይፈታል ብዬ ነው የማምነው ይህም የፍቅር መንገድ ነው።

***በ1993 ዓ.ም በቀድሞ ጓዶችዎ መካከል የተፈጠረውን የሀሳብ ልዩነትስ ሲሰሙ ምን ተሰማዎት? በተለይ ደግሞ ከዚያ በኋላ እነ አቶ ስዬ እርስዎ ያሉበት እስር ቤት ድረስ ሲመጡ ሁኔታውን በምን መልኩ አዩት?***

ቅድም እንዳልኳችሁ ነው። እኔ ያለፈ ነገር ላይ ማውራት አልፈልግም። ከዚህ በኋላም ቢሆን የሚያስፈልገው ፍቅር ነው። ለእነርሱ ብቻ አይደለም፤ ለእነ ስዬና ለሌሎች ብቻ አይደለም። እኔ ነገሮችን እንዲህ አጥብቤ መመልከት አልፈልግም። ምክንያቱም እናንተ ያነሳችሁልኝ ሁለት ጉዳዮች ብቻ አይደሉም ያሉት፤ ሌሎችም ጉዳዮች እኮ አሉ። ለምንድነው ከዛ ውስጥ ይኼ ብቻ ወጥቶ የሚታየው። አሁንም እንዲህ ነው የሚያዋጣው የለም እንዲያ ነው የሚል ነገር ይነሳል። በአመፅ መደራጀት ነው የሚያዋጣው የሚሉ ሀይሎች አሉ አይደለም? እኔስ ራሴ አለሁ አይደል?
እኔ ታሰርኩ። በታሰርኩበት ጊዜ ተበሳጨሁ። መበሳጨት ብቻ አይደለም ቂም ሁሉ ይዤ ነበር። ምንም ማድረግ የማልችል ቢሆንም የያዝኩት ቂም የበቀልም ጭምር ነበር። እንዴት እንዲህ ይሆናል የሚል ዓይነት እልህም ይዞኝ ነበር።
በኋላ ግን ነገሬ ሁሉ በእግዚአብሔር ሲለወጥ ተውኩት። የሆነው ሁሉ ሆነ። በዛ በሆነው ነገር ሰውንም ሀገርንም መገንባት አይቻልም፤ እሱን ይዘህ ብታላዝን የትም አትደርስም ብዬ አመንኩ። ለወደፊቱ ምን ላድርግ ብዬ ጠየቅሁ። በመጀመሪያ የወሰድኩት እርምጃ ለምን ታሰርኩ በሚል የያዝኩትን ቂምና ጥላቻ ለመተው መወሰን ነው። እናም ተውኩት። ጥላቻም ቂምም በማንም ላይ አላሳድርም፤ ፍቅር ይሻለኛል አልኩ። ይኼ ለእኔ ፈውስ ነው የሆነልኝ።
ማንም መጥቶ ስለ እገሌ፤ ስለ እገሌ ስለፓርቲ ቢጠይቀኝ መጀመሪያ እግዚአብሔርን፣ እመን ቀጥሎ ሌላውን ወንድምህን አፍቅር፤ ከዛ በኋላ ነገሮች ሁሉ ይፈታሉ ብዬ ነው

የምነግረው:: ለእናንተም ይኼንኑ ነው የምላችሁ:: ሌላ ምንም ነገር አይፈታውም:: ደግሞም በዚህ እምነቴ ፅኑ ነው:: ሁሉን ነገር የሚፈታው ፍቅር ነው:: በቃ! ሰዎች እንዴት ይህንን ፍቅር እናግኝ ብለው ራሳቸውን ይመርምሩ:: ማንም ይሁን ማን!

***ምርጫ 97 ሲካሄድ እስር ቤት ነበሩና ምርጫ 97ን «አመለጠኝ»? ወይስ «አመለጥኩት» ነው የሚሉት?***

ሁለቱንም አልልም:: እስር ቤት ነው ያለሁትና ምርጫ አልመረጥ ነገር:: ደግሞም በህገ መንግስታችን እስረኛ አይመርጥም አይደል!?

***እንደው ውጭ ብሆን ኖሮ ብለው አላሰቡም?***

ይቅርታ አድርግልኝና እንዲህ ብሆን ኖሮ እንዲህ አደርግ ነበር የሚል አስተሳሰብ በጭራሽ ተሰምቶኝ አያውቅም:: ለምን መሰለህ? አይሆንማ በቃ! አልሆነም አልሆነም:: ውጪ አይደለሁም፤ አይደለሁም::

***ለ15 ዓመት ትግል አድርገው ለድል በቅተዋል:: በኋላ ደግሞ ተከሰው ፍ/ቤት ቀርበዋል፤ ተፈርዶብዎታል:: እንዴት ነበር የፍርዱስ ሂደት?***

አሁንም ወደኋላ እየመለስከኝ ነው:: ልናገር የምችለው ብዙ ነገር ቢኖር እንኳ አይጠቅምም:: አለፈ በቃ:: ይኼንን የምልህ በጭራሽ አትጠይቀኝ ለማለት አይደለም:: ለምን ባለፈ ጉዳይ ላይ ጊዜዬንስ አጠፋለሁ? ለምንስ አዕምሮዬን በዛ ጉዳይ አስጨንቃለሁ::
ጉዳዩ የኢንተርቪው ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ የፖሊሲ ቀረፃ ቢሆን፤ ወደፊት የፍትህ ራዕያችን ምን ይሁን? ካለፈውስ ምን እንማር? አይነት ቢሆን ኖሮ፤ እንዲህ እንዲህ ነበር፤ እንዲህ እንዲህ ይደረግ ማለት ይቻል ነበር:: አሁን ግን ምን ይጠቅማል?

**እንደው ከእግዚአብሄር ቃል አንጻርስ ስለአገራችን ፍትህ ምን ይላሉ?**

እግዚአብሔርማ ፍትህን አታጓድሉ ይላል:: በመፅሐፍ ቅዱስ ከትላልቆቹ የእግዚአብሔር ቃል ዋና ዋና መመሪያዎች አንዱ ፍትህ ነው:: እንደውም መፅሐፈ ምሳሌ ውስጥ ፍትህ ሲጓደል አገር አይረጋጋም የሚል ጥቅስ አለ:: ይኼንን አምናለሁ:: ፍትህ አንድ ቁልፍ መሳሪያ እንደሆነ አምናለሁ:: የእግዚአብሔር ቃልም ስለሆነ እናገረዋለሁ::

***ይኼንን ነገር እንድናየው ምንድነው የሚያስፈልገው?***

የሚያስፈልገውማ ፍ..ቅ..ር! ነዋ:: ከምሬ ነው:: ዳኞቹም ፍቅር ይኑራቸው:: ህዝቡም ፍቅር ይኑረው! በፍትህ ጉዳይ ላይ የሚመጣ ሁሉ ፍቅር ይኑረው:: ፍቅር ቢኖር እኮ ይሄ ሁሉ ነገር አይነሳም:: የእኔ እምነት ይኼ ነው:: ስለ ፍቅር ብናስብ እናንተ የምታነሱት ነገር መጀመሪያውኑ አይነሳም:: እንዲህ ሆነ እንዲያ ሆነ የሚባለውና እናንተም የምትሉት እኮ በሬዲዮም በምንም እሰማለሁ:: ያንን መድገም አያቅተኝም:: እሱ አይደለም ቁም ነገሩ:: ከዚህ አድማስ ወጥቻለሁ:: እኔ የምለው ምን መሰለህ? ሁሉም በያለበት መንግስትም በለው፣ ህዝብም በለው፣ እኛም፣ እናንተ ጋዜጠኞችም ጭምር፣ ማንም ሰው ቁጭ ብሎ ስለ ፍቅር ከልቡ ያስብ:: ፍቅር ማለት እግዚአብሔርን ማወቅ፤ እግዚአብሔርን መፍራት ነው መጀመሪያው:: እግዚአብሔርን ካልፈራህ ነገር ይበላሻል:: እኔ እግዘአብሔርን አልፈራም ነበር:: ከዛ ቀጥሎ የሚመጣው አንተን በፍቅር መውደድ፤ በፍቅር ስወድህ ደግሞ በሙሉ ልቤ ነው::
በሙሉ ልብህ ሰውን ከወደድህ ምን ልታደርግ ሌላ ነገር ውስጥ ትገባለህ:: የሀሳብ ልዩነት ሊኖር ይችላል:: ምን ልታደርግ ከዛ በላይ ለማለፍ ትሞክራለህ? ትወደዋለህ ማለት እኮ ነው::
እኔ ባለፈው ከእስር ስወጣ «እግዚአብሔር በፍቅር እንውደድ፤ ኢትዮጵያን በፍቅር እናሳድጋት» ያልኩት ለዚህ ነው:: አሁን ካለው ድባብ እስቲ ወጣ እንበል:: እስቲ ለየት

ያለ ነገር እንስራ:: እኔ ከእግዚአብሔር ቃልና ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት አንፃር ለየት የለ ነገር ለማየት ሞክሬአለሁ:: ሌሎች ደግሞ ከራሳቸው ምልከታ አንፃር ይነሱ:: እናንተም ተነሱ:: ፖለቲከኛውም ይነሳ:: ግን እስቲ ለየት ይበል:: ለየት ያሉ መፍትሔዎች፣ አቅጣጫዎችና መንገዶች ይዞ ይምጣ:: ለዚህ ነው በመጀመሪያ እምነቴን ላሳያችሁ የተነሳኹት::

**ክርስቲያን ያልሆኑና የሌላ እምነት ተከታይ የሆኑ ወገኖቻችንስ በዚህ አስተሳሰብ ጥላ ስር ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው?**

*አሁን ጥሩ ጥያቄ አመጣህ:: የእኔ እምነት ክርስትና ስለሆነ እንጂ ሌሎቹ እምነቶች ዋጋ የላቸውም ማለቴ አይደለም:: ለዚህም አስተዋፅኦ የላቸውም ማለቴ አይደለም:: ብዙዎቹ እምነቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እኮ ተመሳሳይ ናቸው::*

በነገራችን ላይ እኔ የእስልምና ሃይማኖት መመሪያ የሆነውን ቁርአን አንብቤአለሁ:: ጠልቄ ባላውቀውም በተወሰነ ደረጃ ተረድቼዋለሁ:: ቢያንስ እስር ቤት ሆኜ አንብቤዋለሁ:: በተመጠነች ደረጃ ቁርአንን አወቀዋለሁ:: በዛች በተመጠነች ደረጃ ባለኝ ዕውቀት እኔ ከምለው ነገር ጋር ይጋጫል ብዬ አላምንም:: ሰላም፤ ፍቅር ይሁን ይላል:: ብዙዎቹም እንደዛው:: አንድ ላይ እንሁን፤ ይኼንን ነገር እናራምድ ማለቴ ነው:: ስለዚህ እምነቶች የሚለያዩበት ነገር ቢኖር እንኳ የሚስማሙባቸው ነገሮች አሉ ማለቴ ነው:: ይኼንን ጥያቄ ስላነሳህ በጣም አመሰግናለሁ::

***ታዲያ ይህንን አመለካከት እንዴት ነው ወደ ህብረተሰቡ ማድረስ የሚቻለው?***

እንዳልኩህ እየተጠነቀቅሁ ነው:: እግረ መንገዴን ሰዎችን በምላሴ፣ በንግግሬ እንዳልጎንጥ:: መጀመሪያ ነገር እኔ ከማምንበት እምነት አንፃር አንድ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ያለ ይመስለኛል:: ከኢየሱስ ክርስቶስ አንፃር ይኼን እምነቴን ሰዎች እንዴት ሊረዱት ይገባል? የሚለው ይቀድማል::

ቅድም እንዳልኩት የኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ የኃይማኖት መንገድ ብቻ አይደለም:: ምን ማለቴ መሰለህ? የሀይማኖት መንገድ ሲባል ትፆማለህ፣ ትፀልያለህ፣ ቤተክርስቲያን መሄድ ብቻ አይደለም:: ዋናው የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱ ራሱ ሲመረመር ፆማችሁ፣ ፀሎታችሁ፣ መስዋዕታችሁ፣ ቁርባናችሁ፣ ምናምናችሁ ለኔ ምኔም አይደለም የሚል ነው:: መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ መፅሐፈ ኢሳያስን እዩ:: ምዕራፍ 58 «እነኚህ ሁሉ ለኔ ምኔም አይደሉም፤ እኔን ማመን ማለት ይኼ አይደለም:: እኔ እውነተኛ የህይወት መንገድ ነኝ» ነው የሚለው::

የህይወት መንገድ ምንድነው? እንዴት እንደምትኖር፣ እንዴት ግንኙነት እንደምትፈጥር፣ ከራስህ ጋር፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደምትኖር፣ ህብረተሰብን እንዴት እንደምትገነባ ማወቅ ማለት ነው::

ሶሻሊዝም፣ ኮሚኒዝም፤ ሊብራል ዲሞክራሲ፣ሶሻል ዲሞክራሲ፣ ሪቮሉሽነሪ ዲሞክራሲ ወዘተ የሚባሉት ሁሉ ከመምጣታቸው በፊት ህብረተሰብ እንዴት ይገንባ፤ እንዴት ይያዝ የሚሉት ነገሮች በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፈዋል:: ሰዉ በዚህ ላይ አይኑን ማሳረፍ ነው ያልቻለው:: የቻለ ችሏል፤ እሱን ማለቴ አይደለም:: ያልቻለ ግን ይቻል:: በዚህ እምነት ውስጥ ስለገባሁ ነው እንዲህ ዓይነት ለውጥ ያመጣሁት::

ፍትህ እንዴት እንደምትሰጥ፤ ህዝብን እንዴት እንደምታስተዳድር... ወዘተ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ:: በነገራችን ላይ አብዛኞቹ ፍልስፍናዎች ከመፅሃፍ ቅዱስ ተወስደው ነው እገሌ ፍሎዞፊ፤ እገሌ ፖለቲክስ ምናምን የተባለው:: ስለዚህ መጀመሪያ ነገር ወደ እግዚአብሔር እንዙር:: እሱ ራሱ ይነግረናል:: የሚቀድመው ይኼ ነው:: እኔ ይኼን አድርጌአለሁ:: ገና ያልበሰልኩ ብሆንም መንገዱን ይዤዋለሁ ብዬ አምናለሁ::

ይኼ ማለት አገሪቷ የሀይማኖት ትሁን፤ መንግስት የኃይማኖት ይሁን ማለት አይደለም:: በዚህ መልኩ ሰው እንዳይረዳኝ እለምናለሁ:: ከዚህ በተረፈ በኔ በኩል በተቻለኝ መጠን፤ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ይኼን ነገር አስተምራለሁ::

በነገራችን ላይ ዛሬ (ከትናንት በስቲያ ዕሁድ ማለት ነው) ቤተክርስቲያን ሄጄ ነበር:: በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያን ዛሬ ሄጄ እግዚአብሔርን አመለክሁ:: እኔም

እማራለሁ፤ በእንደዛ ዓይነት መድረኮች ላይ ደግሞ አስተምራለሁ:: ትልቁ ስራዬ ይኼ ነው የሚሆነው::

*በቃ ከእንግዲህ ፖለቲካ ውስጥ አይገቡም ማለት ነው አቶ ታምራት?*

ከእንግዲህ በድርጅት መልክ ፖለቲካ ውስጥ አልገባም:: በድርጅት መልክ ያልኩበት ምክንያት ምንድነው? አንዳንድ ጊዜ ማህበራዊ ህይወት በራሳቸው ፖለቲካዊ መሆን ሲችሉ አስተያየት ይኖረኛል:: በሚነሱ ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ እንደማንኛውም ሰው አስተያየት ይኖረኛል:: እነዛን አስተያየቶቼን እንደየአግባቡ እሰነዝራለሁ:: ሀሳብ እሰጣለሁ:: አስተምራለሁ:: ይህንን ሳደርግ ደግሞ ወገን አልለይም:: ከእገሌ ጋር እንዲህ ልሁን፤ ከእገሌ ጋር እንዲህ ላድርግ፤ እገሌ እገሌ በሚባለው፤ እስካሁን ያለው የክፍፍል ጐራ ውስጥ አልገባም:: ከሁሉ አስቀድሞ ለሰው ልጅ ሁሉ ክብር አለኝ:: ማንንም ቢሆን አከብራለሁ:: ቀድም እንዳልኩት ጥላቻ፣ ቂም በቀል የሚባለውን እግዚአብሐር አንስቶልኛል:: ከዚህ በፊት እንዲህ ሰራኝ፣ እንዲህ አደረገኝ፣ እናንተን ባይጨምርም እንዲህ ፃፋችሁብኝ (ከዚህ በፊት ብዙ ጋዜጦች ሲፅፉብኝ ነበር) እነሱን ሁሉ በአጠቃላይ ማንንም አልኮንንም:: አልወቅስም:: እወዳችኋለሁ:: እንደኔ እህቴ ነሽ፤ ወንድሜ ነህና እባካችሁ ይህቺን አገር በፍቅር እናሳድግ ወደሚል እምነት ነው የመጣሁት:: ሰው ሁሉ እንዲህ ቢሆን እንዴት እመኛለሁ መሰለህ:: ከዚህ ጐን ለጐን ይኼንን ስራዬን ሊያራምዱና ሲቪል ማህበረሰብን ሊገነቡ የሚችሉ ከእምነቴ ጋር የማይጋጩ ስራዎች ብዙ አሉ:: በእንደዛም አይነት መድረኮች ገብቼ አስተምራለሁ:: የማስተምረው ስለፍቅር ነው:: በቃ!! ህይወቴ ይኼ ነው የሚሆነው::

**እጅግ እናመሰግናለን::**

# «ከአመራርነት እንጂ ከፓርቲ አባልነት አልለቀቅሁም»

*ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም*

***ሰሞኑን የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም ለፓርቲያቸው የመልቀቂያ ደብዳቤ እንዳቀረቡ በስፋት ተነግሯል:: ከአውራምባ ታይምስ ወንድራድ ደብረጽዮንና ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን በዚህና ሌሎች ተያያዥ ርዕሶች ዙሪያ ከዶክተር ያዕቆብ ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል::***

***ውይይታችንን ለመጀመር፤ እርስዎ በአለም አቀፍ ፍ/ቤት በዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ የመሰረቱባቸው የቀድሞው የሩዋንዳ ባለስልጣን ሰሞኑን ተፈርዶባቸዋል:: ስለክሱ መነሻ፣ ሂደትና ፍርድ በጥቂቱ ሊነግሩን ይችላሉ?***

አዎ! የሩዋንዳው ዘር ማጥፋት ዋና አቀንቃኝ የሆነው ባጐሶራ ባለፈው ሳምንት ተፈርዶበታል:: ሰውየው የዘር ማጥፋቱን ተግባር የመራ ነው::
በወቅቱ የሩዋንዳ ፕሬዝዳንት ሀቢያራማና ካጋሜ ከሚመራው አርበኞች ግንባር ጋር በታንዛንያ ተደራድሮ ሲመለስ አውሮፕላኑን በሚሳይል ጣሉት:: ይህ የሆነው አፕሪል 6/1994 ነው:: እዛ አውሮፕላን ውስጥ የብሩንዲም ፕሬዝዳንት ነበሩ:: ሁለቱም ሞቱ:: አውሮፕላኑ በተመታ በ1 ሰዓት ውስጥ ቱትሲዎችን የማጥፋት ዘመቻ ተጀመረ:: አስቀድሞ በታቀደ ሁኔታ ነው ጭፍጨፋው የተካሄደው:: የፕሬዝዳንቱን አውሮፕላን ማን እንዳጋየው እስካሁን አልታወቀም::
ባጐሶራ የሩዋንዳን ጠ/ሚ/ር (ሴት ናት) ገድሎ ወዲያውኑ ስልጣን ተቆናጠጠ:: ከዚያ ዘር ማጥፋቱን በበላይነት መራ:: ወደ 800 ሺ ሰዎች ለእልቂት ተዳረጉ:: እንደሩዋንዳውያን

ስሌት ከ1 ሚሊዬን በላይ ሰው እንዳለቀ ነው የሚነገረው:: ባለፈው ሳምንት የተፈረደበትን ባጉሰራ ክስ የመሰረትኩበት እኔ ነኝ:: ሰውየው ፈርጠምጠም ያለ ወፍራም ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ ፍ/ቤት ሲቀርብ «በ48 ሰዓት ፍ/ቤት መቅረብ ሲገባኝ አልቀረብኩም፤ ጊዜው ተራዝሟልና ልከሰስ አይገባም» ብሎ ተቃውሞ ነበር:: እኔ በ48 ሰዓት ያልቀረበበትን ምክንያት በበቂ ሁኔታ አስረድቼ ክሱ ቀጠለ::

ሩዋንዳ አሩሲ ክፍለ ሀገርን ነው የምታክለው:: 12 ሚሊዮን ህዝብ አላት:: 85 በመቶ የሚሆኑት ሁቱዎች፤ 15 በመቶ የሚሆኑት ቱትሲዎች ናቸው:: ለዘር ማጥፋቱ መንስኤ የሆነው የህብረተሰቡ አወቃቀር ነው:: ሩዋንዳ ከቤልጅየም ቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጣችው እ.ኤ.አ 1962 ዓ.ም ነው:: በዚያ ወቅት ቤልጅየሞቹ የሚያቀርቧቸው እና ከበሬታ የሚሰጡት ቆዳቸው ነጣ፣ አፍንጫቸው ሰልክክ ላለው ለቱትሲዎች ነው:: የስልጣን ውክልናም የሚሰጧቸው ለቱትሲዎች ነበር:: ቤልጅየሞች ሲወጡ 85 በመቶ የሚሆኑት ሁቱዎች ስልጣን ያዙ:: ነገሩ ተገለበጠ:: ሁቱዎች ቱትሲዎችን ማስቃየት ጀመሩ:: ያኔ ቱትሲዎች ወደ ሩዋንዳ ተሰደዱ:: የዛሬው የሩዋንዳ መሪ ፖል ካጋሜ በወጣትነት ዘመኑ ወደ ኡጋንዳ ከሸሹት ቱትሲዎች አንዱ ነበር:: እንግዲህ የዘር ጭፍጨፋው አመጣጥ በአጭሩ ይኼን ይመስላል::

***እርስዎ በሩዋንዳ ዘር ማጥፋት የፈፀሙ ሰዎችን ክስ በዐቃቤ ህግነት ለመያዝ የቻሉት በምን መስፈርት ወይም ሁኔታ ነበር? ክስ ሲመሰርቱስ ማስረጃ ያሰባሰቡት እንዴት ነው?***

አሜሪካ አገር ዩኒቨርስቲ ውስጥ ህግ ለብዙ አመታት አስተምሬአለሁ:: የህግ ዕውቀትና መጠነኛ ተመክሮ ያለው ለዚህ ስራ እንደሚፈለግ ማስታወቂያ አይቼ አመለከትኩ:: በዚህ ሁኔታ ተመረጥኩና ጉዳዩን ያዝኩ::

ጉዳዩን ለመያዝ እንደተመረጥኩ ከአሜሪካ ተነስቼ በቀጥታ ወደ ሩዋንዳ ነው የሄድኩት:: ከዛ እንደ አንድ አቃቤ ህግ ባጉስራ ላይ ክስ ስመሰርት የፈፀመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው ወይስ አይደለም? በሰው ዘር ላይ የሚፈፅም ወንጀል ነው? «Crime against humanity» የጦር ወንጀል ፈፅሟል ወይ? የሚለውን ለይቼ ካወጣሁ በኋላ በዕድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ የሚጠይቅ ክስ ነው ያቀረብኩት:: ማስረጃ በማሰባሰብ በኩል ምንም ችግር አልነበረም:: አንድን ዘር ለማጥፋት ሆን ብለው፤ አቅደው መነሳታቸውን የሚያሳዩ በርካታ ሰነዶች፣ ቃለ ጉባኤዎች፣ ሌሎችም ማስረጃዎች ነበሩና::

***ሁቱዎች ቱትሲዎችን ከገደሉ በኋላ ወደ አገራችሁ ሂዱ እያሉ ሬሳቸውን ወንዝ ውስጥ ይከቱ እንደነበር አንብበናል፤ ሰምተናል:: ይህንን የዘር ማጥፋት ክስ የመሰረቱት እርሶዎ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነዎትና እዛ ቦታ ላይ መገኘት ምን ስሜት አሳድሮብዎት ነበር?***

በዚህ ጉዳይ ላይ እኔም አስቂኝ ነገር ገጥሞኛል:: ፍ/ቤት ቀርቤ ስከራከር የተከሳሹ ጠበቃ ያዕቆብ ይህን ክስ ሊመሰርት አይገባም፤ ገለልተኛ አይደለም ብሎ ለዳኛው አመለከተ:: ለምን ሲባል ኢትዮጵያዊ ነውና የሚል መልስ ሰጠ:: ዳኛው ተገርመው ኢትዮጵያዊ መሆን ከተከሳሾቹ ጋር ምን ግንኙነት አለው ብለው ሲጠይቁት ቱትሲዎች እኮ ኢትዮጵያዊያን ናቸው ነበር ያለው:: እና ዳኛው ጥያቄውን ውድቅ አደረጉት::
በእርግጥ አብዛኞቹ ቱትሲዎች ኢትዬጵያዊያን ነን ብለው ያምናሉ:: የፈለስነው ከኢትዮጵያ ነው ይላሉ:: ለኢትዮጵያም ለየት ያለ ፍቅር አላቸው:: የተከሳሹ ጠበቃ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም የሚል ክርክር ያነሳው በ4ኛ ደረጃ የምንፈልገው ካሪማራ የተባለ ተከሳሽ ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቱ እንደተሰማ ነው::

***እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ቻለ?***

እሱን እርግጠኛ አይደለሁም:: የዘር ጭፍጨፋው ካበቃ በኋላ ለብዙ ጊዜ ኪጋሊ ውስጥ ተደብቆ ቆየ:: ከዚያ ተሹለክልኮ ወደ ኢትዮጵያ ይገባና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ህንድ ያመራል:: ህንድ ሲደርስ ቪዛ አልነበረውምና የህንድ ባለስልጣናት መልሰው ኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ከተቱት:: አ/አበባ ከገባ በኋላ እንደለመደው ተሹለክልኮ ሊወጣ ሲል ደህንነቶች አድነው ያዙት:: ሲመረምሩት ካሪማራ ሆኖ ተገኘ::

የኢትዮጵያ ደህንነቶች እኛ ጋ ደውለው ሲጠይቁ የምንፈልገው ሰው ነውና የተመድ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፍ/ቤት ወዳለበት ታንዛኒያ እንዲልኩት ተጠየቀ። የሩዋንዳ መንግስትም ለኔ ስጡኝ ብሎ ጠየቀ። በዚህ መሀል የኢትዮጵያ መንግስት ሲያቅማማ ጐልድስቶን የሚባሉት ደቡብ አፍሪካዊ አለቃዬ እኔ አዲስ አበባ ሄጄ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ተነጋግሬ ተከሳሹን እንዳመጣ አዘውኝ ነበር።
ትዕዛዙ በተሰጠኝ በማግስቱ የኢትዮጵያ መንግስት ተከሳሹን ወደ ኪጋሊ ላከው። በዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈለግን ሰው ወደ ኪጋሊ የላከች ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ሌሎቹ ሀገሮች ወደ ተመድ ፍ/ቤት ታንዛኒያ ነው ተከሳሾችን የላኩት።
ሰውየው ኪጋሊ ውስጥ ፍ/ቤት ቀረበ። ከ22 ሰዎች ጋር ሞት ተፈረደበት። በነገራችን ላይ የኢህአዴግ መንግስትና የሩዋንዳ መንግስት ፍቅር መሰረቱ ይኼ ሳይሆን አየቀርም። ታስታውሱ እንደሆን ኢትዮጵያና ኤርትራ ወደ ጦርነት በገቡ የመጀመሪያ ሳምንት ከሁሉ በፊት አስታራቂ ሆና የመጣችው ሀገር ሩዋንዳ ናት። አሁንም የጠበቀ ወዳጅነት አላቸው።

***የዘር ማጥፋት ክስ ነገር ሲነሳ በወሬ ደረጃ የሰማነው ነገር ትዝ አለን። እርስዎ የደርግ ባለስልጣናት ላይ ልዩ አቃቤ ህግ ሆነው ክስ እንዲመሰርቱ በመንግስት ተጠይቀው ነበር ይባላል። ይኼ ምን ያህል ዕውነት ነው?***

ተጠይቄ ነበር። በወቅቱ አሜሪካ ዩኒቨርስቲ ውስጥ መምህር ነበርኩ። አንድ የመንግስት ባለስልጣን ስልክ ደውሎ «ይኼንን ጉዳይ በልዩ አቃቤ ህግነት እንድትይዝልን እንፈልጋለን» ብሎ ጠየቀኝ። እስቲ ላስብበት አልኩት። በሌላ ቀን መልሶ ሲደውል ይኼንን ጉዳይ የምቀበለው ሙሉ በሙሉ ነፃ የሆነ እንደሆነ ነው፣ ከበጀት በስተቀር ምንም አይነት መመሪያ ከመንግስት አልፈልግም፣ ሰራተኛ የምቀጥረው፣ ማን መከሰስ እንደሌለበት፣ ማን መከሰስ እንዳለበት የምንወስነው እኔና አብረውኝ የሚሰሩት ሰዎች ናቸው። ይኼን ሁኔታ የሚሟላልኝ ከሆነ እሺ እሰራለሁ አልኩ። ከዛ በኋላ እዚህ ላይ ቆመ። በነገራችን ላይ የደርግ ባለስልጣናት በዘር ማጥፋት ክስ መከሰስ አልነበረባቸውም። ይህንን ደጋግሜ ተናግሬአለሁ።

***የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲባል ምን ትዝ ይልዎታል?***

እንደምታውቀው! እኔ የዘር ማጥፋት ወንጀል ከሳሽም ተከሳሽም ሆኜ አይቼዋለሁ። እኛ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ፍርድ ብዙ ነገር ልንማር እንችላለን። የዘር ማጥፋት ወንጀል በፌዝ የሚታይ፣ እንዲሁ እንደዘበት ሰውን ለማስፈራራት፣ የፖለቲካ ባላንጣን ለማጥቃት የሚለጠፍ ተራ ወንጀል ተደርጐ መወሰድ የለበትም። በጣም ከባድ ወንጀል ነው። መንግስት ከመገልበጥም ህገ መንግስት ከመናድም በላይ የሆነ የከፋ ወንጀል ነው። የወንጀሎች ቁንጮ ነው።
እኛ በተከሰስን ጊዜ በጣም ያስቆጨኝ ያስከፋኝ ነገር ቢኖር በዘር ማጥፋት ወንጀል መከሰሳችን ነው። በእርግጥ የኋላ ኋላ የክሱን ፍሬ ከርስኪነት ተረድቶ መንግስት ክሱን አንስቷል፣ ለክሱ መነሳት ቅድም ከጠቀስኩልህ ደቡብ አፍሪካዊው አለቃዬ በኋላ አለቃዬ ሆና የተሾመችው አ/አበባ መጥታ ይኼ የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ አዋራጅ፣ ጥቅም የሌለው መሆኑን ማስረዳቷና ባለስልጣናትን ማሳመኗ ይታወቃል።
በመሰረቱ የዘር ማጥፋት መንስኤ ከሌላ ወንጀል መንስኤ በጣም የተለየ ነው። አንዱ ዘር ከሌላው የተለየ ጥቅም አግኝቷል የሚል ነው መነሻው። ለምሳሌ ያህል ቱትሲዎች የተጨፈጨፉት ሁቱዎች በኮሎኒያሊዝም ዘመን በጣም ይጠቀሙ ነበር። የስልጣን ውክልና ያገኙ ነበር። ንግድ በነሱ ዕጅ ነበር፣ ውትድርናው በነሱ እጅ ነበር። ትምህርት የሚማሩት እነሱ ነበሩ የሚል ነው መነሻው። ይኼ ይኼ ነገር እየቆየ ከፍተኛ ጥላቻ ፈጠረ። ጥላቻቸው ወሰን የሌለው ጥላቻ ነበር። በሰዎች መሀል ጥላቻ መፍጠር በጣም ቀላል ነው። ሰዎችን በዘር ማጣላትም በጣም ቀላል ነው።

***ካገኙት ትምህርትና ልምድ አንጻር ለአገርዎ ምን አገልግሎት ሰጥተዋል? ወይም ምን አድርገዋል?***

በዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ዐቃቤ ህግነት ለ2 ዓመታት እንደሰራሁ አስተምርበት የነበረው ዩኒቨርስቲ ወደ ስራህ ተመለስ ወይም ስራህን ልቀቅ ስላለኝ ዐቃቤ ህግነቱን ትቼ ወደ አሜሪካ ነው የሄድኩት::ከ3 ዓመት በኋላ ደግሞ የናይጄሪያና የካሜሩን የድንበር ጉዳይ በተመለከተ የተመድ የህግ አማካሪ ሆኜ ሰርቻለሁ:: በዚህ ጊዜ ጠ/ሚ/ር መለስ እንከን የለሽ ምርጫ እናካሂዳለን ብለው ቃል ሲገቡ ወደ ሀገሬ መጣሁ:: ከዛ በኋላ የሆነውን እናንተም ታውቃላችሁና መድገም አያስፈልግም::
እኔ ከተመድ የህግ አማካሪነት ስራዬን ለቅቄ ስመጣ በቀረችኝ ዕድሜ ሃገሬን ላገልግል ብዬ ነው:: አንድ የህግ ሰው ሊሰራ የሚችለውን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ:: ይኼ የሆነው በኢትዮጵያ ህዝብ ውለታ ነው:: ይህንን ውለታ ለመክፈል ነበር የመጣሁት:: ነገሩ እንዳልሆነ ሆነ::

***አሁን ያለው የፖለቲካ ድባብ እንዴት ይገመግሙታል? ተስፋ ሰጪ ነው?***

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት የሚያደፋፍርና የሚያዝናና አይደለም:: በተለይ ከ1997 ምርጫ በኋላ የፖለቲካው ሜዳ እየጠበበ፣ የፕሬስ ነፃነት እየተገደበ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ እየተደናቀፈ፣ የፓርቲዎች እንቅስቃሴም እየተገደበ ነው የሄደው:: ከ1997 በኋላ ወደፊት ከመሄድ ይልቅ ቀኝ ኋላ ዞረን ነው እየሄድን ያለነው:: ከ3ኛው ዓለም ሀገራት ጋር እንኳ ብንወዳደር ጥሩ ማርክ የምናገኝ አይመስለኝም:: ምናልባት ሰብዓዊ መብት ይጣስባቸዋል ከሚባሉ ሀገሮች ከቀዳሚዎቹ ተርታ ሳንመደብ አንቀርም:: ዲሞክራሲን በማቀጨጭ ደረጃ በቀዳሚነት ልንታይ እንችላለን::

***ታዲያ በእንዲህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ የፖለቲካ ትግሉን የመቀጠል ፅናትዎ እንዴት ነው?***

እኔ እንግዲህ ፅናቱ አለኝ ባይ ነኝ:: እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አንድነት ፓርቲ ውስጥ ነበርኩ:: አመራርም ውስጥ ነበርኩ:: አሁን ከፓርቲው የመልቀቂያ ደብዳቤ አቅርቤአለሁ:: ነገር ግን የመልቀቂያ ጥያቄዬ ይፅደቅ አይፅደቅ እስካሁን የሚታወቅ ነገር የለም:: ሀገሬን በምንም መልኩ ለማገልገል ዝግጁ ነኝ::

***ይቅርታ ዶ/ር ያዕቆብ... በቅርቡ ወደ አሜሪካና አውሮፓ ተጉዛችሁ ስለፓርቲያችሁ እንቅስቃሴ አስረድታችሁ ከተመለሳችሁ አንድ ወር እንኳ ሳይሞላ ከፓርቲው የመልቀቂያ ደብዳቤ ማቅረብዎ በህዝብ ውስጥ ምን ስሜት የሚፈጥር ይመስልዎታል?***

እ!... አሁን በዝርዝር ስለዚህ ጉዳይ መግለፅ አልፈልግም:: በሌላ ጊዜ ብንነጋገርበት ይሻላል:: መጀመሪያ ያቀረብኩት ማመልከቻ ውሳኔ ያግኝ እስቲ::

***ከተነሳ አይቀር ብለን ነው....***

መጀመሪያ ውሳኔ ካገኘ በኋላ በሰፊው ብንነጋገርበት ይሻላል:: ግን! በደፈናው እኔ ከፓርቲው አመራርነት ለመልቀቅ የፈለግኩት ለሌላው ምሳሌ ለመሆን ነው:: እንደሚታወቀው በአገራችን አንዴ ስልጣን ላይ ከተወጣ ወይም የፓርቲ አመራር ከተሆነ ለ20 እና 30 አመታት ነው የሚቆየው:: ይኼ ሁኔታ በእውነት መቀየር አለበት:: ወጣቶችም ሀላፊነት ሊሰጣቸው ይገባል:: ፓርቲ እኮ ወደፊት ሃገሪቱን የሚረከቡ ሰዎች መሰልጠኛ መሳሪያ ቦታ ነው:: ወጣቶች ፓርቲ ውስጥ ከገቡ በኋላ የሀገሪቱን አመራር በሚረከቡበት ጊዜ ልምድ የሚያገኙበት ቦታ ነው በሚል እምነት ነው የመልቀቂያ ደብዳቤ ያቀረብኩት::

***ግን እንደው ከባህር ማዶ ተመልሳችሁ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ መልቀቂያ ማቅረብዎ በደጋፊዎቻችሁ ዘንድ ምንም የሚፈጥረውን ስሜት የለም?***

አስቤበታለሁ:: መልቀቂያ የማቅረብ ሀሳቤ ዛሬ የመጣ አይደለም:: ቀደም ሲልም ያሰብኩበት ጉዳይ ነው::የስራ ባልደረቦቼም ያውቃሉ:: ነገር ግን በአንድ ወቅት መወሰን ያስፈልጋል:: ያ ጊዜ ደግሞ ከአሜሪካ ከተመለስኩ ጥቂት ቀናት በኋላ ሆነ::

*በውጪ አገር ቆይታችሁ ወቅት የምትከተሉት ሰላማዊ የትግል ስልት አያዋጣም የሚል ተደጋጋሚ ሙግት ሲገጥማችሁ እናንተ ደግሞ እንደሚያዋጣ በጣም ትከራከሩ ነበር:: አሁንም የሰላማዊ ትግል ዕምነትዎ እንዳለ ነው?*

እኔ ሌላ አማራጭ አለ ብዬ አላስብም:: የሀገራችን ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው:: ከዚህ አዙሪት መውጣት አለብን:: የፈጀውን ያህል ጊዜ ይፍጅ የፖለቲካ ትግሉ ሰላማዊና ሰላማዊ ብቻ መሆን አለበት:: ሁለት ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ ምክንያት ጦር የሚማዘዙበት ምክንያት አይታየኝም በጠረጴዛ ዙሪያ ጉዳያቸውን መፍታት አለባቸው:: በእርግጥ ሰላማዊ ትግል ከባድ ነው:: ረዥም ጊዜ ሊወስድ ይችላል:: ቢሆንም ሌላ አማራጭ የለም:: የትጥቅ ትግል የሚሳካ ቢሆን እንኳ አልደግፈውም:: የሚሳካ ቢሆን እንኳ ሰው አልቆ፣ ንብረት ወድሞ፣ ሀብት ባክኖ፣ በህዝብ መሃል ጠላትነት ሰርፆ ነው መሳሪያ የያዙ ሰዎች የሚያሸንፉት:: በዛ መልኩ ለውጥ ቢገኝ አዲሱ ከነበረው የባስ የሚሆንበት ሁኔታ ይመጣል:: ስለዚህ በኢትዮጵያ ሁኔታ ከሰላማዊ ትግል አማራጭ ውጭ የሚጠቅም የለም::

*ንብረት መውደም፣ ሀብት መባከን፣ የሰው ህይወት መጥፋት፣ በዘርማጥፋት ወንጀል መከሰስ... ወዘተ በሰላማዊ ትግል ውስጥ አይከሰቱም?*

ሊከሰቱ ይችላሉ:: ግን እጅግ ባነሰ ሁኔታ ነው:: የትጥቅ ትግል ዓላማው መገዳደል ነው:: በጦር ሃይልና በመሳሪያ መሸናነፍ ነው:: ሰላማዊ ትግል ግን ዓላማው መገዳደል አይደለም:: ስለዚህ በሁለቱም መሃል ብዙ ልዩነት አለ::

*ዶ/ር ያዕቆብ! እርስዎና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የቅርብ ጓደኛሞች ነበራችሁ:: የአንድ ፓርቲ አመራርም ሆናችኋል፣ አብራችሁ ታስራችኋል:: አሁን ደግሞ ሁለታችሁም በዓላማም በዒላማም ተለያይታችኋል:: ዶ/ር ብርሃኑ ለውጥ ለማምጣት የተለየ የትግል ስልት መከተል ያስፈልጋል ይላሉ:: እርስዎ ደግሞ ሰላማዊ ትግል ብቻ ነው አማራጩ ይላሉ:: አሜሪካ አገር በሄዱ ጊዜ ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ተገናኝታችሁ በአመለካከታችሁ ልዩነት ዙሪያ አልተወያያችሁም? አልተነቃቀፋችሁም?*

የነበርነው በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ ስለሆነ እኔና ዶ/ር ብርሃኑ በአካል አልተገናኘንም:: በስልክ ግን ረዥም ውይይት አድርገናል:: የውይይታችን መደምደሚያ የሆነው ከእንግዲህ መነቃቀፍ ይቁም የሚል ነው:: እኔ ሀይል የተቀላቀለበት የትግል ስልት የመረጡ ሁሉ ወደ ሰላማዊ ትግል ይምጡ እኛን ይቀላቀሉ ብዬ ሀሳቤን አስረዳሁት:: እሱ ደግሞ ሰላማዊ ትግል አያዋጣም የሚል የራሱ ዕምነት አለውና አልተቀበለኝም:: በመጨረሻ ሁላችንም በመረጥነው ስልት እንንጓዝ፣ ነገር ግን መነቃቀፉ መወራረፉ፣ መተቻቸቱ አስፈላጊ አይደለምና ይቁም በሚል ሁለታችንም ተስማማንና ውይይታችን አበቃ::

*በአሜሪካን አገር የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እንቅስቃሴ አንድነት ፓርቲ ደጋፊ እንዲያጣ አድርጓል:: በዚህም የተነሳ በጠራችሁት ስብሰባ ላይ ደጋፊ አላገኛችሁም ወይም ከ10 እና ከ20 ሰው የበለጠ ማግኘት አልቻላችሁም ይባላል:: ይኼ ነገር እንዴት ነው?*

በፍፁም ውሸት ነው:: እኔ በተገኘሁበት ሶስት ስብሰባ ነበር የጠራነው:: አንዱ በቦስተን የተደረገው የፓርቲው አመራር አባላት ስብሰባ ነው:: በዳላስ በተደረገው ስብሰባ ከመቶ ሰው በላይ ተገኝቷል:: በዋሽንግተን ግን ከ200 ሰው በላይ ነበር የተገኘው:: በጣም አስደሳች ስብሰባ ነበር የተደረገው::

*እናንተ ስብሰባ በጠራችሁበት ተመሳሳይ ወቅት ግንቦት 7 የጠራው ስብሰባ ላይ በርካታ ህዝብ መገኘቱን ሰምተናል:: ከዚህ አንፃር የአንድነት ስብሰባ ላይ የተገኙትን ሰዎችን ቁጥር ስታነፃፅሩት እንዴት ነው?*

እኔ የግንቦት 7ን ስብሰባ አላየሁም መቼና ምን ያህል ህዝብ እንደተገኘ የማውቀው ነገር አልነበረም::

*ከእስር ቤት ወጥታችሁ ወደ አሜሪካና አውሮፓ በሄዳችሁ ጊዜ እጅግ በጣም ብዙ ደጋፊ ነበራችሁ:: አሁን ደግሞ ደጋፊዎቻችሁ በጣት የሚቆጠሩ ሆነዋልና ህዝብን ተስፋ የሚያስቆርጥ የፓለቲካ ስልት እየተከተላችሁ አይመስልዎትም?*

መቼም ከቃሊቲ እንደተፈታንና አሁን በውጭ አገር የሚገኘው ህዝብ ስሜት ተመሳሳይ ነው ማለት አይቻልም:: አዝኖ፣ ተበሳጭቶ፣ ልቡ ተሰብሮ ወደ ቤቱ የገባው ህዝብ ብዙ ነው:: በቁጣ፣ በንዴት፣ በብስጭት ነው ሰዉ ቤቱ የገባው:: ያም ሆኖ ግን የተወሰኑ ሰዎች ደግሞ በብስጭት ብቻ የሚሆን ነገር የለም በሚል ተስፋ ባለመቁረጥ የሚታገሉ አሁንም አሉ:: ቁጥራቸው እንደመጀመሪያው አይደለም፣ በጣም በጣም ቀንሷል::
ነገር ግን ይኼ ነገር እያንሰራራ ነው:: በአማሪካም ሆነ በሌላ አገር የሚገኘው ደጋፊ የፖለቲካ ግለትም ሆነ ቅዝቃዜን የሚወስነው እዚህ አገር ውስጥ የሚደረገው ትግል ነው:: ለምሳሌ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ 34 ቢሮዎችን በተለያዩ ክልሎች መክፈቱ በተሰማ ጊዜ ሰዉን በጣም አነቃቃው:: እኔም በተዘዋወርኩባቸው የአሜሪካ ከተሞች ያነጋገርኳቸው ሰዎች አሁን ተስፋቸው እንደለመለመ ነግረውኛል:: እና የውጭውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚወስነውና ተስፋ የሚያሳድረውም ሆነ የሚያስቆርጠው እዚህ የሚደረገው እንቅስቃሴ ነው::

*በፖለቲካ ጉዳይ የሚዘግቡ አንዳንድ ድረ ገፆች በአንድነት ፓርቲ እንቅስቃሴ የተበሳጩ መሆናቸውን የሚያመለክት ዘገባ እያቀረቡ ነው:: ምክንያታቸው ምን ይመስልዎታል?*

ምክንያታቸው አንድም የፉክክር ጉዳይ ነው:: በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረኩን ሁሉም ሊቆጣጠረው ይፈልጋል፣ በበላይነት ሊወጣ ይፈልጋል:: የእኛም ፓርቲ ሆነ ሌላው የኢትዮጵያን ፓለቲካ በበላይነት መቆጣጠር ይፈልጋል:: ነገር ግን እኛ እንደመመሪያ የተቀበልነው በማንም ፓርቲ ላይ ዘለፋ አለማካሄድን ነው:: ያም ሆነ ይህ በአንድነት ፓርቲ ላይ ዘለፋና ትችት መብዛቱ የፓርቲውን ጥንካሬ የሚያስመሰክር ነው ማለት ነው:: አንድነት ፓርቲ እየጠነከረ ነው ማለት ነው:: የሌሎች ደጋፊዎች ወደ አንድነት በመጡ ጊዜ አንድነት ይጠነክራል:: ስለዚህ መተቸቱ አይቀርም::

*አንዱ ፓርቲ ሌላውን ፓርቲ መንቀፉ ጤናማ ነው ይላሉ?*

እኔ በእውነቱ ነቀፋው በጨዋ መልክ ከቀረበ፣ የዘለፋ ቃላት ካልተቀለቀለበትና ይህ ስልት ያዋጣል ያ ስልት አያዋጣም የሚል አይነት ውይይት ጤነኛ ነው ብዬ አምናለሁ:: ምክንያቱም አንዱ ሌላውን ሊያሳምነው ይችላል::

*ከኢህአዴግ ባህርይ፣ ከህዝቡ አስተሳሰብና ከመሳሰሉት አንፃር ሰላማዊ ትግል ውጤት ለማምጣት ምን ያህል አቅም አለው ብለው ያምናሉ?*

አሁን ሰላማዊ ትግል ለውጥ የማምጣት ጥንካሬ አለው፣ አቅም አለው ለማለት አልችልም:: ግን ደግሞ የሚገነባ ነው:: በአሁኑ ወቅት ግን ስልጣን መረከብ የሚያስችል የሰላማዊ ትግል ደረጃ ላይ ተደርሷል ብዬ ልደመድም አልችልም::

*አንድነት ፓርቲ በፓርቲነት ስለመቀጠሉ፣ በሚቀጥለው ምርጫ ተወዳድሮ አሸናፊ ስለመሆኑ፣ ስላለመከፋፈሉ፣ በአመራሮቹ ፖለቲካዊ ፅናት ላይ ምን ያህል እርግጠኛ መሆን ይቻላል?*

በዚህ ዓለም እርግጠኛ መሆን የሚቻልባቸው ነገሮች በጣም በጣም ጥቂት ናቸው:: በተለይ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: አፄ ኃ/ስላሴ አንድ ነገር ተጠይቀው፤ ይኼንን ለማወቅ ነቢይ መሆን ያሻል ብለው መልሰው ነበር:: እና እኔም ነቢይ አይደለሁም:: ነገር ግን መከፋፈል ሊኖር ይችላል፤ መጠላለፍ ሊኖር ይችላል:: በሀገራችን ፓለቲካ ሂደት ውስጥ በጣም በበዛ መልኩ ተከስቷል:: ገኘው ፓርቲ ጭመር በተደጋጋሚ ተከፋፍሏል::
ነገር ግን ይኼንን በመገንዘብ አንድነት ፓርቲ አንዳንድ መቆጣጠሪያ አስቀምጧል:: ለምሳሌ የግለሰቦችን ገኖ መውጣትና ፓርቲው የተመካት ዝንባሌ እንደገና እንዳይከሰት በደንቡ ውስጥ መጠበቂያዎች አስፍሯል:: ያም ሆኖ ግን አንድነት አይሰነጣጠቅም ብዬ ቃል ልገባ አልችልም:: ማንም ቃል ሊገባ አይችልም::

***ከገዢው ፓርቲ ረገድስ? ፓርቲው ስሙን ሰላለመነጠቁ ወይም ቢሮው ስላለመዘጋቱ ምን ዋስትና አለ?***

ምንም ዋስትና የለም:: ግን ይኼን ነገር ትግሉ የሚወስነው ነው:: ፓርቲው ተጠናክሮ ከተገኘና የህዝብ ድጋፍ ካለው ማንም ሀይል ተነስቶ ስሙን ሊነጥቅ፤ ቢሮውን ሊዘጋ አይችልም:: ይኼን የሚወስነው የፓርቲው ጥንካሬ እንጂ የመንግስት ችሎታ አይደለም::

***ከጥቂት ደቂቃ በፊት ከአንድነት ፓርቲ ለመልቀቅ ማመልከቻ ማስገባትዎን ነግረውን ነበር:: አሁን ደግሞ ስለፓርቲው ጥንካሬ እየነገሩን ነው:: አሁንም መንፈስዎ ከፓርቲው አልተነጠለም ማለት ነው?***

እኔ ከአመራርነት እንጂ ከፓርቲ አባልነት ለመልቀቅ አልጠየኩም:: የፓርቲው አባል ነኝ:: የታዘዝኩትን እሰራለሁ:: ከአመራር ለመልቀቅ ያቀረብኩት ማመልከቻ የሚወስነው ከሰኞ (ከትናንት ማለታቸው ነው) በኋላ ነው:: ምን እንደሚወስን አላውቅም:: ቢሆንም የፓርቲ አባልነቴን አልለቅም::

***እርስዎ ከፓርቲ አመራርነት ለመልቀቅ ያቀረቡት ምክንያት በአንድነት ፓርቲ አመራር ባለመደሰትዎ መሆኑ በአንድ ጋዜጣ ላይ ተዘግቦ ነበር:: ምክንያቱ ይኼ ነው?***

ጋዜጣው ያቀረበው ዜና በፍፁም ሀሰት ነው:: እኔ ከአመራርነት ለመልቀቅ ያቀረብኩት ምክንያት የተለየ ነው:: ወጣቶች ወደአመራርነት መምጣት አለባቸው የሚል ነው::

***ከፓርቲ አመራርነት ለመሸሽ ምክንያትዎ ፍርሃት ነው የሚል ነገር ይሰማል:: ይኼ ነገር እንዴት ነው?***

እኔ በእውነት በቅርብ ጊዜ አሜሪካ ነበርኩ:: እዛው ልቀር እችል ነበር:: አሜሪካ አገር የተሟላ ኑሮ እንዳለኝ ብዙ ሰው የሚያውቅ ይመስለኛል:: ከምርጫ በኋላ ፓርላማ እንግባ አንግባ በሚባል ግዜ አሜሪካ ነበርኩ:: እንደምንታሰር እናውቅ ነበር:: ያኔ እንኳ መጥቻለሁ እንደምንታሰር እያወቅኩ:: አሁንም 15 ቀን አይሞላም ከአሜሪካ ከተመለስኩ:: ልቀር እችል ነበር:: አልቀረሁም:: ፍርሃት ቢሆን ኖሮ እዛው እቀር ነበር::
በፍርሃት ነው መልቀቅ የፈለገው የሚለው ነገር የስም አጥፊዎች ወሬ ነው:: ማንም እንዲያውቅ እፈልጋለሁ:: ምንም የሚያስፈራኝ ነገር የለም:: መታሰር ቢኖር እንኳ አልፈራም:: ይኼን ደግሞ ስራዬ ይገልፀዋል:: የስም አጥፊዎች ወሬ ነው::

# «ጅራፍ» በአጋጣሚ የተሞላ ፊልም

በነበበ ብሩ

ዛሬም እንደተለመደው ጅራፍ ፊልምን ለመቃኘት እንሞክራለን:: ጅራፍ በከተማችን በአሁን ሰዓት እየታዩ ካሉ በርካታ ፊልሞች መካከል አንዱ ነው:: የዚህን ፊልም ቅኝት ከሜካፑ እንጀምራለን::
የሜካፕ ባለሙያውን በብዙ ፊልሞች ላይ ባናየውም ሌላ ተስፋ ሰጭ ሆኖ አግኝተነዋል:: በተለይ የአደጋዎቹ ትዕይንቶች ላይ ብቃቱን ተጠቅሞ ጥሩ የሜካፕ ጥበብ አሳይቶናል:: ይህ ብቃቱ ግን በገፀ ባህርያቱ ላይ (ከሰለሞን ቦጋለ በስተቀር) አልተንፀባረቀም:: አንዳንድ ትዕይንቶች ላይ ያየነውን ተሰጥኦ በገፀ ባህሪያቱም ጭምር በአጠቃላይ ሜካፕ በሚፈለጉት ትዕይንቶች ሁሉ ላይ መታየት ነበረበት፡ በተረፈ ግን ጥረቱን ሳናደንቅ አናልፍም::
የካሜራ ባለሙያው ጥበብ ብዙ አይመስጥም:: ምክንያቱም አንዳንድ ትዕይንቶች ላይ እያየነው ያለው ሰው ማን እንደሆነ ይጠፋናልና፡ እናም ካሜራ ማኑ ባለሁለት ስብዕና ነው፤ ወይም ሁለት ሰዎች በካሜራ ስራው ላይ ተሳትፈዋል እስክንል ድረስ ግራ አጋብቶናል:: ይኼ ቢታሰብበት ለፊልሙ ጥንካሬ አስተዋፅኦ ይኖረው ነበር::
በእውነቱ ኤዲቲንጉ ጥሩ ነው:: ቢያንስ ፊልሙ ሲያልቅ አንረበሽም:: በተለይ ፊልሙ ሲያልቅ ካፕሽን (ርዕስ) እየተፃፈ የምናያቸው ምስሎች ያዝናናሉ:: የተቀመጡበት ቦታም ጥሩ ነው:: ኤዲተሩ ለወደፊቱ አሪፍ ስራ ይሰራል የሚል ግምት አለን::
በመቀጠል የምንቃኛቸው ተዋንያኑን ነው:: በቅድሚያ የምንቃኘው ዮሴፍን ነው:: መለኮታዊ ሀይል ያለው ገፀ ባህሪ በህንድና ቆየት ባሉ የአሜሪካ ፊልሞች ላይ በብዛት እንመለከት ነበር:: በገሀዱ አለም ካለው ስብዕና ከፍ ያሉ፣ ተወዳጆች፣ እጅግ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው፣ ማንኛውንም ሁኔታና ችግር ውስጥ ማለፍ የሚችሉ ወዘተ ማለት ነው:: የዮሴፍን ገፀ ባህሪ የወከለው የፊልሙም ዳይሬክተር ጭምር ነው:: ገፀ ባህሪው ተወዳጅ፣ የሚታዘንለት፣ ተፈቃሪ፣ ተባራሪ፣ ብልሃተኛ፣ በችሎታ የተካነ ሰዓሊ፣ ሙዚቀኛ፣ ቴአትረኛ፣ በአጠቃላይ በአንድ ሰው ውስጥ በብቃት ይኖራሉ ብለን የማንገምታቸው ችሎታዎች ሁሉ የታጨቀበት ነው:: እዚህ ላይ ዳይሬክተሩ ይህን ሁሉ ችሎታ ለራሱ ብቻ ያደረገው በስስት ያስመስልበታል:: የፊልሙም በሽታ ይሄው ገፀ ባህሪ ነው:: እውነት ለመናገር ይህን ሁሉ ችሎታ ጠራርጐ ለራሱ ገፀ ባህሪ ሲያሸክም ዳይሬክተሩ ራሱ ሌላ ዳይሬክተር ያስፈልገው ነበር ብንል አልተጋነነም:: ከነ አካቴው ዮሴፍን ከፊልሙ ንቅል አድርገን ብናስወጣው የሚጐድል ነገር የለም:: ካሜራው በአንድ መስመር ይዞን መጓዝ ችሎ ነበር:: ዮሴፍ ግን ፊልሙን በጥብጦታል «በጥባጭ ካለማን ጥሩ ይጠጣል?» አሉ እማትርፌ:: ስዕል ሊሸጥ ሄዶ ኦረጋን ይመታል፤ በዛው ደግሞ የሚማረክ ሰው አለ:: በምሽት እህቱን እያሳሳቀ ሳለ ወደ ቤቱ እንግዳ ሲመጣ በቀልዱ ይገፋበታል:: በአገራችን እንግዳ ክብር ይሰጠዋል፤ ለእንግዳው ክብር ሲባል እንኳን ለቀልዱ ለከት ቢያበጅለት ጥሩ ነበር:: የት/ቤቱ ትዕይንት ላይ ልጅቷ ስትመጣ ሊያስቀን ይንተባተባል:: ይሄ ከገፀ ባህሪው ስብዕና ውጭ ነው:: ባላጠፋው ጥፋት ይሸሻል:: ስትመጣ ሊያስቀን ይንተባተባል::ሌላም ሌላም.... የካፍቴሪያው ትዕይንት፣ ራሱን ለውጦ የሚወጣበት ወዘተ እያልን ብንሄድ ይህንን «አስደናቂ» ገፀ ባህሪ ያለበቂ ምክንያት በፊልሙ ውስጥ ሲንከላወስ እናየዋለን:: ለምን? ይሄ በግልፅ አማርኛ አላስፈላጊ ትርፍ ለማፈስ ወይም ደግሞ ርካሽ ዝና ለመግኘት ሲባል የተደረገ የገፀ ባህሪ ግንባታ ነው:: ዘመኑንና ህብረተሰቡን የዘነጋ እና ፍፁም የራስ ወዳድነት ዛር የሰፈረበት ገፀ ባህሪ ነው:: ሊታሰብበት ይገባ ነበር::
አቶ ብርሀኑን እንዲህ ቃኘናቸው:: እኚህ ትልቅ ሰው ነገሮችን እንዲመረምሩ ተደርገው ያልተሳሉበት ምክንያት ግልፅ አይደለም:: አቶ ብርሀኑን ቤት ውስጥ በሙሉ ሱፍ ልብስ አይተናቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ በቢጃማ እንዲሄዱ የተደረጉበት ምክንያት ምንድነው?

በአጠቃላይ እድሜ ማለት ምን እንደሆነ በሀገራችን ፊልሞች በአብዛኞቹ ላይ አይንፀባረቅም:: እኔ የሚገርመኝ የደራሲው ስህተት ከኤዲተሩ፤ የኤዲተሩ ስህተት ከዳይሬክተሩ፤ የዳሬክተሩ ስህተት ከአዘጋጁ እንዴት እንደሚያልፍ ነው፤ ወይስ ሁሉም አንድ አይነት መነፅር አድርገው ነው የሚሰሩት:: ኧረ ጉድ ነው ጉበዝ! የወለደ የከበደ ሰው ስንል ለነገ ትውልድ ማስተማር ያለበት ከምንም በላይ ስራ መውደድ ነው:: እነዚህ ፊልሞች ግን ስስ ሆነው እናገኛቸዋለን::
ገፀ ባህሪዎቹ አይናቸውን ታስረው እንዲናገሩ ብቻ የተደረጉ ናቸው ለማለት ያስደፍራል:: ለምሳሌ ሳሮንን እንውሰድ:: ማነው የሚያሳድደኝ? ምንስ ትዝታ ትቷል? ብላ አትጠይቅም:: ይህን ለመጠየቅ ድፍረትም የላትም:: በቀጭን ገመድ ታስራ ስትጉተት ነው የምናያት:: እድሜዋና የትምህርት ደረጃዋ ነገሮችን ለመመርመር የሚያበቃት ቢመስልም እንድትጠቀምበት ተደርጋ አልተሳለችም::
በላይን እንውሰድ፤ በእርግጥ አካላዊ ገፅታው በቆንጆ ሁኔታ ተለውጧል:: የፊት አጨዋወቱና የጥራቱ ነገር የሚታማ ባይሆንም ቆም ብሎ የሚያስብባቸው አጋጣሚዎች በፊልሙ ውስጥ ነበሩ:: ነገር ግን እነዛን አጋጣሚዎች አይጠቀምባቸውም::
ሌሎች አንዳንድ ትዕይንቶችን ስናይ ጥያቄን እናነሳለን:: ለምሳሌ የደፈራውን ትዕይንት እንውሰድ:: እዛው ቤት ውስጥ የራሱ ሴት እያለች እንዴት ሌላ ሴት ሊደፍር ይነሳሳል? እያደረገ ያለውስ ነገር ለዚህ ነገር ይጋብዛል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች በገፀ ባህሪው አሳሳል ላይ ሊመለሱ የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው:: በእርግጥ ገፀ ባህሪው አጨዋወቱ ጥሩና ከነዚህ ሁሉ ገፀ ባህሪያት ጉልቶ ቢታይም የልባችንን የሚሞላ አንዳች ስሜት አይሰጠንም::
በፊልሙ ውስጥ የተወከሉትን ፖሊሶች እኛ እንመርምራቸው:: በቂ የክትትል ፍንጭ እያገኙ በዝምታ ያልፉታል:: ይሄ ከፖሊስ መቼም አይጠበቅም:: የሚፈልጉትም ነገር በፍፁም ግልፅ አይደለም:: እንደፈለጉ የሚበርቁ ፖሊሶችን አይተን በዚያው ቅፅበት የወንጀለኛ ልብስ ጠረጴዛ ላይ ደርድረው ስንመለከት ግራ ግብት ይለናል:: እነዛ እንደፈለጉ ያደርጉ የነበሩ ፖሊሶች ወዲያው ከአሜሪካ የፊልም ፖሊሶች የተማሩትን ጥበብ ሲያሳዩ እንዴት  እንድንል እንገደዳለን:: በጥቅሉ በዚህ ፊልም ውስጥ የሁለት አለም ፖሊሶችን እናገኛለን::
ወሮበሎቹን አቀራረፅ  የተጋነነ ነው:: ት/ቤት ድረስ ገብተው ሰው ለማገት ሲሞክሩ እና በአደባባይ ካፍቴሪያ ውስጥ ሰው ሲያመናጨቁ እናየቸዋለን:: ምንም ለራሳቸው ከለላ የላቸውም:: ልብ ሊባል የሚገባው ት/ቤት ሄደው ሰው ለማገት ሲሞክሩና በጠራራ ፀሀይ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ካፍቴሪያ ውስጥ ገብተው ሲፈነጩ ምንስ ወሮበላ ዱርዬ ቢሆኑ የህግ የበላይነት ይጠፉቸዋል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው:: ይሄ በጣም ተጋኗል:: በዚያ ላይ ለፊልሙ ምንም ጠቀሜታ የሌላቸው የስፖርት ወሬዎችን እንሰማለን:: በዚህ ትዕይንት ላይ ፖሊሶቹ ከወሮበሎቹ፤ ወሮበሎቹ ከፖሊሶች ብዙም ለውጥ የላቸውም:: ምክንያቱም ሁለቱም ያላቸው ስብዕና አንድ አይነት ነውና::
ወደ ደራሲው እንምጣ:: በመሰረቱ አንድ ደራሲ መንፈሱ ሰፊ ቢሆን ይመረጣል:: ገፀ ባህሪያቱ በበዙ ቁጥር ስለ እያንዳንዳቸው በቂ እውቀትና ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ድርሰት የስሜት ስራ እና የተሰጥኦ ጉዳይ ብቻ አይመስለኝም:: ድርሰት የእውቀት፤ የሀላፊነትና የመሪነት ጉዳይም ጭምር እንጂ:: ጅራፍ የተሰኘውን ፊልም ድርሰት ጠቅለል አድርገን ስንመለከት መሰረት ያላቸው ገፀ ባህሪያት የሉትም:: በጠቅላላ ድርሰቱ አጋጣሚዎችን መሰረት ያደረገ ነው:: በጅራፍ ፊልም ውስጥ የታጨቁት አጋጣሚዎች ከመብዛ ቸው የተነሳ ደራሲውም የፃፈው በአጋጣሚ ነው እንዴ እንድንል ያደርገናል:: ስለፖሊስ ባልደረቦች ሲፅፍልን አንዳቸው እንኳን የምርመራ ሂደትን ወይም የምንጭ አጠቃቀምን ወዘተ ሲያከናውኑ አያሳየንም:: ስለፖሊም ሆነ ስለ ሌላ ባለሙያ ሲፃፍ በዛ ሙያ ውስጥ ካለ ሰው ጋር በመያየት ግንዛቤና እውቀት መቅሰም ሲቻል ሰውን በውሸት ጅራፍ መግረፍ ምን ይባላል?
በአጠቃላይ ከጅምሩ መሰረት ያላቸው ገፀ ባህሪያት ሲኖሩ ስቃያቸውንም ሆነ ደስታቸውን አብረን እንካፈላለን:: በሚገባ የተሰራ ገፀ ባህሪ የምናውቀውን ያህል ይቀርበናልና ልባችንን ይነካናል:: ይሄ ሁኔታ በጅራፍ ፊልም ድርሰት ውስጥ የለም::
እንዲያም ይሁን እንጂ የዳይሬክተሩ ጥረት መልካም ነው:: የተቻለውንና አቅሙ የፈቀደውን ያህል ሊያሳየን ሞክሯል:: ዳይሬክተሩ በተቻለው መጠን አስገራሚ (አድቬንቸር) የፍቅር ታሪክ አክሽን፣ ሰስፔንስ፣ ኮሜዲ በአጠቃላይ የፊልም አይነቶችን

በአንድ ላይ አምቆ አምጥቷል። ነገር ግን ትርፍና ተቆርጠው ቢወጡ ዋናውን መሰረት የማይነኩ ሽርፍራፊ ታሪኮች ቢከረከሙ ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር። በአጠቃላይ ፊልሙ ሊለን የፈለገው ነገር ቢኖርም በጠንካራ ታሪኩ ውስጥ ወይም ምሉኡነት ባላቸው ገፀ ባህሪያት ስላልተዋቀረ በደምሳሳው አይተን እንጨርሰዋለን እንጂ የልባችንን ሊያደርስልን አቅም ያንሰዋል። ምክንያቱም ድርሰቱ መሰረት የሌለውና በአጋጣሚ የተሞላ መሆኑ በአጋጣሚ እንጂ ታስቦበት እንዳልተፃፈ ምስክር ነውና። ስለዚህ በሲኒማ ሙያ ላይ የተሰማራችሁ ሁሉ ራሳችሁን በእውቀትና በራስ መተማመን እንፃችሁ እንጂ በአጋጣሚ አትስሩ ባይ ነን።

ቸር እንሰንብት።